# የመናፍቃን ማንነትና መልሶቻቸው



ከዲያቆን አሐዱ አስረስ

## ማውጫ

1. መግቢያ .......... 5

2. የተለያዩ እምነቶች እንዴት ተመሠረቱ .......... 8

3. ካቶሊክ ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ጋር ያለው ልዩነት .......... 12

4. በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንና በኦርቶዶክስ መለካውያን መካከል ያለው ልዩነት .......... 26

5. በኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያንና በፕሮቴስታንት መካከል ያለው ልዩነት .......... 27

ልዩ ማውጫ (Index) መጨረሻ ገጽ ላይ ይዩ። የፈለጉትን ክፍል ለማንበብ ይረዳዎታል።

## ልዩ ማውጫ

### ትርጉም


- ኦርቶዶክስ ተዋህዶ .......... 9
- ካቶሊክ .......... 10
- ኦርቶዶክስ መለካውያን .......... 10
- ፕሮቴስታንት .......... 11


### የልዩነት ነጥቦች
### ካቶሊኮች


- በክርስቶስ .......... 18-16
- በማርያም .......... 17
- በታቦት .......... 19
- በጾም .......... 21-22
- በክህነት .......... 23-24
- በቊርባን .......... 25


### ፕሮቴስታንት


- በቅዱሳት መጻሕፍት .......... 28-29
- በክህነት .......... 32-33
- በጥምቀት .......... 34
- በቊርባን .......... 47

- በታቦት በሥዕል በመስቀስ በቤ/ክርስቲያን ................ 53

**<u>የኦርቶዶክስ ትምህርት</u>**

**<u>ጥምቀት</u>**

- የ40ና የ80 ቀን ጥምቀት ................ 36
- የአጠማመቅ ሥርዐታችንና ፍቺው ................ 37
- በጥምቀት የምናገኛቸው ነገሮች ................ 39

**<u>ቁርባን</u>**

- የአይሁድ ተቃውሞ ................ 49
- ሥጋና ደሙን ለመቀበል ምን መሆን አለብን ................ 51

**<u>ታቦት</u>**

- ማብራሪያ ................ 53
- ጽላት የእግዚአብሔር ነው ................ 57
- ለታቦት የሚደረግ የጸጋ ስግደት ................ 58

**<u>ቤተክርስቲያን</u>**

- ማብራሪያ ................ 67
- ለምን እንሳለማለን ................ 69
- የክርስቲያኖች አንድነት ................ 74

**<u>ሥዕል</u>**

- ማብራሪያ ................ 76
- በብሉይ ኪዳን ................ 79
- በአዲስ ኪዳን ................ 81
- ፊት ቆሞ መጸለይ ................ 82
- የጸጋ ስግደት ................ 85

**<u>መስቀል</u>**

- ታሪካዊ አመጣጥ ................ 86
- የመስቀል ምሳሌዎች ................ 87
- በማዕድናት የሚሰራው መስቀል ትርጉም ................ 91
- መስቀል በኢትዮጵያ ................ 91

**<u>ጾም</u>**

- ጾም ................ 93
- ምን ይጠቅማል ................ 93
- የጾም ዓይነቶች ................ 104
- የአዋጅ ጾም ................ 105
- ዓቢይ ጾም ................ 106
- የሳምንታቱ ትርጉም ................ 107
- ከነቢያት ጾም እስከ ገሃድ ................ 112-117
- የእመቤታችን ትንሣኤ ................ 114
- በጾም የማይበሉ ................ 118

**<u>በፕሮቴስታንት እና በጆሆቫ የሚነሱ ጥያቄዎች</u>**

- በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ................ 30
- በጥምቀት ላይ ................ 42
- በቁርባን ................ 47
- በታቦት ................ 59
- በመሳለም ................ 73
- በመስቀል ................ 88
- በጾም ................ 119

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ትምህርት ሥርዐትና ደንብ መሠረት የተዘጋጀ

All Right reserved

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

## ማሳሰቢያ

በተቻለዎ መጠን ይህን መጽሐፍ ሲያነቡ መጽሐፍ ቅዱስ ባይለይዎት መልካም ነው።

## መግቢያ

በዚህ ባለንበት በ20ኛው መቶ ክ/ዘመን ሁሉም ነገር በበቂ ምክንያት እየተገለጸ የሚሄድ መሆኑ የታወቀ ነው። እንዲሁም ሃይማኖትንም የሚመለከቱ ነገሮች ሁሉ በዚህ መልኩ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ያላቸውን ቁርኝት እያንዳንዱ የእምነት ድርጅት ለማስጨን ይፈልጋል። እኛም እንዲሁ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን እምነታችንን ለመግለጽ እንፈልጋለ። እንደ ጥንቱ የእናት የአባቴ ሃይማኖት ነው ብሎ መሄዱ እጅግ አስቸጋሪ ሆኖአል። ስለሆነም እያንዳንዱ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረገውን ሃይማኖቱን ለመግለጽ መሞከር አለበት። ካልሆነ ግን ተጠራጣሪዎች በሆኑት መናፍቃን ከእውነት መንገድ ልንወጣ እንችላለን።

ይህ ደግሞ ሊወገድ የሚችለው መጽሐፍ ቅዱስንና ሃይማኖታችንን ስንረዳ ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ብዙ ነገር ያስተምረናል። በተለይም መናፍቃን እኛን መስለው በመምጣት እንደሚያጠምዱ ሲናገር “የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ” ይላል ማቴ. 7÷15 በተለይም ተአምራት እናደርጋለን በማለት ከሚያስቱ ሰዎች እንድንጠንቀቅ እንዲሁም ተአምራት ሁሉ የእምነት መለኪያ ስላልሆነ እያንዳንዱ በዚህ ከመሳት እንዲጠነቀቅ እንዲህ ይላል “በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት አይገባም ያን ጊዜ ብዙዎች ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህ አጋንትን አላወጣንምን? በስምህ ተአምራት አላደረግንምን? ይሉኛል የዚያን ጊዜም ከቶ

አላውቃችሁም እናንተ አመፀኞች ከኔ ራቁ ብዬ እመሰክር ባቸዋለሁ" ማቴ. 7፥20-23 በአምላክ ዘንድ ያልታወቀ አገልግሎት ስለሆነ ሐሰተኛነቱን ያረጋግጣል። ዛሬም እንዲህ በማለት ብዙውን ለመሳብ የሚራወጡ ሁሉ ጌታ እንደማያውቃቸው ሊረዱ ይገባል። ሰውን ወደ ሞት ይመራሉ ስገዛ ምኞታቸው ማስፈጸሚያ አስተማሪዎችን ያከማቻሉ። በማለት ሐሰታቸውን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት ይገልፀዋል። ፊቃደ እግዚአብሔር የሌለበት ነውና "አንተንም የሰው ልጅ ሆይ ከገዛ ልባቸው ትንቢት በሚናገሩ በሕዝብህ ሴቶች ልጆች ላይ ፊትህን አድርግ ትንቢት ተናገርባቸው እንዲህም በል ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ነፍስን ለማጥመድ ለእጅ ድጋፍ ሁሉ መክዳ ለሚሰፉ ለሰውም ሁሉ ራስ እንደየቁመቱ ሽፋን ለሚሰሩ ሴቶች ወዮላቸው የሕዝቤን ነፍስ ብታጠምዱ በውኑ ነፍሳችሁን ታድናላችሁን? ውሸታችሁን ለሚሰሙት ሕዝቤ እየዋሻችሁ ሞት የማይገባቸውን ነፍሳት ትገድሉ ዘንድ በሕይወትም መኖር የማይገባውን ነፍሳት በሕይወት ታኖሩ ዘንድ ስለ ጭብጥ ገብስና ስለ ቁራሽ እንጀራ በሕዝቤ ዘንድ አርክሳችሁኛል" (ሕዝ. 13፥17-19) በማለት ነፉስን ወደ ሞት ስለሚሰዱና ስለሚያደርጉት ተነግሮአል። እንዲሁም ለጥፋታቸው አስተማሪዎችን እንደሚያከማቹ ወንጌሉን እንደሚያጣምሙና ልዩ ክርስቶስ እንደሚያስተምሩ የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት።

- "ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሡበት ዘመን ይመጣልና ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለ ሆነ እንደ ገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ።" 2ጢ.ሞ 4፥3።



- "የሚያናውጡአችሁ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንዳንዶች አሉ" (ገላ. 1፥8፤ ሐዋ. 15፥1-24)።
- "የሚመጣውም ያልሰበክነውን ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክ ወይም ያልተቀበላችሁትን ልዩ ወንጌል ብታገኙ በመልካም ትታገሣላችሁ።" 2ቆሮ. 11፥4 ያረጋግጥልናል።

እንዲሁም እውነተኛው መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ነገር ግን ማንም በዚህ መሠረት ላይ እንዴት እንደሚያንጽ ይጠንቀቅ ይላል (1ቆሮ.3፥11) ስለዚህ ክርስቶስ ብሎ መጥራት የመዳን ምልክት ሳይሆን ለጥፋታቸው ይጠቀሙበታል። ሁሉም ኢየሱስ እያለ መነሳቱ ሊያስደንቀን ወይም ሊገርመን አይገባም። ምክንያቱም ጌታ በማቴ. 24፥6 በመጨረሻው ዘመን ብዙዎች በስሜ ይመጣሉና በማለት ገልጾ ነግሮናል። አሁንም የእውነት መንገድ ኢየሱስ በማለት የሚገኝ ሳይሆን እውነትን በክርስቶስ ማንነት ለይቶ ማወቅ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን የጠየቃቸው ይህንኑ ነበር። ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደሆንኩ ይሉኛል? የሚል ነበር። ሁሉም የራሳቸውን መልስ ኤልያስ ነው፤ ኤርምያስ ነው፤ ከነቢያት አንዱ ነው በማለት መልስ ሰጥተዋል። ጌታ መልሶ እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ? ብሎ ጠየቃቸው ከእነርሱም አንዱ ጴጥሮስ አንተ በእውነት የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብሎ መልሷል። ጌታም "ይህንን ሥጋና ደምህ አልገለጸልህም የሰማዩ የአባቴ መንፈስ እንጂ" ብሎታል። ስለዚህ ሥጋና ደም የገለጸውን እውቀት ሳይሆን ከሰማይ አባታችን የተገለጸልንን ትክክለኛ እምነትና እውቀት ይዘን ልንጓዝ ይገባናል። ማቴ. 16፥13-20 ሃይማኖት አንዲት ናትና ኤፌ. 4፥5።

## <u>የተለያዩ እምነቶች እንዴት ተመሠረቱ?</u>

መጽሐፍ ቅዱስ እምነት አንድ መሆኑን ይናገራል። ነገር ግን ለምን ይህ ሁሉ እምነት ተፈጠረ? እግዚአብሔር እንዲህ ይላል "በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች እወቁ በእርሷም ላይ ሂዱ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ እነርሱ ግን አንሄድባትም አሉ።" (ኤር 6÷16) ሰዎች አልጠየቁም የቀደመችውን መንገድ አልፈለጉም። የራሳቸውን መንገድ መረጡ ስለዚህም ሳቱ። መንገድ ብሎ የነገረን ሃይማኖትን እምነትን ነው። ይህንኑ አጥብቀን ለመረዳት እንድንችል ደግሞ በዕብ 7÷13 "የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሯችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ የኑሮአቸውን ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው" ብሎ አረጋግጦልናል። አባቶቻችንን ምን አመኑ? ዋኖቻችን ምን አመለኩ? ምን ብለው አመለኩ? ብሎ በመጠየቅ ፍሬ ያለን ሰዎች ሆነን በሃይማኖት እነሱን እንድንመስል አስተምሮናል። ለዚህም በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጾ የማዕዘኑን ራስ ክርስቶስ ማግኘት ይቻላል። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ (ኤፌ. 2÷20) ይህን መሠረት ማግኘት መለያየት ፈጥሮአል። ማለት የሐዋርያትና የነቢያትን።

ክርስትና በጌታችን ስም ለመጀመሪያ ጊዜ የተመሠረተው በአንጾኪያ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ደቀመዛሙርትም መጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ ይለናል። ሐዋ 11÷26 ክርስትና በዚህ መልኩ በአንድነት እስከ 325 ዓ.ም. ድረስ ከተጓዘ በኋላ ኢየሱስን ፍጡር የሚል አስተሳሰብ በመነሳቱ በኒቂያ ጉባኤ በ318ቱ ዓለም አቀፍ ሊቃውንት በተገኙበት አርዮስ ከነትምህርቱ ተወግዞ ተለይቷል።

- <u>ኦርቶዶክስ ተዋህዶ፡-</u> ኦርቶዶክስ ማለት ከሁለት የጽርዕ ቃላት የተጣመረ ሲሆን ኦርቶ ማለት ቀጥተኛ፣ እውነተኛ ትክክለኛ የሚል ፍቺ ያለው ነው። ዶክስ ማለት ዶኮ ከሚለው የጽርዕ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጓሜውም አስተያየት፣ አመለካከት፣ ሃይማኖት (እምነት) ማለት ነው። ስለዚህ ኦርቶዶክስ ማለት ቀጥተኛ አስተያየት እውነተኛ ሃይማኖት ትክክለኛ አመለካከት ያለው ማለት ነው።

ተዋህዶ ማለት ደግሞ አምላክ ሰው ሆነ ሰው አምላክ ሆነ ማለት ሲሆን ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባህርይ ጌታ ነስቶ በአንድ አካልና በአንድ ባህርይ በተዋህዶ ተወለደ ማለት ነው። ዮሐ 1÷1,14፤ ገላ. 4÷4፣ ዕብ. 2÷15፣ ኦርቶዶክስና ተዋህዶ የሚለው ስያሜ ቤተክርስቲያናችን ሊሰጣት የቻለው በመጀመሪያ አርዮስ ባስነሳው የስህተት ትምህርት ቤተ ክርስቲያን ድምጿን በማሰማቷ አርዮስን በውግዘት በ325 ዓ.ም. በኒቂያ ጉባኤ ሲለይ የነበረችው የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ኦርቶዶክስ የሚል ስያሜ ስጥተዋታል። ተዋህዶ የሚለውን ስያሜ ያገኘችው በንስጥሮስ መወገዝ ማለትም በ431 ዓ.ም. በኤፌሶን ጉባኤ ላይ ነበር። የኤፌሶን ጉባኤ መነሻው የንስጥሮስ የክህደት ትምህርት በሁለት ባህርይና ሁለት አካል በሚል ያስተማረው ትምህርት ነበር።

- ካቶሊክ፡- ካቶሊክ ለመመስረት የበቃው በ451ዓ.ም. በኬልቄዶን ጉባኤ ነበር። የዚህ ጉባኤ አዘጋጆችና ጠሪዎች የሮም የጦር አለቆችና መኳንንቶች ነበሩ። ፓፓ ሊዮን ከንስጥሮስ ጓደኛ ከአውጣኪ ጋር ባደረገው የሁለት ባሕርይና የሁለት አካል ትምህርት ላይ 636 የሚደርሱ ሊቃውንት ተገኝተው ነበር። አብዛኛው የጉባኤውን ምንነት አውቆ ተረድቶ የተሰበሰበ አልነበረም። በወቅቱም ሮም በነበራት ኃይል በዚህ የኬልቄዶን ጉባኤ የካቶሊክ ሃይማኖት ሊመሰረት ችሏል። ኦርቶዶክሳዊያን ግን ይህን ጉባኤ አይቀበሉትም። ጉባኤ ከለባት ብለው ሰይመውታል። ይህም የውሾች ጉባኤ እንደማለት ነው። በዚህ ጉባኤ ወቅት መከራ ከተቀበሉት እውነተኛ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ልጆች አንዱ ዲዮስቆሮስ ነበር። የግብጹ ሊቀ ጳጳስ ዲዮስቆሮስ እውነተኛውን ሃይማኖት በመመስከሩ በጥፊ ተመቷል። በቡጢ ጥርሱ ወልቋል። የማንረሳው ሁሌ የምናስታውሰውና ለአንዲት እውነተኛ ሃይማኖት መኖር እውነተኛ ተጋድሎ የፈጸመ ሰው ነበር። መለያየትን ተቃውሟል። የአባቶችን ትምህርት እንያዝ በማለት አሳስቧል። ሐዋርያትንና አባቶቻችንን በእምነት እንድንመስላቸው አበክሮ በጉባኤው ላይ ገልጿል (ዕብ. 13፥7-10)።

ካቶሊክ ማለት ሁሉ ለሁሉ ማለት ነው።

- የግሪክ ኦርቶዶክስ (ኦርቶዶክስ መለካውያን)፡- 1054 ዓ.ም. የተመሠረተ ሲሆን ሊመሠረት የበቃው በሮሙ ፓፓና የቁስጥንጥንያው ፓትርያርክ መካከል በነበረ አለመግባባት ነበር።



- ፕሮቴስታንት፡- መሥራቹ ማርቲን ሉተር ሲሆን በ1517 ዓ.ም. ኢጣሊያ ግዛት የተመሠረተ ነው። ፕሮቴስታንት በማርቲን ሉተር ለመመሥረት የበቃው አንደኛ በሮም ውስጥ ቫቲካን ለሚሠራው የጴጥሮስ ቤ/ክርስቲያን ማስፈጸሚያ ገንዘብ ስላጠራቸው በሮሙ ፓፓ ትዕዛዝ የመንግሥተ ሰማያት መግቢያ ብለው በሸጡት ካርድ ምክንያት ሁለተኛ ከዘጠና እስከ ዘጠና አምስት በሚደርሱ ነጥቦች ላይ ያለውን ተቃውሞ በሉተንበርግ ቤተክርስቲያን ላይ ለጥፎ በመውጣቱ ምክንያት ተቃውሞው ተባብሶ ተቃዋሚ (protestant) ብሎ የራሳቸውን ቤተክርስቲያን እስከ መመሥረት ደርሶአል።

ከዚህ በኋላ የተሐድሶ ቤተክርስቲያን (Reformed Church) ተብለው የተቀሰቀሱ ሌሎች ቡድኖች ተመሠረቱ፤ እነዚህም፡-

ካልቪኒስት፡- ካልቪኒስቶች በጆን ካልቪን በማርቲን ለተር ረዳት ስም የተመሠረተ እምነት ሲሆን መሥራቹ ጆን ካልቪን ፔፑዛ በተባለ ተራራ ላይ ሁለት ሴት ልጆቹን ይዞ በመሄድ ጌታ ይመጣል ብሎ ይጠባበቁ የነበሩ ናቸው። ካልቪኒስቶች ባደረጉት እንቅስቃሴ የተነሳ በ18ኛ መቶ ክፍለ ዘመን የአድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ለመመሥረት በቅቷል። አድቬንቲስት ትምህርት ስለ ጌታ መምጣት ብቻ ነው። እነሱም በሦስት ይከፈላሉ አንደኛው ዘሰቨን ደይ አድቬንቲስት ቅዳሜን ሰንበት የሚሉ፤ ሁለተኛ ዘአድቬንቲስት ክርስቲያን ቸርች ቅዳሜና እሁድን በሰንበት የሚቀበሉ፤ ሦስተኛ ዘአድቬንቲስት ክርስቲያን አፍ ጎድ ኦፍ ዘአብርሃሚክ ፌዝ የሚባሉ ናቸው።

**<u>ሜቶዲስት፡-</u>** ሁለተኞቹ ሲሆኑ እነዚህም 26 ዲኖሚኔሽኖች አሏቸው። ከእነሱም አንዱ ባፕቲስት ሚሽነሪ ሲሆን አለቃ ወይም የቤተክርስቲያን የበላይ ጠባቂ አያስፈልግም ይላሉ ቤተክርስቲያንንም አያምኑም።

**<u>ሜኖናይት</u>**፡- እነዚህም እንዲሁ ለጴንጤዎች መመሥረት የመሠረት ድንጋይ ያኖሩ ሲሆን ዛሬ ጴንጤዎችን ከመሠረቱ በኋላ የበላይ ጠባቂ በመሆን ሥራ እየሰሩ ያሉ ናቸው።

**<u>ጴንጤዎች (Pentecostal Church)፡-</u>** እነዚህ በ19ኛው መቶ ክ/ዘመን መጨረሻና በ20ኛው ክ/ዘመን መጀመሪያ ላይ የተመሠረተ እምነት ነው። ማለትም፡ እነ ሙሉ ወንጌል (1901 ዓ.ም.)፣ መካነ ኢየሱስ፣ ቃለ ሕይወት ወዘተ... እነሱም በሁለት ይከፈላሉ። አንደኛ በሥላሴ ወይም በአንድነት በሦስትነት ያምናሉ። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስን አማላጅ ነው ይላሉ። ሁለተኞቹ ደግሞ በሥላሴ አያምኑም ሦስት አካል መኖሩን አያምኑም ያለው አንድ አካል ብቻ ነው ይላሉ። ለምሳሌ Only Jesus (የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን) ብለው ራሳቸውን ሰይመውታል። አንድ ያደረጋቸው ነጥብ ሁለት ሲሆን፡-

- አንደኛው፡- በልሳን መናገር በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ፣
- ሁለተኛው፡- በሕፃናት መጠመቅ የለባቸውም በሚለው ይለያሉ

## <u>ካቶሊክ ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ጋር ያለው ልዩነት</u>

1ኛ) የካቶሊክ ቤ/ክርስቲያን አንድ አካል ሁለት ባሕርይ ነው ትላለች። ይህም ትምህርት "ምንታዌ" Dualism ይባላል "ሁለትነት" ማለት ነው። ይህን ትምህርት የጀመረችው በ451 ዓ.ም. በፓፕ ሊዮን ቀዳማዊ ዘመን ነው። ይህም ተረፈ ንስጥሮሳዊ አመለካከት ነው። በዚህ የምንታዌ ትምህርት መሠረት ክርስቶስ ሁለት ባህርይ ሁለት ፈቃዳት አሉት ይላሉ። በመሆኑም የመለኮት ባህርይና የሥጋ ባህርይ ስላልተዋሀዱ የየብቻ ሥራቸውን መለኮት የመለኮትን ሥራ፣ ሥጋ የሥጋን ሥራ ይሠራል። ተአምራት ሲያደርግ፣ ሕሙማን ሲፈውስ፣ ለምፃም ሲያነፃ፣ ሙታን ሲያስነሣ በመለኮታዊ ባሕርዩ ነው። ሲራብ፣ ሲጠማ፣ ሲታመም፣ ሲሞት፣ በሥጋ ባሕርይው ነው ይላሉ።

በአጠቃላይ አነጋገር ካቶሊኮች የአብ ልጅና የማርያም ልጅ በማለት በመከፋፈል የአብ ልጅ የማርያም ልጅ እስከ መስቀል ቀራኒዮ ድረስ አብረው ነበሩ በቀራኒዮ የአብ ልጅ ተለይቶት ስለሄደ መከራ መስቀልን የተቀበለው የማርያም ልጅ ነው የአብ ልጅ አይደለም ይላሉ። በካቶሊኮች አነጋገር እግዚአብሔር ሞቶ አላዳነንም ይላሉ። በማቴ. 27÷46 "አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ?" ያለውን ገጸ ንባብ ይዘው የአብ ልጅ ተለይቶት ሲሄድ እሩቅ ብዕሲ የማርያም ልጅ ያሰማው የብቸኝነት ንግግር ነው ይላሉ። ደግሞ ጌታ በጌቴሴማኒ ያሰማውን ጸሎት (ማቴ. 26÷39) "አባት ሆይ ይህቺ ጽዋ ከእኔ ትለፍ ነገር ግን እንደ አንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ እንደ እኔ አይሁን" የሚለውን ገጸ ንባብ የአብ ልጅ ተለይቶት ሊሄድ ሲል ያሰማው የፍርሃቱና የደካማነቱ ጸሎት ነው። ሊሞት መጥቶ ሞትን ፈራ ይላሉ ይህም በሥጋው ብቻ ስለሆነ ነው ይላሉ።

✞ እኛ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኞች ግን በፍጹም ተዋህዶ የከበረ ነው እንላለን ይህም መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ዮሐ 1÷1 “በመጀመሪያም ቃል ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ” ይለናል ቁ 14 ላይ ስንሄድ “ቃልም ሥጋ ሆነ…” ይላል ያ ቃል ሥጋ የሆነው እግዚአብሔር ነው ይኸውም በተዋህዶ ነው። ተዋህዶ ስንል ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባህርይ አንድ ባህርይ አደረገ ማለት ነው። እንዴት ለሚለው ጥያቄ አንዱ አካል የአምላክ አካል ነው ይህ አካል ስፉሕ፣ ምሉዕ ነው፣ ረቂቅ ነው፣ የማይጨበጥ፣ የማይዳሰስ ነው፣ ሌላው አካል የሰው አካል ነው። ይህ አካል ይጨበጣል፣ ይዳሰሳል፣ ይታያል፣ ውሱን ነው፣ ጠባብ ነው፣ እነዚህን ሁለት አካላት በማዋሀድ አምላክ የሰውን ውሱን አካል በመያዝ ተጨበጠ፣ ተዳሰሰ፣ ውሱኑ የሰው አካል ረቂቅ ከሆነው ጋር በመዋሀዱ የረቂቅነትን፣ የስፉህነትን ነገር ገንዘቡ አደረገ። ስለዚህ አምላክ ሰው ሆነ ሰው አምላክ ሆነ እንላለን። በተዓቅቦ (በመጠባበቅ) አንዱ የአንዱን አካል ያዘ ማለት ነው። ስለዚህም በእግዚአብሔር መልክና አርአያ አየነው። ማረጋገጫ ጥቅሶችን እንመልከት። ፊል 2÷6 “… እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም ነገር ግን የባርያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ” ይለናል። ይህ የአካል ተዋህዶን ያሳየናል። እኔን ያየ አብን አየ ሲል ዮሐ. 10÷30 ተዋህዶን ምሥጢረ ሥላሴን አንድነቱን ያሳየናል።

በባህርይው ተዋህደ ማለት ደግሞ የሰው ባህርይ የሚጠማ፣ የሚራብ፣ የሚታመም፣ የሚነሳቀል ወዘተ ነው። የአምላክ ባህርይ



ግን አይጠማም፣ አይነሳቀልም፣ አይራብም፣ አይታመምም ወዘተ በባህርይ የለም። ስለዚህ የማይታመመው ታመመ፣ የማይጠማው ተጠማ፣ የማይነሳቀለው ተነሳቀለ፣ የሥጋ ባህርይን ገንዘቡ አደረገ፣ ሥጋም የአምላክን ባሕርይ ገንዘቡ አደረገ። ለምሳሌ ያለምንም ምግብና ውሃ ለአንድ ሰው ለ40 ቀን መቆየት አይቻለውም ነገር ግን ሥጋ ገንዘቡ ባደረገው የአምላክ ባህርይ 40 ቀን ቆየ ማቴ. 4÷1፣ አምላክ የመጠማት ባሕርይ የለውም ነገር ግን ገንዘቡ ባደረገው የሥጋ ባህርይ ተጠማሁ አለ። የኛን የነፍስ ጥማት ለመቁረጥ ማቴ. 27÷48 ስለዚህ ካቶሊኮች በመሠረቱ ያመኑት መ/ቅዱስ እንደሚያሳየን ስህተት ነው። የጠቀሱትም ጥቅስ ሁለት ባህርይን የሚያሳይ አይደለም። የጥቅሶቹ ትርጉምና ፍቺ ግን የማቴ. 27÷46 የአዳም ጩኸት ሲሆን የእርሱን ሀዘን አዝኖና የሱን ጉስቁልና ተነሳቁሎ የእኛ እዳ በደል ተሸክሞ ሊያስወግድ ስለተገለጸ አምላኬ ለምን ተውከኝ አለ። ይኸን ጩኸት ዳዊት መዝሙረኛው (መዝ. 21÷1) ተናግሮታል። በጭንቀታችን በሀዘናችን ጊዜ ወደ እርሱ እንድንጮህ ሲያስተምረን ነው። አንድም ቃሉ ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ ነው።

- ማቴ 26÷39 ያለው “አባት ሆይ ቢቻልህ ይህች ጽዋ ትለፍ እንደ አንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ እንደ እኔ አይሁን” ያለው እሱ ሥልጣን ሣይኖረው ቀርቶ ሳይሆን እኛ ሁልጊዜ የሱን ፈቃድ እየጠየቅን እንድንኖር ለማመልከት፣ ሁለተኛ የለበሰው ሥጋ መዋቲ ነው ፍጹም ሰው ሆኖ መታየቱን ለማረጋገጥ ሦስተኛ የአዳም ሥርየተ ኃጢአት በዚህ ሞት የሚፈጸም ስለሆነ የአዳም ጭንቀት ምን ያህል ከባድ እንደነበረ ለማጠየቅ ነው።

2ኛ) ካቶሊኮች መንፈስ ቅዱስ ከአብም ከወልድም ሠረፀ ይላሉ፤ ይህን ትምህርቷን የጀመረችው በ1014 ዓ.ም. በፓፓ ቤኔዲክቶስ ዘመን ነበር። ለዚህ አባባሏ ከቅዱስ መጽሐፍ ያገኘችው አስረጅ የለም። የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያንና የግሪክ ቤተክርስቲያን ከጉባኤ ኬልቄዶን በኋላ 602 ዓ መቃት አብረው ከኖሩ በኋላ በ1054 ዓ.ም. ተወጋግዘው የተለያዩት በዚህ የካቶሊክ ትምህርት ነው።

✞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ሠረፀ እንላለን ይኸውም መጽሐፍ ቅዱስ በዮሐ 15፥25 "መንፈስ ቅዱስን እልክላችኋለሁ። እርሱም ከአብ የሚወጣ ነው" ሲል ያረጋግጥልናል። ከአብ ሠረፀ የምንለው ለዚህ ነው እንዲሁ ዮሐ. 14፥25 "አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ... " በማለት ከአብ የሠረፀ መሆኑን ያረጋግጥልናል። ስለዚህም በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርታችን መሠረት አብ ወልድን ይወልደዋል፣ መንፈስ ቅዱስን ያሰርፀዋል። በማለት አባቶቻችን ያስተማሩን ይህንኑ ነው ይህ ማለት ግን አብ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ይበልጣል ማለት አይደለም። በእሪና እኩል ናቸው እንጂ።

3ኛ) ካቶሊኮች ድንግል ማርያምን ያከበሩ መስሏቸው የሰው ወገን፣ የአዳም ዘር ሳትሆን ከጠፈር የተገኘች ኃይለ አርያማዊት ከጠፈር የተገኘች ሰማያዊት ናት ይሏታል።

✞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ግን ድንግል ማርያም የሰው ዘር የሆነች ኢያቄም የሚባል አባት፣ ሃና የምትባል እናት ያላት እንደ ሰው ተወልዳ ያደገች፣ እግዚአብሔር አስቀድሞ የጠበቃት፣ የአዳም የውርስ ኃጢአት ያላገኛት፣ ከጥንተ አብሶ ኃጢአት የጸዳች፣ ንጽሕይት፣ ክብርት፣ ድንግል፣ የድኅነታችን ምክንያት ናት። መንፈስ ቅዱስ የጸለለባት ጸጋ የተሞላች ነች። ከሰው ዘር መሆኗ እንዲታወቅም ዮሴፍ እጮኛህ ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ ተብሎአል። በሉቃ. 1፥36 "እነሆ ዘመድሽ ኤልሳቤጥ" የሚለው የመልዐኩ የገብርኤል ንግግር ለዮሴፍ መቃጨቷን እንመለከታለን፣ ለዮሴፍ የታጨችው ንጹህ ሆኖ እንዲጠብቃት ነው። ነገር ግን ሰማያዊ ብትሆን ኖሮ ጠባቂ አያስፈልጋትም ነበር። ማቴ. 1፥1 የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሀረግ ስንመለከተው ብዙ ነገር ያረጋግጥልናል። ድንግል ማርያም የቆየችው 64 ዓመት ነው። በ64 ዓመቷ በዮሐንስ ወንጌላዊ ቤት ሣለች አርፋለች፣ በጌቴ ሴማኒ ተቀብራለች። በተቀበረችም በ3ኛው ቀኗ እንደ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ አርጋለች። የእመቤታችን መነሳት ለሚጠራጠሩ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን እንዲያስተውሉ እንነግራቸዋለን። ዘፍ. 5፥24 "ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም እግዚአብሔር ወስዶታልና" ይላል። እንግዲያው ሄኖክ በእግዚአብሔር ከተወሰደ፤ ድንግል ንጽሕይት ወላዲተ አምላክማ ወደ ልጇ ማረጓ ምን ያስገርማል። በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን (ዘፍ- 18፥14፤ ሉቃ. 1፥37) ይህ ብቻ ይደለም የኤልያስ ማረግ ማረጋገጫ ይሆናል። ጌታ በወንጌሉ እንዳረጋገጠልን። በማቴ. 16፥28 እንዲህ ይላል "እውነት እላችኋለሁ የሰው ልጅ በመንግሥቱ ሲመጣ እስኪያዩ ድረስ እዚህ

ከሚቆሙት ሞትን የማይቀምሱ አንዳንድ አሉ" ይለናል። ከዚህ በላይ ምን ማረጋገጫ ይኖራል።

4ኛ) ካቶሊኮች ፓፓቸውን "የክርስቶስ እንደራሴ የጴጥሮስ ወራሽ" ነው አይማማትም የተናገረው እግዚአብሔር የተናገረው ነው። በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ላይ የበላይ ልህቅና አለው ይላሉ። እንዲሁም የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ዓለም አቀፋዊ ቤተክርስቲያን ናት ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ንዐ ማን (ታናሾች) ናቸው ትላለች። እንዲሁም የክርስቲያኖች ማዕከል መዲና (The center of Christianity) ኢየሩሳሌም ሳትሆን ሮማ ቫቲካን ናት ትላለች። ለዚህ ሁሉ አባባሏ የምታቀርበው አብይ ጉዳይ ቢኖር በ64 ዓ.ም. ቅ/ጴጥሮስ በሮም በኔሮን ቄሣር ዘመነ መንግሥት የመሞቱን ጉዳይ ነው። ቅ/ጴጥሮስ በማቴ. 16፥16 እንደተገለጸው በፊሊጶስ ቂሣርያ ያቀረበውን ጥያቄ በመመለሱ "አንተ መሠረት ነህ በአንተ ላይ ክብርት ቤተ ክርስቲያኔን እሠራታለሁ የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻ ቁልፍ እሠጥሃለሁ" የተባለውን በመጥቀስ የመንግሥተ ሰማያት ቁልፍ ለጴጥሮስ ብቻ እንደ ተሰጠና የሐዋርያት ሁሉ አለቃ ጴጥሮስ ነው። በማለት የቅ/ጴጥሮስ መቃብር ሮም ቫቲካን በመሆኑ ይህንን ራስን ከፍ የማድረግ ፍላጎቷን ታረካበታለች።

✞ እኛ ኦርቶዶክሳዊያን የሮማ ፓፓ የበላይ ልህቅና አይሳሳትም የሚለውን አይቀበሉትም ሰው እስከሆነ ድረስ (absolute) ፍጹም የማይሳሳት ትክክለኛ አይደለም ይሳሳታል። የተናገረውም ሁሉ እግዚአብሔር የተናገረው አይደለም



የክርስቲያኖች ማዕከል ክርስቶስ የተወለደባት፣ የተጠመቀባት፣ ያረገባት፣ ስለሰው ልጆች መከራ የተቀበለባት፣ የተገረፈባት፣ የተሰቀለባት፣ የሞተባት፣ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሣባትና ያረገባት ኢየሩሳሌም እንጂ ቫቲካን አይደለችም። ቤተክርስቲያን አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት በአይናቸው አይተው፣ በጆሮአቸው ሰምተው፣ በእጃቸው ዳስሰው፣ ትምህርቱን 3 ዓመት ከ3 ወር ተምረው የመሠከሩላት ናት 1ዮሐ. 1፥1፣ ነገር ግን ቤተክርስቲያን የእገሌ ናት የእገሌ አይደለችም አትባልም። ማቴ. 16፥16 የተጠየቀው ጥያቄ እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ? የሚል ነው። ጥያቄውም መልሱም የ12ቱ ሐዋርያት ነው የብጽዕና ቁልፍም የተሰጠው ለ12ቱ ሐዋርያት ነው። በት/ቤት ደንብ መሠረት መላሹ አንዱ እጁን አውጥቶ ይመልሳልና።

5ኛ ካቶሊኮች የብሉይ ኪዳን አህዛባውያን ስለነበሩ የብሉይ ኪዳን ውርስ ስለሌላቸው ታቦተ ሕጉ ጽላተ ኪዳኑ የላቸውም። ያላቸው "ሜንሳ" (mensa) ነው። "ጠረጴዛ" ማለት ነው ዳሩ ግን እኛን ለመምሰል ሳያምኑበት ታቦት ይዘው ይታያሉ። ተቀባይነት ለማግኘት ሲሉ ነው በቫቲካን ግን ታቦት ክልክል ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማረጋገጫ የላቸውም።

6ኛ ካቶሊኮች የኃጢአት ማስተሠርያ ካርድ የሚባል ለምዕመናቻቸው ይሸጣሉ ይህንን ካርድ የገዛ ከማናቸውም ኃጢአት ነፃ ይሆናል የሚል አመለካከት ነበራቸው። ለዚህ ነው ካቶሊካዊው ቄስ ጀርመናዊው ማርቴን ሉተር በ1517

ዓ.ም. የፕሮቴስታንት እምነት ከካቶሊክ ቤተክርስቲያን ለይቶ ሊመሠርት የቻለው።

✞ ኃጢአት የሚያስተሰርየው በካርድ ሳይሆን ደሙን ያፈሰሰውን ኢየሱስ ክርስቶስ አምኖና አውቆ ወደ ንስሐ በመምጣት ነው።

7ኛ ካቶሊኮች "የእሳት መንጽሔ" (Purgatory) እምነት አላቸው በዚህ ትምህርት መሠረት ቀኖናዋን ሳትጨርስ የተለየች ነፍስ ወደ እሳት መንጽሔ ገብታ ወደ እሳት ከገባች በእሳት ከነፃች በኋላ ወደ ገነት ትገባለች የሚል እምነት አላቸው።

✞ ስለእሳት መንጽሔ ካቶሊኮቹ የተናገሩት አንዳችም መጽሐፋዊ መረጃ የሌለው ከንቱ ፈጠራ ይመስላል መጽሐፍ ቅዱስ "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ" ይለናል ማቴ. 4፥17 ታዲያ ንስሐ እዚሁ እያለን ስንኖር በሥጋ የበደልነው በደል የሠራነው ኃጢአት በነፍስ የምንኮነንበት ስለሆነ ንስሐ እዚሁ ገብተን ከኃጢአት ጸድተን መሄድ እንዳለብን ያስተምረናል። በ2ቆሮ. 6፥2 "የመዳን ቀን አሁን ነው" ይላል። ነገር ግን ንስሐዋን (ቀኖናዋን) ሣትጨርስ የሄደች ነፍስ እንደ እግዚአብሔር ፍርድ የሚገባትን ይሰጣታል እንጂ የእሳት መንጽሔ የሚባል ነገር የላትም። አስቀድሞ ግን ንስሐ ባለመግባት ከሚመጣ ጠንቅ ለማምለጥ ሁሌ የንስሐ ሰው መሆን ይገባል እንጂ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንማረው አንድ **ሰው በተናዘዘ ጊዜ ኃጢአቱን በገለጸ ጊዜ የኃጢአት ሥርየትን እግዚአብሔር ይሰጠዋል። ለምሳሌ በማቴ. 3፥6 በኃጢአታቸው እየተናዘዙ በተጠመቁ ጊዜ ምህረትን አግኝተዋል። ይህንንም መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ ከሚመጣው**



ቁጣ እንድትድኑ ማን አመለከታችሁ በማለት ከቁጣው በነፍስ ካለ ከስኅና ወቀሳ ማምለጣቸውን ተናግሯል። እንዲሁ በማቴ. 8፥1-3 ለምፃሙ ልታነፃኝ ትወዳለህን ባለው ጊዜ እዎን እወዳለሁ ንጻ ብሎታል። ከዚህ በኋላ ከእነፃው ከአጠራው በኋላ "ሙሴ ያዘዘውን መባ ሂደህ አቅርብ ራስህን ለካህን አሳይ" አለው። ስለዚህም ዋናውና ትልቁ ነገር በፍጹም ልብ መዳንን መንጻትን ከኃጢአት ጠርቶ መገኘትን ፈልጎ ሲመጣና ሲለምን እግዚአብሔር ያጠራዋል ያነፃዋል ይቅር ይለዋል ቀኖናዋ ያቺ ነፍስ ባታልቅም በእውነት ንስሀ አልገባችም አትባልም የኃጢአት ለምጹ ተወግዶላታልና። በቀኙ የተሰቀለው ወንበዴም ይህ ዕድል ነበር የተሰጠው ሉቃ.23፥42-43 ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም የሚናዘዘባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል ምሳ. 28፥13።

ካቶሊኮች ረቡዕና አርብ አይጾሙም የሚጾሙት ቅዳሜ ነው የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ከዚህ እምነቷ መሠረት በ1626 ዓ .ም. በአፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት የካቶሊክ ሃይማኖት ብሔራዊ ሃይማኖት ተብሎ ታውጆ ነበር። ይህን ትምህርት የካቶሊክ ቤተክርስቲያን መርቅያን ከተባለ የሶርያ ግኖስቲክ የወሰደችው ሣይሆን አይቀርም ኢትዮጵያውያን በዚህ እምነት በቅኔ እንዲሁ ሲሉ ገልፀውታል

ለሰንበትሂ ንጹሙማ ከመዘረቡዕ ዕለት
መርቅያን በአመኣ ወአነ በንዴት

የቅኔውም ትርጉም ሰንበትን (ቅዳሜን) እኔና መርቅያን እንደ ረቡዕ ዕለት እንያማታለን እኔ ግን በችግር ነው (ያን ቀን የሚበላ አጥቶ ረሀብ ውሏልና) መርቅያ ግን በክህደት ነው ሲል ገልጾታል።

✞ በኢ/ተ/ቤ/ክርስቲያን ረዕቡና ዓርብ የጾም ቀናት ናቸው። ቅዳሜና እሁድ ሰንበታት ናቸው።

ረቡዕ፡- የምንጾመው የአይሁድ መንፈሳዊ ሸንጎ ሲካሄድ ጌታን አርብ ለመስቀል የመጨረሻ ውሣኔ ያስተላለፉበት ዕለት ስለሆነ መድኀኔዓለም ለሰው ልጆች ሲል የተፈረደበትን ዕለት በጾም በማስተዋል እንጾማለን። እኛንም ከፍርድ ከክፉ ሥራ ሁሉ አውጣን ብለን እንጾማለን።

ዓርብ፡- ጌታ ለሰው ልጆች ሲል የተሰቀለበት ዕለት ስለሆነ በጾም ይከበራል ረቡዕና ዓርብ ያመ ድኅነት ይባላል።

ቅዳሜ፡- የምናከብርበት እግዚአብሔር ስድስት ቀን ሠርቶ በሰባተኛው ቀን ቅዳሜ ስላረፈ የእግዚአብሔር ቀን ተብላ በኦሪት የከበረች ስለሆነች።

እሁድ፡- የጌታ ቀን ተብላ በአዲስ ኪዳን የከበረች ስለሆነች ራእይ 1፥10 ጌታ የተወለደባት፣ የተነሣባት፣ ለሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን የላከባት፣ ታላቅ ዕለት ስለሆነች ሰንበት ናት ብለን እናከብራለን።



9ኛ የካቶሊኮች ካህናት መነኮሳት ብቻ ናቸው።

✞ የኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን ካህናት በቅዱስ ጋብቻ ያገቡ ቀሳውስትና በድንግልና የመነኮሱ ካህናት አሏት ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምናነበው ራሳቸው ለእግዚአብሔር አገልገሎት በወደዱት መልኩና እግዚአብሔር በፈቀደው መልኩ ለይተዋል። ለምሳሌ አብርሃም ባለ ሚስት ነበር። ሚስት አግብተሃልና ለኔ አገልጋይ አትሆንም አላለውም ከዘመዶችህ ተለይተህ ውጣ አለው እንጂ ዘፍ 12፥1-5 እንዲሁም በትዕግስቱ የሚታወቀው ኢዮብ እንዲሁ ባለሚስት ነበር ኢዮ. 2፥15-25 ሌላው በድንግልና አገልግለውት የሄዱ ደግሞ አሉ እንደነኤልያስ ያሉ አባቶች በድንግልና አገልግለው አርገዋል። ከሐዋርያትም መካከል ያገቡም ነበሩ። ለምሳሌ ጴጥሮስ አግብቶ የነበረ ሰው ነው። ጌታ የጴጥሮስ አማት ታማ ሊፈውሳት እንደሄደ ይነግረናል። ማቴ 8፥14 ጌታም በድንግልና ስላለ አገልግሎት ሲናገር በማቴ. 19፥11 “ይህ ነገር ለተሰጣቸው ነው እንጂ ለሁሉ አይደለም በእናት ማህፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ፤ ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ፤ ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ። ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው አላቸው።”

ስለዚህ በግድ መነኩሴ ካልሆነ በስተቀር በክህነት ማገልገል አይችልም የሚል ትምህርት በመጽሐፈ ቅዱስ ውስጥም ሆነ በትውፊት አንዳች ነገር አናገኝም።

10ኛ ካቶሊኮች የሚመሩበት ባሕረ ሃሳብ የጎርጎርዮስ 7ኛ ነው። አዲስ ዓመት ከልደት በኋላ እንዲሆን ብሎ በጥር እንዲሆን የወሰነው ጎርጎርዮስ 7ኛው (1075-1083 ዓ.ም.)

✞ የኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን አዲስ ዓመት የምንለውጠው ከመስከረም ነው ይኸውም እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ነፃ ከወጡባት ከመጋቢ ወር ጀምሮ 7 ወር ቆጥረው በመስከረም እንዲለውጡ በአዘዘው መሠረት ነው። ሌላው ከምሥጢረ ሥጋዌ መፈፀም ጀምሮ ነው። ምክንያቱም አንድ ጽንስ ሙሉ ሰው የሚባለው 6 ወር በማህፀን ከቆየ በኋላ ስለዚህም መልዐኩ ቅ/ገብርኤል ድንግል ማርያም እመቤታችንን ካበሰረበት ከመጋቢት 29 ጀምሮ ስንቆጥር መስከረም ወር ስድስት ወር ይሆናል። ስለዚህም አምላክ ሰው ሆነ ሰው አምላክ ሆነ የሚለው ምሥጢር በእውነት ዛሬ ተፈፀመ የምህረት ዓመት ካሁን በኋላ ሆነ በማለት እንለውጣለን።

11ኛ ካቶሊኮች አዳም በጥንተ አብሶ ባሕሪው ጎሰቆለ እንጂ ጸጋው አልተነካም ይላሉ።

✞ ኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን አዳም በጥንተ አብሶ ባሕሪው ጎሰቆለ ጸጋው ተገፈፈ ትላለች። እንደ ካቶሊኮች አባባል ከሆነ ግን የኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣት የአዳምን ባሕርዩን ለማደስ እንጂ ጸጋውን ለመመለስ አይደለም ያሰኛል። እንዲሁም አዳምና ሔዋን ዕርቃናቸውን መሆናቸውን ጸጋው ስለተገፈፈ ነው "በጸጋው አዳነን" ያሰኘው እኮ ጸጋችን ተገፎ ስለነበረ ነው። ስለዚህ ያለምንም ነገር ጸጋውን አደለን ብለን እናምናለን። እኛም በጸጋው ልጆቹ እንሆን ዘንድ



በጥምቀት ልጆቹ አድርጎ ሥልጣኑን ሰጠን በጸጋው አዳነን ስንል ግን እንደ ፕሮቴስታንቶች አገላለጽ አይደለም። በቸርነቱ ይቅር አለን ከጥንተ አብሶ ኃጢአት አነፃን ስንል እንጂ በሞቱ ሕይወት ሆኖልናልና። ዮሐ. 1÷12-13፤ ሮሜ 3÷24

12ኛ ካቶሊኮች ለምዕመኖቻቸው ሥጋውን ደሙን አያቀብሉም። የሚያቀብሉት ሥጋውን ነው። ይኸውም ሥጋው ደም አለው የሚል ፍልስፍናዊ አመለካከት ስላላቸው ነው።

✞ ኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን ሥጋውን ደሙን ለምዕመኖቿ ታቀብላለች። ይኸውም ጌታ በምሴተ ሐሙስ "እንካችሁ ይህ ሥጋዬ ነው፤ እንካችሁ ይኸ ደሜ ነው" ብሎ ሥጋውን በተለየ ደሙን በተለየ ሰጥቷል። ማቴ. 26÷26። ስለዚህ እኛ ተዋህዶን የምናምን ልክ እንደ ጌታ ቀድሞ ካህኑ ሥጋውን ያቀብላል ዲያቆኑ ደግሞ ደሙን ያቀብላል። የምንቀበለው ሥጋና ደም አማናዊ እውነተኛ የጌታ ሥጋና ደም ነውና ይኸውም ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሀደው ነው። ጌታም በተለይ መቀበል እንዳለብን ሲያስረዳ "ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜ እውነተኛ መጠጥ ነውና" ዮሐ. 6÷55 ይለናል። የጌታን እውነተኛ ምብል የሆነው ሥጋውና እውነተኛ መጠጥ የሆነው ደሙ የዘለዓለም ሕይወት የሚያሰጥ ነው። ሥጋውን ካልበላን ደሙን በተለየ ካልጠጣን ሕይወት የለንምና።" ዮሐ. 6÷54

13. ካቶሊኮች የሚቆርቡት ከበሉ ከጠጡ በኋላ ነው።

✞ ኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን ግን ከመቁረባችን በፊት ከ15-18 ሰዓት ድረስ እንፆማለን። ሆዳችንን ባዶ ሲሆንና ለአፋችን ምሬት ሲሰማን እንድንቆርብ የቤተክርስቲያናችን ሥርዐት ያዘናል። "ያለ ሥርዐት የሚሄዱ ገስጹአቸው" ይለናል 1ኛ ተሰ. 5፥14። እንዲሁ አምልኮት አገልግሎት ማንኛውም ነገር ሁሉ በአግባቡና በሥርዐቱ እንዲሆን መጽሐፍ ቅዱስ ያዘናል 1ቆሮ. 14፥40።

## በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክርስቲያንና በኦርቶዶክስ መለካውያን መካከል ያለው ልዩነት

| ኦርቶዶክስ ተዋህዶ | ኦርቶዶክስ መለካውያን |
|---|---|
| 1. ግብጽ | 1. ግሪክ |
| 2. ኢትዮጵያ | 2. ሩሲያ |
| 3. ሶርያ | 3. ቡልጋሪያ |
| 4. አርመን | 4. ሩማኒያ |
| 5. ሕንድ | 5. ዩጎዝላቪያ' ወዘተ ናቸው። |
| ኦሪየንታል አብያተ ክርስቲያናት ይባላሉ | ኢስተርናል አብያተ ክርስቲያናት ይባላሉ |

1ኛ ኦርቶዶክስ መለካውያን ክርስቶስ አንድ አካል ሁለት ባህርይ ነው ስለሚሉ ሁለት ባሕርይ ባዮች ናቸው።

2ኛ ኦርቶዶክስ መለካውያን ታቦት የላቸውም፤ ነገር ግን ያላቸው የጌታ የግንዘቱ ወይም የስቅለቱ ስዕል ያለበት ነዌ የሀር መጎናፀፊያ ነው። ይህንንም "እንደምኤሲዮን" ይሉታል።



"ህየንተ ታቦት" በታቦት ፈንታ ማለት ነው። በእነዚህ አንዳንድ ሥርዐቶች እንለያያለን።

## በኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያንና በፕሮቴስታንቶች መካከል ያለው ልዩነት

ፕሮቴስታንቶች (ጴንጤዎች) ብዙ ዓይነት መመሪያ አላቸው እምነቱ ሲመሰረት መነሻ መርሆዎች፡-

1. ገዳማት ምንኩስና አያስፈልግም
2. በቅዱሳን አማላጅነት መለመን አስፈላጊ አይደለም።
3. እምነት በመ/ቅዱስ እንጂ ሌላ መጻሕፍት አያስፈልግም።
4. እምነት እንጂ ምግባር ለመዳን አያስፈልግል የሚሉና ሌሎችም።

መጽሐፍ ቅዱስን ሁሉም በገባው መልኩ መተርጎም ይችላል። የሚል ትምህርት የነበራቸው በመሆኑ በዚህ ነጥብ መነሻነት በክርስትና ውስጥ ያልነበረ አዲስ ትምህርት በ16ኛ ክ/ዘመን ጀምሮ ማሰራጨት ያዙ። ከ16ኛ መቶ ክ/ዘመን በፊት ክርስቶስ እንደማይታወቅ አድርጎ እንደ አዲስ ነገር "እንደ ግል አዳኝህ አድርገህ ተቀበለው" ማለት ተጀመረ። በተለይ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን ሁሉም በገባው መልኩ እንዲተረጉም እምነቱ ስለፈቀደ እጅግ ለመቁጠር የሚታክት ክፍፍል በፕሮቴስታንት ውስጥ ተከሰተ። ይኸም በተለይ እጅግ እየበዛ መከሰት የጀመረው በቅኝ አገዛዝ አስፋፋት ወቅት ነበር።



www.ethiopianorthodox.org

የፕሮቴስታንት ሃሳባቸው መብዛትና እንዲህ ያለው መለየት መፈጠር መነሻው ብዙ ምክንያቶች ናቸው በተለይ ደግሞ በእምነት ስም ለተቋቋሙ ድርጅቶች በሙሉ የሚሰጠው መብት አንዱ ነው። ከእነዚህም መካከል፡-

1. የቀረጥ ያለመክፈል ነፃነት
2. ቦታን ያለምንም ግብር የመጠቀም ነፃነቶች

የተወሰኑት ምክንያቶች ናቸው። ይህ በአሁኑ ሰዓት በከፍተኛ ደረጃ ቁጥሩ እየበዛ ለመጣው የፕሮቴስታንት ሃይማኖት በብዛት በአሜሪካና በተወሰኑ አውሮፓ ክፍሎች እየተሰራበት ስለሆነ ዛሬ ለምናየው ቁጥሩ የበዛ እምነት ድርጅት ወሳኝ ሚና ያላቸው አህጉሮች ናቸው።

## <u>የፕሮቴስታንት ሃይማኖት</u>

1ኛ ፕሮቴስታንቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ከአበው ሐዋርያት ጀምሮ በተነሱ በቤ/ክርስቲያን ሊቃውን መጻሕፍትና ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው በክርስቲያናዊ ትውፊቶች አያምኑም አይቀበሉም። የሚቀበሉትም የመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥር 66 ሲሆን ይኸውም ከብሉይ 39 ከሐዲስ 27 ነው።

✞ የኦርቶዶክስ ተ/ቤ/ክርስቲያን የእምነት መሠረቷ መጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን ከዚህም ጋር በቤተክርስቲያን ሊቃውንት መጻሕፍት በክርስቲያናዊ ትውፊቶች ላይ የተመሠረተ ነው። የምንቀበለው መጻሕፍት ቁጥር 81 ሲሆን ይኸውም ከብሉይ ኪዳን 46 ከሐዲስ ኪዳን 35 ነው። በርግጥ የቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር በዚህ የሚገደብ አይደለም ለምሳሌ ያህል



66ቱ መጽሐፍት የማያሟላቸው ወይም ያልያዟቸው መጻሕፍት አሉ። እስኪ እነዚህ ከማረጋገጫ ጋር ተራ በተራ እንመልከታቸው። በመጀመሪያ ዘፍ.4፥17 ላይ እንደምን መለከተው "... ቃየል ሚስቱን አወቃት ፀነሰችም" ይላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተፃፈልን ስለ አቤልና ቃየል መወለድ እንጂ ሌላ የሰው ዘር እንዳለ አንዳች ነገር እናነብም ነገር ግን የቃየል ሚስት ከየት መጣች የሚለውን ጥያቄ በ66ቱ መጽሐፍ ውስጥ የምናገኘው መልስ የለም ነገር ግን 81 መጽሐፍ ላይ በመጽሐፈ ኩፋሌ ከምዕራፍ አንድ ጀምሮ እስከ አስር የሰውን ልጅ የመፈጠርና የመብዛት ሁኔታ ሲያብራራ ስለ ሴቲቱ ማንነት ገልጾታል።

2ኛ በሉቃ. 3፥23 "ኢየሱስም ሊያስተምር ሲጀምር ዕድሜው ሠላሳ አመት ሆኖት ነበር ይላል ኢየሱስ ከሰላሳ አመቱ በፊት የት ነበር? ምን ያደርግ ነበር? ምን ይሠራ ነበር? ለሚለው ጥያቄ 66ቱ መጽሐፍት አንዳች የሚሰጠን ነገር የለውም ነገር ግን በትውፊታዊ መጻሕፍቶች ስለ ዕድገቱ ሁኔታ በእያንዳንዱ ተዘርዝሮ ተጽፎአል። ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ዮሐ. 20፥30 "ኢየሱስ በዚህ መጽሐፍ ያልተፃፈ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ ይላል ቃዲያ ከዚህ መጽሐፍ ውጪ የተፃፈበት ቦታ እንዳለ ያመለክተናል።" እንዲሁ በዮሐ. 21፥23 "... ሁሉ በእያንዳንዱ ቢጻፍ ዓለም ለመጻሕፍቱ ማስቀመጫ ባልበቃች ይመስለኛል" ይላል። እንግዲህ ዓለም ሊበቃው የማይችለውን እውነት ከዚህ ከ66ቱ መጽሐፍ ውጭ የለም ማለት እግዚአብሔር ሥራ አልሠራም ማለት ነው ያሰኛል ይህ ደግሞ በራሱ ክህደት ነው።

3ኛ ይሁ. 1፥14-15 ሄኖክ ስለ ጌታ ትንቢት እንደተናገረ ጽፎአል። ነገር ግን የሄኖክን መጽሐፍ በ66ቱ ውስጥ አናገኝም ነገር ግን በሰማኒያ አሐዱ (81) መጻሕፍት ግን እናገኘዋለን። ታዲያ ሄኖክ የተናገረው ትንቢት በ66ቱ ከሌለ የለም ይህን መጽሐፍ አንቀበልም ቢሉ ከራሳቸው ጋር ይጣላሉ የተነገረው እውነት ነውና ያለውን ማመን ይገባል።

በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ የቅዱሳት መጻሕፍት መጠን ይህ ነው። ከዚህ ውጭ የለም አላለንም እንዲያውም የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ እንደሚጠቅመን ሲናገር እንዲህ ይላል። "የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል" 2ጢሞ. 3፥16 ከዚህ በላይ ማረጋገጫ ምን ያስፈልጋል።

## ፕሮቴስታንቶች በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የሚያነሱት ጥያቄ

ፕሮቴስታንቶች (ጴንጤዎች) በተለይ በራዕ. 22፥18-19 በዚህ የትንቢት መጽሐፍ የጨመረ የቀነሰ ማንም ቢኖር በዚህ መጽሐፍ ያሉት መርገሞች ይደርሱበታል ይላልና ሌላ መጽሐፍ የለም ይላሉ። ይህ ቃል ግን ራእይ ዮሐንስን የሚወክል እንጂ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን አይደለም። ምክንያቱም መጻሕፍቶቹ በሙሉ የተፃፉት በተለያየ ቦታ ነበር በአንድ ላይ አሰባስበው በአሁኑ መልክ ያደረጉት 318ቱ ሊቃውንት ናቸው። እነዚህ በየቦታው ከተጻፉት አንዱ ደግሞ ራእይ ዮሐንስ ነው። ይህም በፍጥሞ ደሴት ላይ ነበር።



እነዚሁ ሊቃውንት ያሰባሰቧቸውን መጻሕፍት በአንድ ሲያደርጓቸው ራእይ በአፃፃፉ ከ95 ዓ.ም. እስከ 100 ዓ.ም. ባለው ጊዜ በመጻፉ በመጨረሻ ላይ አደረጉት። ምክንያቱም ሌሎቹ ከዚህ በፊት ቀድመው የተጻፉ ስለነበሩ። ያለው እውነት ይህ ነው። ቃሉንም ብናይ በዚህ ትንቢት መጽሐፍ አለ እንጂ በወንጌል በመልዕክታት አላለም። ወንጌል ትንቢት አይደለም። ማለት የተፈፀመ ነው በብዙ የተገለጸበት። ታዲያ እውነቱ ይህ ከሆነ እንዴት ሁሉን ሊወክል ይችላል። ይህማ ባይሆን ኖሮ በዚህ መጽሐፍ ያልተፃፈ ሌላ አለ ባላልን ነበር ዮሐ. 20፥31፤ 21፥25 ስለዚህም ሌሎቹ መጻሕፍት ከጌታ ጋር የሚያጣሉ አይደሉም ጳውሎስ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ብሎ የተናገረው ለዚህ ነው። 2ጢሞ. 3፥16።

ነገር ግን የዮሐንስን አባባል ለየቱ እንደተገለጸ ካልተረዳነው ዮሐንስ ለወንጌሉም ለራዕዩም ጸሐፊው እሱ በመሆኑ በአንድ አፍ ሁለት ምላስ ሆኖአል። ማለት ነው። ምክንያቱም እዚህ ወንጌሉ ላይ ሌላ ያልተጻፈ አለ ብሎ እንደገና ደግሞ ራዕዩ ላይ የለም ካለ በጣም ይቃረናል። ስለዚህ አሁን ማንን ልንወቅስ ልንኮንን ነው። ዮሐንስን እንዳንል በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርቶ እንደጻፈው ገልጾአል። ራእይ 1፥9 ታዲያ እኛ ወይስ ፕሮቴስታንቶቹ የተሳሳትነው? ነገር ግን እኛ አይደለም። እነርሱ ግን ባለማስተዋላቸው ብዙ ስተዋልና በደንብ አነፃጽረው እንዲያጤኑት እንጠይቃለን። ማስተዋል ከኃጢአት መራቅ ነውና እግዚአብሔርን መፍራት ጥበብ ነው። ኢዮ 28፥28።

2ኛ) በፕሮቴስታንቶች አንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ እንደፈለገው መተርጎም ይችላል ለዚህም ነው ዛሬ እጅግ



www.ethiopianorthodox.org

ተከፋፍለውና ተበራክተው የምናገኛቸው በተለይ በአሜሪካ ብቻ የየግል ሃይማኖታቸውን ይዘው የሚገኙ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ቁጥር እጅግ ብዙ ሆኖ የምናገኘው።

✞ በኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን ማንም እንደፈለገው ሊተረጉም አልተፈቀደም ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ "ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ" 2ጴጥ. 1፥21 ይለናል። መጻሕፍትን እንደፈለጉ እንደ ራስ ሀሳብ መተርጎምን መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ይቃወማል። በእምነት አባቶቻችንን እንድንመስል መጽሐፍ ያስተምረናልና። ዕብ. 13፥7

3ኛ) ምንም እንኳ ስልጣነ ክህነት ከጌታ ለሐዋርያት የተሰጠ ቢሆንም ከሐዋርያት ጊዜ ጀምሮ ሲያያዝ የመጣ መሆኑን በመቃወም እንደሚስጢር ባይቆጥሩትም ከሦስቱ ማዕረግ ክህነት፣ ዲቁናንና ቅስናን ይቀበላሉ። ስለዚህ እያንዳንዱ ክርስቲያን ግብረ ገብነቱን የተመረከዘ መልካም ኑሮና በቂ የመንፈሣዊ ትምህርት እውቀት ካለው የክህነት ሥራ ሊሰራ ይችላል ይላሉ። በፕሮቴስታንት ዘንድ ስልጣነ ክህነት የመንፈስ ቅዱስ ስልጣን ሳይሆን እንደ ቀበሌ ሹንጎ ያለ ነው። ይኸውም በድምጽ ብልጫ አገሌ ለዚህ ዓመት ቄስ ሆኖ ሲያገለግል ቆይቶ ከዚያ ሌላ በድምጽ ብልጫ ይሾማል።



ከፕሮቴስታንት የእንግሊዝ ቤተክርስቲያን ብቻ ሦስቱን ማዕረግ ክህነት እንደ ምስጢር ቆጥራ ትቀበላለች። በፕሮቴስታንቶች ዘንድ ሴቶች ስልጣነ ክህነት ሊኖራቸው ይችላል።

✞ በኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን ስልጣነ ክህነት ከሡባቱ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን አምስተኛው ምሥጢር ሲሆን የመንፈስ ቅዱስ ሲመት ነው። ይኸውም ዮሐ. 20፥21 "... ይኸንንም ብሎ እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋልና የያዛችሁባቸውም ተይዞባቸዋል" አላቸው ይህ ቃላቅ የሥልጣነ ክህነትን ምስጢር የያዘ ነው። ሁሉም ካህን መሆን አይችልም ይህ ሆኖ ቢሆን ኖር ሐዋርያትን ለይቶ በማቴ.10፥1 ላይ ባልመረጠ ነበር። እንዲሁም ሐዋርያት ይህንን አብነት አድርገው በሐዋ.6፥5 ሰባት ዲያቆናትን መምረጥ ባላስፈለጋቸው ነበር። ሁሉንም ካህናት ናችሁ ብሎ ለይቶ አገልጋዮችን ባልመረጠ ነበር።

ፕሮቴስታንቶች ሁላችንን ካህናት አድርጎ ሾሞናል ይላሉ እርግጥ እያንዳንዳችን በአምላካችን ስም በትእምርተ መስቀል አምሳያ አማትበን አጋንንትን ማሳደድ እንዳይቀርቡን ማድረግ እንችላለን። ነገር ግን ሁላችን የክህነትን አገልግሎት እንፈጽማለን ማለት በራሱ ትዕቢት ነው። አምላክ እንደ ፈቀደ አገልግሎትን እሱ በመረጣቸው ይፈጽማልና።

ሴቶች ሥልጣነ ክህነት ሊኖራቸው አይችልም። ምክንያቱም ጌታ በማቴ. 10፥1 ጌታ ሥልጣነ ክህነት ሲሰጥ የወንዶችን ስም እንጂ የሴት ስም አልጠቀሰም ደግሞም ካህን የክርስቶስ ስዕል ነው። ወንድ እንጂ ሴት የክርስቶስ ስዕል አትሆንም። በዮሐ. 20፥17 "አትንኪኝ" የሚል ገጸ ንባብ እናገኛለን ይህም የጌታን ሥጋና ደም የመፈተት ሥልጣን የተሰጣቸው ወንዶች እንጂ ሴቶች እንዳልሆኑ ያመለክተናል። በተጨማሪ 1ጢሞ 2፥11-15 ተመልከት።

4ኛ) <u>ጥምቀት፡-</u> ጥምቀት በፕሮቴስታንት ዘንድ አንድ ሰው በእግዚአብሔር ለማመኑ ምልክት (symbol) ነው ማለትም ሰውየው የዳነው በጥምቀቱ ሳይሆን በማመኑ ነው ለማመኑ ምልክት ይሆነው ዘንድ ተጠመቀ ይላሉ አንዳንዶቹ ጭራሽ አያጠምቁም በሕፃንነት የሚደረግ ጥምቀትን ይቃወማሉ ጌታ የተጠመቀው በ30 ዓመቱ ነውና ሰው አድጎ ሃይማኖቱን አውቆ መጠመቅ አለበት ይላሉ።

✞ የኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን ጥምቀት የመጀመሪያው የቤተክርስቲያን በር መግቢያ መሆኑን ትገልጻለች። መጽሐፍ ቅዱስም በዮሐ. 3፥5 "እውነት እውነት እላችኋለሁ ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለዳችሁ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት አትችሉም" ይላል። ስለዚህም ጥምቀት ልጅነት መቀበያ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚያስገባ እንጂ ምልክት አይደለም። የግድ መወለድ ይገባል የጌታ ልጆች ተብለንም እንጠራለን። ብዙ ጊዜ ፕሮቴስታንቶች ለዚህ እንደ ማረጋገጫ የሚሰጡት "ያመነ የተጠመቀ ይድናል



ያላመነ ግን ይፈረድበታል" ይላል። ማር. 16፥16 ስለዚህም ፍርድ የሚያመጣበት አለማመኑ እንጂ አለመጠመቁ አይደለም፤ ማለት የበቂት በዚህ ጥቅስ ነው። ነገር ግን የዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የሚነግረን እምኖ የመጠመቅን ምሥጢር እንጂ ጥምቀት አያስፈልግም ወይም ወሳኝ አይደለም አያሰኝም ይህ ቃል ይበልጡኑ ልንረዳ የሚገባው ወደ አላመኑትና ገና ቃሉ ወዳልደረሳቸው ሐዋርያት ስለሚጓዙ የተሰጣቸው መመሪያ ነው። ዓለም አላመነም ነበርና ለዚህም ነው ከፍ ብለን ከቁጥር 13 ጀምሮ ስናነብ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ያለው ይህም ዓለም ያመነ ስላልነበ ቀድሞ ማመን ስለሚገባው እንጂ ጥምቀትን ዋጋ ቢስ የሚያደርግ አይደለም። ያለ ጥምቀት ልጅነት የለምና።

ሌላው ከዚህ ጥቅስ ጋር በተያያዘ የ40 ቀንና የ80 ቀን ጥምቀት አያስፈልግም ሰው ካወቀና በእድሜው ከበሰለ በኋላ መጠመቅ ይኖርበታል ይላሉ በርግጥ አምላካችን በ30 ዓመቱ ተጠምቋል ይህም ምክንያቶች ነበሩት "ጽድቅን እፈጽም ዘንድ ይገባኛል።" እንዳለ በ30 ዓመቱ የተጠመቀባቸው ምክንያቶች እንደ ቤተክርስቲያናችን ትምህርት።

1. የአዳምን ልጅነት ለመመለስ፣
2. ሊቀ ካህናት ተብሎ ሊሾም የሚችለው በዚህ እድሜ ስለሆነ፣
3. ለመልካም ሥራ ሁሉ ስትነሱ በዚህ ዕድሜ ማስተዋል ታገኛላችሁ ለማለት ነው።

መጠመቅ የግድ ትልቅ መሆንን አይፈልግም። ለምሳሌ ያህል መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተሰጡን ጥቅሶች አሉ። "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁን ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋ ቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" ማቴ. 28፥19 ይላል ቃሉ ተጠምቆ ማመን መኖሩን ያመለክተናል ይህ ደግሞ ላመኑ እንጂ ላላመኑ አይደለም። እንዲሁም በሐዋ 16፥31-34 እንደምናነበው በአንዱ እምነት ቤተሰቦቹ ሁሉ እንደዳኑ ይነግረናል። "... እርሱና ቤተሰቦቹ ተጠመቁ" ይላል። ቤተሰብ ሲባል ከትልቅ አንስቶ እስከ ትንሽ ያሉትን ሕፃናትን በሙሉ የያዘ ነው ስለዚህም ሕፃናት አይጠመቁም የሚያሰኝ አይደለም። ሐዋ 16፥15 ላይ ያለው የሊዲያ ታሪክ ይህንኑ ያሳያል።

## የ40 ቀንና የ80 ቀን ጥምቀት ከየት መጣ

ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን የመጀመሪያው ምሥጢር ሲሆን ጥምቀት "ዳግም ልደት" ነው። ጥምቀቱ የሞትና የትንሣኤ ምልክት ነው። ወደ ማጥመቂያው ውስጥ ሲነከር ወደ መቃብር ከጌታ ጋር መውረድ፤ ወደ ላይ ብቅ ሲል ከክርስቶስ ጋር መነሣቱ ምሳሌ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠንን መረጃ እንመልከት "... ወይም ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር እንደተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን"



ሮሜ 6፥3-4 ይለናል። ይህን እውነት ለመፈጸም ቤተክርስቲያን በመንከር ሕፃናትን ታጠምቃለች።

ለሕፃናት በሚደረግ ጥምቀት መጽሐፍ ቅዱስ አይቃወምም እንደውም ይደግፋል እንጂ። ለዚሁም ማረጋገጫ ጌታችን "ሕፃናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው" ይላል እንደዚህ ሕፃን የእግዚአብሔርን መንግሥት የማይቀበላት አይገባባትም ብሏል (ማቴ. 19-14)። ቃሉ ይህን እውነት ይዘን ስንጓዝ ወደ ብሉይ ኪዳን መለስ ብለን እናስተውለዋለን፡ ይህም በዘሌ 12 ላይ ከቁ. 1-8 ስናነብ ይህንኑ የወንድ ልጅና የሴት ልጅ ወደ እግዚአብሔር ቤት መሄድ የሚገባቸውን ጊዜ እንዲህ በማለት ገልጾታል። "ሴት ብታረግዝ ወንድ ልጅ ብትወልድ ሰባት ቀን ያህል የረከሰች ናት። በስምንተኛው ቀን ከሥጋው ሸለፈት ይገረዝ ከደምዋም እስክትነፃ ሠላሳ ሦስት ቀን ትቀመጥ" ይላል ሰባትና ሰላሳ ሶስትን ስንደምረው አርባ ቀን ይሆናል። ለወንድ ልጅ የሚደረገው ይህ ነው ብሏል። ቀጥሎም "ለሴት ልጅ ደግሞ ሁለት ሳምንት ያህል የረከሰች ናት ከደምዋ እስክትነፃ ድረስ ስድሳ ስድስት ቀን ትቀመጥ" ይላል። ይህን ስንደምረው ሰማኒያ ቀን ይሆናል። ከዚህ በኋላ በመቅደስ ሔዳ መስዋዕት እንዲያቀርቡ ያዛል። እውነት ነው። እውነተኛ መሥዋዕት በመሆን ያዳነን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ ከጥምቀቱ በኋላ ሥጋ ደሙን ይቀበላሉ ይህ ታላቅ የድህነት ምሥጢር በቤተክርስቲያን ይፈጸምላቸዋል።

**ነገር ግን በአጋጣሚ ከ40 ቀን በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ቢያልፍ በሌላ ጊዜ መጠመቅ አይችልም ማለት አይደለም ከዛም**



www.ethiopianorthodox.org

ቀን በፊት ልጁ ችግር ቢደርስበት ከዛ ቀደም ብሎ በሞግዚት ሄዶ መጠመቅ እንደሚችል ፍትሐ ነገሥት ያዛል።

እጅግ ልናስተውለው የሚገባው ደግሞ አምላካችንን ይህንኑ ሥርዐት መፈፀሙን ነው። ሉቃ. 2፥22-24

## የአጠማመቅ ሥርዐታችንና ፍቺው

"የሥጋንም ሰውነት በመግፈፍ በክርስቶስ መገረዝ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ ደግሞ ተገረዛችሁ በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ በጥምቀት ደግሞ ከሙታን ባስነሳው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ" ቆላ. 2፥11-13 ይህን እውነት ይዛ ቤተክርስቲያን በመንከር ታጠምቃለች ወደ ውሃ ውስጥ ሲነከር ከክርስቶስ ጋር የመሞቱ ምሳሌ ነው። ወደ ላይ ሲያወጣው ደግሞ ከክርስቶስ ጋር የመነሣቱ ምሳሌ ነው። ይህም የሥጋን ሰውነት ገፍፎ የእግዚአብሔር ልጅነት ይሰጣል። የመነከሩም ምሥጢር በክርስቶስ የመገረዝ ምልክት ነው።

ከመነከሩ በፊት የሚፈጸመው

- ዲያቆኑ ሕፃኑን ይዞ ፊቱን ወደ ምዕራብ አዙሮ እክህደከ ሰይጣን በማለት ሦስት ጊዜ ይናገራል። ይህም ሰይጣንን እክደዋለሁ ማለት ነው።
- **እንደገና ፊቱን ወደ ምስራቅ ሕፃኑን እንደያዘ ይመልስና አአምን በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ በማለት ሦስት ጊዜ ከተናገረ በኋላ ወደ ማጥመቂያው ያቀርበዋል።**



ይህም በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምናለሁ ማለት ነው።

"በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ" ብሎ እንዳዘዘው ማቴ. 28፥19

## በጥምቀት የምናገኛቸው ነገሮች

1. መዳናችን በጥምቀት የተሟላ ይሆናል። ይህ ማለት በእውነት የእግዚአብሔር ልጆች በመሆን የሞተልንንና ያዳነን አምላካችን በእውነት ለኛ የፈጸመልንን የመዳን ምስጢር ሙሉ በሙሉ ያደርግልናል። ምክንያቱም የሥጋን ሰውነት በመግፈፍ አዲስ ሰው መሆን ሰጥቶናል። ስለዚህም "የሥጋን ሰውነት በመግፈፍ በክርስቶስ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ ደግሞ ተገረዛችሁ በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ በጥምቀትም ደግሞ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር አሰራር በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ" ቆላ. 2፥11

2. በጥምቀት ሁለተኛውን ልደት እናገኛለን። "ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለዳችሁ በቀር መንግሥቴን አትወርሱም" ብሎአልና ዮሐ. 3፥5።

3. በጥምቀት ሕይወታችን ይታደሳል። ይህም የኃጢአት ሰውነትን ትተን በክርስቶስ ኢየሱስ የምናገኘው አዲስ ሕይወት ነው። መጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ ይለናል። "... በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።" ሮሜ 12፥2

4. በጥምቀት የኃጢአት ሥርየት እናገኛለን ሐዋ 2፥30-37

5. በጥምቀት ከሚያምኑ ወገኖች ተቀላቅለናል በግዝረት በብሉይ ኪዳን የአካል ክፍል ተቆርጦ እንደሚጣል እንደሚሞት የታወቀ ነው። ይህም በጥምቀት የሆነውን ፍጹም ሞት ያመለክተናል። ግዝረት ሊጠፋ የሚችል ምልክት እንዳልሆነ እንዲሁ ጥምቀት ፈጽሞ ሊጠፋ አይችልም። በግዝረት ደም እንደሚፈስ ሁሉ የደሙ ዋጋ ስለኛ በጥምቀት በምናገኘው አዲስ ሕይወት ተከፍሏል።

የተገረዘ ሁሉ ከዘሩ እንዲሆን እግዚአብሔር ለአብርሃም እንዳረጋገጠ እንዲሁ የተጠመቀ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን አካል ይሆናል። ዘፍ 17÷7 "እንዲሁም ክርስቶስ አንድ አካል እንደሆነ እናንተም ደግሞ የክርስቶስ አካሎች ናችሁ" ይለናል። 1ቆሮ. 12

ለአብርሃም ጌታ እግዚአብሔር ሲናገረው ከዘሩ ያልተገረዘ ቆላፍ ሁሉ ከወገንህ ተለይታ እንደምትጠፋ ሁሉ እንዲሁ ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ያልተወለደ መንግሥቱን ሊያይ አይችልም። ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር ሕብረት የሚኖረን ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ስንጠመቅ ብቻ ነው ዮሐ. 3÷5። ከእርሱም ጋር ሕብረት የሚኖረን ልጅ በመሆን ስንጠመቅ ብቻ ነው። ዘፍ. 17÷14 ለዚህም በጥምቀቱ ከክርስቶስ ጋር አብሮ መቀበር ነው። ሮሜ 6÷4 ነገር ግን ከእርሱ ጋር በጥምቀት ካልተቀበርን ከእርሱ ጋር አንነግም።

መገረዝ አብርሃም የሚያምነውን አምላክ ለማወቃቸው ከእርሱም ጋር ሕብረት እንዳላቸው ማሳወቂያ ግዴታ እንደነበር



ለኃጢአት ሥርየትና ከማኅበረ ምዕመናን ለመቀላቀል ደግሞ መጠመቅ ግዴታና አስፈላጊ ነው።

6. ጥምቀት ኃጢአትን ያስወግዳል፣ ሕይወት መታደስ ይሰጣል፣ ክርስቶስን ለብሰነዋል ከእርሱም ጋር መሞትና መነሳት ነው።

ጥምቀት ኃጢአትን ያጥባል ያስወግዳል፣ ለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል። ሃናንያ የተመረጠው በጳውሎስ ገና ወደ ክርስትናው ሲገባ ስሙ ሳውል ነበርና እንዲህ አለው "አሁንስ ለምን ትዘገያለህ ተነሥና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ ከኃጢአትህም ታጠብ" አለው ሐዋ. 22÷16 በመጠመቃችን አንዱ ውጤት ከኃጢአት መታጠብ ነው። የጥንተ አብሶ (የአዳም በደል) ሁሉ ይወገዳል። በእርሱም የመዳናችን ምስጢር ይፈጸምበታል። ሳውል የእግዚአብሔር ምርጥ ዕቃ ነበር። ምርጥ የሆነው ጳውሎስ አስደናቂ የሆነውን አገልግሎቱን ይፈጽም የነበረው ከሁሉ በፊት በጥምቀት ባገኘው አዲስ ልደትና በመንፈስ ቅዱስ መታነጽ ነው። የእግዚአብሔር አጠራርና አሠራር የሚያስደንቅ ስለሆነ እግዚአብሔር ለጳውሎስ እንዲህ ብሎ ተናግሮለታል "ጌታም ይህ በአህዛብም በነገሥታትም በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነውና ሂድ ስለ ስሜ ስንት መከራ ሊቀበል እንዲያስፈልገው እኔ **አመለክተዋለሁና አለው።" ሐዋ. 9÷15-16 ይህን ሥርየትና መመረጥም የጌታን ስም መሸከም ያገኘው ጳውሎስ ከኃጢአት ስለ መታጠብና መንጻት በጥምቀት ስላለ በረከት ሁሉ ያስተምር ነበር። 1ቆሮ. 6÷11**

በጥምቀት ኃጢአትን እንደሚያስወግድና የሚያነፃ መሆኑን ሐዋርያትም ምን እናድርግ ብለው ለጠየቋቸው ምዕመናን በግልጽ አስረድተዋቸዋል። ሐዋ. 2፥38

ክርስቶስን እንደለበስነው ሲገልጽም "ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋል" ገላ. 3፥27 በቀደመ በደላችን ምክንያት ጸጋችን በመገፈፉ አጥተነው የነበረውን እግዚአብሔር መምሰል ተላብሰነዋል።

ሌላው ጥምቀት የሚያሳየን ከክርስቶስ ጋር የመሞትና የመነሣትን ምስጢር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ "የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነው።" ይላል ሮሜ 6፥23 ስለኃጢአታችን የሞተውን ኢየሱስ ክርስቶስን በማሰብ ከሞቱ ጋር ሕብረት እንዳለን በጥምቀት እንገልጻለን። የተነሣውንም ትንሣኤ ለኛም እንደሆነ እኛም እንደምንነሣ በጥምቀት እናረጋግጣለን። ሮሜ 6፥4 ጥምቀታችን ከእርሱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ ነውና።

## በጥምቀት ላይ የሚነሱ የፕሮቴስታንት ጥያቄዎች

አብዛኛውን ጊዜ በፕሮቴስታንቶች በኩል በጥምቀት ላይ የሚያነሷቸው ጥያቄዎች ጎላ ብለው የምናገኛቸው ሁለት ናቸው።

1ኛ) ሕጻናት መጠመቅ የለባቸውም

2ኛ) እምነት እንጂ ጥምቀት አያድንም የሚሉ ናቸው።

በመጀመሪያ ደረጃ ሕጻናት መጠመቅ የለባቸውም ብለው ለሚያነሱት ጥያቄ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠን መልስ አለ። በቅድሚያ ግን እንደማረጋገጫ የሚያቀርቧቸውን አባባሎች እንመልከት።



በማር. 16፥16 ላይ ያለውን በመጥቀስ አንድ ሰው አምኖ መጠመቅ አለበት እንጂ ሳያምን፣ ሳያውቅ ቢጠመቅ ምን ይረባዋል? የሚል ነው። በማር. 16፥16 ላይ "ያመነ የተጠመቀ ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል" ይላል። ይህ ቃል ላመኑት ሳይሆን ላላመኑት የተነገረ ነው። በተለይም ወደ ዓለም በሚሄዱበት ሰዓት ሐዋርያት አገልግሎታቸው የቀና ይሆን ዘንድ ያላመኑት ማመን ስለሚያስፈልጋቸው ነው። ለቃሉ መነሻ የሆነው ግን እንዲህ ይነበባል "... ተነስቶም ያዩትን ስላላመኑአቸው አለማመናቸውንና የልባቸውን ጥንካሬ ነቀፈ" ማር. 16፥14 ይህ ቃል ነው እንግዲህ ያመነ የተጠመቀ ይድናል ለሚለው መነሻው ታዲያ ጌታ አለማመናቸውን የነቀፈበትን ቃል ሕፃናት መጠመቅ የለባቸውም ብሎ ከሚያምን ቤተሰብ በተገኙ ሕጻናት ላይ መፍረድ እጅግ ከሁሉ የከፋ ኃጢአት ነው።

ሃይማኖት በሥጋ ትልቅነት አይደለም። እግዚአብሔር ገና ትንንሽ ብላቴኖችን መርጦአልና ለምሳሌ "... በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ ከማህጸንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ" ይላል ኤር. 1፥4 ታዲያ ገና በሥጋ ትልቅ አልሆነምና ሊቀደስ አይችልም ማለት ነውን? አይደለም። እግዚአብሔር በማንኛውም ጊዜ መምረጡን አመልካች ነው እንጂ።

"ሕጻናትን ተውአቸው ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው" ማቴ. 19፥14። እነዚህ የሚያመለክቱን ሕጻናት ገና በሕፃንነት ዕድሜያቸው ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት እንዲኖራቸው በግልጽ ያስቀመጡ ናቸው። ታዲያ ከየት አምጥተው ነው ሕጻናት መጠመቅ የለባቸውም የሚል የፈጠራ ወሬ የሚያወሩት ቃሉ እኮ



www.ethiopianorthodox.org

(ማር. 16፥15) ቢሆን የሚገልጠው ስለማመን እንጂ ሕጻናት አይጠመቁ የሚል ፍቺ አይሰጥም "ነገር ግን ለገዛ ጥፋታቸው ወንጌሉን ያጣምማሉ" እንደተባለ እንዲሁ ዛሬም ያጣምሙታል እንጂ ገላ. 1፥8። እነሱ ለሚሉት መግለጫ አይደለም። እግዚአብሔር የእኛን ሥጋ ትልቅነት አይደለም የሚያየው በመንፈሱ ልንኖር የምንችል መሆናችንን እንጂ የእግዚአብሔር ቃል "ሰው ፊትን ያያል እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል" ይላል 1ሳሙ. 16፥7 ይህ እውነት የሚያሳየን በሰው ፊት ያለ ትልምስና በጌታ ዘንድ ምኑም ነው። ብላቴናውን ዳዊትን ለንግሥና ሲመርጠው ገና በለጋነት እድሜው ነበር። ለጌታ ይህ ሰው አያስፈልገውም አላለም። ለጌታ ሁላችን እናስፈልገዋለን። አህያዋና የአህያይቱ ውርንጭላ ተፈተው ጌታ እንደተቀመጠባቸው ሁሉ እንዲሁ እናቶችና አባቶችን ሕጻናትም በሙሉ ሊፈቱ ጌታም ሊከብርባቸው ይገባል።

ሕጻናት መጠመቃቸው እኮ ለጌታ ክብር የተዘጋጁ ማድረጋችን መሆኑ ሊታወቅ ይገባዋል ማቴ. 21፥2-3 ራስን ከፍ በማድረግ ሕጻናትን ንቀን አይጠመቁ ማለት ለእግዚአብሔር ክብር አይዘጋጁ፣ ልጆች አይሁኑት ብሎ መፍረድ ነውና ፕሮቴስታንቶቹ ቢያስቡበትና ይህን አመለካከት አስተካክለው ቢመለሱ ይበጃቸዋል።

በተጨማሪም ጥምቀት ግዝረትን የተካ የማመናቸውን ምልክትና ልጅነት የምናገኝበት መሆኑ ተለይቶ ሊታወቅ ይገባዋል። ለዚህም በቆላ. 2፥11-13 የምናነበው ያስረዳናል። ይህ እውነት ከሆነ በዘፍ 17፥12 ላይ አብርሃም እግዚአብሔርን ማመኑ የታወቀ እንዲሆን በቤቱ ያሉ ሁሉ ተገርዘዋል። በስምንተኛው ቀን ተገርዘው ከአብርሃም አምላክ ጋር እንዳሉ እርሱም አምላካቸው



እንደሆነ በአህዛብ ሁሉ ዘንድ የታወቀ እንዲሆን እግዚአብሔር ለአብርሃም ቃል ኪዳን ሰጥቶት ነበር። ሕጻናቱ ሲገረዙ አውቀው መሆን ነበረበት ትልቅ መሆን ነበረባቸው ብንል እንሳሳታለን። ሁሉም ተገርዘዋል። ጥምቀትም እንዲሁ ነው።

ለምሳሌ በሐዋ. 16፥16 እና ቁጥር 31 ላይ የምናገኛቸው ሊዲያና ቀርኔሌዎስ በእነርሱ እምነት ቤተሰቡ በሙሉ ተጠምቋል። ይህም ሕጻናትን ይጨምራል ሕጻናት የቤተሰብ አባል ናቸውና። በወንጌል ላይ ከ15 ሰዎች በላይ ይህን ምልጃ በመፈጸም በቤተሰባቸው እምነት ልጆች ድነዋል። ይህማ ባይሆን እግዚአብሔር ስለመረጣቸው ሰዎች የገባውን ቃል ኪዳን ያፈርስ ነበር ማለት ነው። ለአብርሃም፣ ለዳዊት ስለገባው ቃል የእነርሱ እምነት፣ በረከት ይኸው ጠብቆን እናያለን። ነገር ግን ይህን መጠራጠር ክህደት ነውና ልባቸውን ይመልስልን። አሜን!

ሁለተኛው እምነት እንጂ ጥምቀት አያድንም የሚል ነው። ለዚህ የሚያቀርቡት ጥቅስ እንዲህ ይላል "... አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሠከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጧል እርሱም ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው።" ሮሜ 3፥21-26

"አብርሃምም አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት" ዘፍ 15፥6

**የሚያጸድቀው እምነት ነው እንጂ መጠመቅ ወይም አለመጠመቅ አይደለም ባዮች ናቸው። በመጀመሪያ እነሱ የጠቀሱትን እንተንትነው። ሮሜ 3፥21 ጀምሮ ያለው የሚገልጠው በሕግ እንድናለን። ሕግ በመጠበቅ እንጸድቃለን የሚሉ ያለ ሕግ**

የተገለጠውን ኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘውን ጽድቅ ይገልጥልናል እንጂ ሳይጠመቁ የሚገኝ ጽድቅን አልተናገረም። በሕግ ለሚመኩ መልስ ሰጠ እንጂ ጥምቀት ያስፈልጋል። ያለ ጥምቀት ልጅ መሆን የለም ለምንል ለእኛ አይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ ጥቅሱ የሚናገረው ስለምን እንደሆነ እንዲለዩት እንጠይቃለን። የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል። እንደሚባለው የመጽሐፉን ቃል ሳያስተውሉ ሮጦ የጥምቀትን መንፈስ ለመጣላት ሲሉ በሁለንተናው እየተጋጩ ነውና ያስተውሉት እንላለን። ወደ ቀደመ ነገራችን እንግባና መልሱን እንመልከት።

ጥምቀት የእኛ ሕግ ሳይሆን ሕገ እግዚአብሔር ነው። እኛ አይደለንም ተጠመቁ ያልነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው እንጂ። ለኒቆዲሞስም ዳግም ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለድክ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አትገባም ብሎታል።

እዚህ ላይ የሚጠይቁን ጥያቄ አለ ታዲያ ፈያታዊ ዘየማን እንዴት ሊገባ ቻለ? እምነቱ እንጂ ያዳነው መጠመቁ አይደለም ይላሉ። ለዚህ መልስ አለን።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ጥምቀት በሦስት ዓይነት መንገድ ይፈጸማል።

1ኛ በውሃና በመንፈስ ቅዱስ፣ ዮሐ. 3÷3-5
2ኛ በእሳትም በመንፈስ ቅዱስም፣ ማቴ. 3÷11
3ኛ በደም 1ዮሐ. 5÷6



ስለዚህም በዚህ መሠረት ፈያታዊ ዘየማን (በቀኙ የተሰቀለው ወንበዴ) የደም ጥምቀት የደረሰው በመሆኑ ልጅነት ተቀብሎ ገባ እንጂ ልጅ ሳይሆን ወደ ገነት አልገባም። እንደ ሰው ሃሳብና ጥበብ ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር እውነት ሁሉ ይደረጋል እንጂ።

ይህን መሠረት አርገን የቀደመውን ነገር እንመልሳለን። ጌታ ለኒቆዲሞስ መጠመቅ እንዳለበት ዋጋም እንዳለው አሳስቦታል። ሐዋርያትም እንዲሁ ላመኑት ሁሉ ተጠመቁ ይሏቸው ነበር ሐዋ. 2÷38፣ ሐዋ. 16÷16፣ 16÷31፣ ሐዋ. 22÷16 ለጠቢብ አንድ ቃል ትበቃዋለችና ይበቃናል። አዳኙ ልጅነት ሰጪው ጥምቀትም መሆኑን በግልጽ ያስረዳናል። ባንጠመቅ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥት ማየት አንችልም። አይደለም መግባት ማየት እንደማንችል ይነግረናል። ለዚሁ ነው አማናዊት ተዋህዶ ሃይማኖታችን ወንድ ልጅ በተወለደ በ40 ቀኑ ሴት ልጅ በተወለደች በ80 ቀኗ የልጅነትን ጥምቀት የምናተጠምቀው።

5. <u>ቁርባን፡-</u> ቁርባን በፕሮቴስታንቶች ዘንድ የክርስቶስ ሥጋና ደም ሳይሆን መታሰቢያ (Remembrance) ነው። ለዚህም ኢክርስቲያናዊ አመለካከታቸው የሚያቀርቡት ነጥብ ቢኖር ሉቃ.22÷19 "...ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ" የሚለውን ነው ነገር ግን ይህን ለመታሰበያዬ አድርጉት ያለው ሥጋዬ ደሜን ስትበሉና ስትጠጡ ሞቴን ህማሜን፣ መገረፌን፣ መነሳቴን ታስባላችሁና ማለት ነው። ለዚህም ቅ/ጳውሎስ በሚገባ አብራርቶታል። አንዳንዶቹ ቁርባን አያስፈልግም ሰው የሚድነው የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ ነው ይላሉ።



www.ethiopianorthodox.org

✞ በኦ/ተ/ቤ/ክ ቁርባን አማናዊ የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው ትላለች እንጂ መታሰቢያ ብለን አናምንም። እስኪ ጌታ ስለ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ አማናዊነት የተናገረውን እንመልከት። በመጀመሪያም ማቴ. 26፥26 ላይ እንዲህ ይላል "ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራውን አንሥቶ ባረከ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ፤ ጽዋውን አንስቶ አመስግኖ ሰጣቸው እንዲህም አለ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው"። ቃሉ በግልጽ እንደነገረን ይህ ሥጋዬ ነው አለ እንጂ ይህ ህብስት የመታሰቢያ ሥጋዬ ነው አላለም። ደሙንም እንዲሁ ታዲያ ከየት አምጥተው ነው እንዲህ የምንለው ብሎ መጠየቅ ይገባል። የሥጋና የደሙን እውነተኛነት ሲያረጋግጥልን በዮሐ. 6፥55 "ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው" ሲል ገልጾልናል። ሥለዚህ የምንቀበለው ሥጋና ደም መለኮት የተዋሀደው ነፍስ የተለየው አዳኝ ነው ብለን እንቀበለዋለን። አዳኝነቱንም ሲገልጽ "ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው" በማለት ገልፆአል ዮሐ. 6፥53።

## መታሰቢያ ነው ለምን አሉ?

"እንጀራንም አንስቶ አመሰገነ ቆርሶም ሰጣቸውና ስለ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ። እንዲሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን አንስቶ እንዲህ አለ ይህ ጽዋ ስለ እናንተ የሚፈሰው ደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው" ሉቃ. 22፥19 ይላል። ይህ ሥጋው መሆኑን አረጋግጦ ከሰጣቸው



በኋላ አስቡኝ ሞቴን መከራዬን ሁሉ አስቡ አለ እንጂ ይህ ሥጋ ለመታሰቢያዬ የሚሆን ነው አላለም ለዚህ የበለጠ የሚያብራራልን ቃል በቆሮንቶስ መልዕክ ላይ የተጻፈው ነው "... ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንስቶ ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ" 1ቆሮ.11፥25 ጽዋው በደሙ የሚሆን አዲስ ኪዳን መሆኑን አረጋግጦልናል። መቼ ይህን እንደምናደርግ ሲገልጽ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ አስቡኝ ሞቴን ትንሣኤን ትመሰክራላችሁ ብሏል። በቁጥር 26 ላይ "ይህን እንጀራ በበላችሁና ጽዋውን በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ሞቱን ትናገራላችሁ" ይላል። እነሆ በልተንና ጠጥተን ልንመሰክር መብቃት እንደሚቻለን ገለጸልን እንጂ ደሙና ሥጋው (ቁርባኑ) መታሰቢያ አይደለም አማናዊ ነው። መታሰቢያማ ቢሆን ሕይወት ልናገኝበት ባልቻልን ነበር። ሥጋዬን ብሉ ደሜንም ጠጡ ያለን ለዚሁ ነውና።

## የአይሁዶች ተቃውሞ

"... የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ ነውና" ዮሐ. 6፥33 የአይሁድ ተቃውሞ ሊነሳ የቻለው እንጀራውን ስጠን ባሉት ጊዜ ነበር ኢየሱስ ግን የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ሲላቸው እንዴት ይህ ሰው ሥጋውን ልንበላ እንችላለን ነው ያሉት። እውነተኛ ሕይወትን የሚሰጥ እንጀራ መሆኑን የገለጸውን አምላክ ተጠራጥረው ሊገሉት ይፈልጉ የነበረው። አማናዊ ሥጋና ደሙን በእምነት ባለመቀበላቸው ብዙ ጎድሎባቸዋል። ከሕብረቱ ወጥተዋል። ይኸው የአይሁድ ተቃውሞ እንዴት ሥጋና ደሙን ልንበላና ልንጠጣ እንችላለን ብለዋል። ያኔ የተጠራጠሩት በዛሬዎቹም ከእምነት በወጡ ቡድኖች ላይ ይታያል።

## የአይሁድ ተቃውሞ

- እንዴት የዚህን ሰው ሥጋ በልተን እንድናለን?
- በእርግጥ ሥጋውን ሊሰጠን ይችላል? እንዴትስ ለሁላችን ይበቃል?
- እንዴት ከሰማይ የወረድኩ እንጀራ እኔ ነኝ ይላል ሕይወትም ታገኛላችሁ እንዴት ይለናል?

## የፕሮቴስታንት/ጴንጤዎች

- መዳን በእምነት ብቻ ነው
- መታሰቢያ ነው እንጂ እንዴት የራሱ ሥጋና ደም ይሆናል?
- ሕይወት በእምነት ብቻ እንጂ ሥጋ ደሙን በመብላት አይደለምን?

እነዚህ ከላይ ያየናቸው ተመሳሳይነት ያላቸው አመለካከቶች እግዚአብሔርን ኢየሱስን በመጠራጠር እንዴት ሊሆን ይችላል በማለት የሚነገሩ ናቸው። ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና ሉቃ. 1÷37 ይህ የጌታ ንግግር ሥጋውን በልቶ ደሙን ጠጥቶ የመዳንን ምስጢርን ሲነግራቸው እንኳን አይደለም ለአሁኖቹ ብዙ በእምነት ለደከሙትና ለሚጠራጠሩት ለሐዋርያትም አስጨንቆአቸው ነበር ነገር ግን ጌታ "ይህ ያሰናክላችኋልን? እንግዲህ የሰው ልጅ አስቀድሞ ወደነበረበት ሲመጣ ብታዩ እንዴት ይሆናል? ሕይወት የሚሰጥ መንፈስ ነው ሥጋ ምንም አይጠቅምም እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው። ነገር ግን ከእናንተ የማያምኑ አሉ"። ዮሐ. 6÷62-64 ብሎ ተናግሯል። ይህንም የክርስቶስ ሥጋ እውነተኛ የራሱ ሥጋ ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሀደው መሆኑን ደሙም እውነተኛ የክርስቶስ ደም መሆኑን ማመን በመንፈስ ነው እንጂ በሥጋ አይደለም። ይህ ደግሞ ሕይወት ነው የማያምኑ አሉ እንዳለ የዛሬዎቹ አለማመን አያስደንቅም ከጥፋት ልጅ ጋር በክህደት የሚተባበሩ ስላሉ አሁንም አማናዊነቱን



ተጠራጥረው ያሉ መታሰቢያ ነው የሚሉ ቀድመው የካዱትን መስለዋቸዋልና መጽሐፍ ቅዱሱን ያስተውሉት እንላለን። ልብ ይስጥልን።

## ቊርባኑ የመረቀልን የሚያድነን እውነተኛ መንገዱ ነው።

"እንግዲህ ወንድሞች ሆይ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ክርስቶስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን በእግዚአብሔር ቤት ውሃ ታጥበን በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ" ዕብ. 10÷19-23 በክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ወደ መንግሥቱ ለመግባት እንዲቻለን ድፍረት እንዳለን ያረጋግጥልናል። ይህም አማናዊ አዳኝ መድኃኒት መሆኑን ይገልጽልናል። ደሙ ኃጢአታችንን ሁሉ አጥቦልናልና። ስለዚህም እውነት የመረቀልን ሕያው የሆነውን መንገዱን ይዘን እንሂድ ይህም የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደሙን በመብላትና በመጠጣት የሚገኝ የእግዚአብሔር ማዳንና በረከት ነው።

## ሥጋና ደሙን (ቊርባኑን) ለመቀበል ምን መሆን አለብን?

ወደ ጌታ ሥጋና ደም ለመምጣት ቊርባኑንም ለመቀበል የሚያስፈልገው ላመኑና ለተጠመቁት ንስሀ ገብቶ በካህኑ ፊት ቀኖና ተቀብሎ መቅረብ ነው። ንስሀ ሳይገቡ መቀበል ግን ድፍረት ነው። በጥሩ ውሃ ታጥበን ያለው ንስሐ ገብተን ማለቱ ነው ዕብ. 10÷23። እንዲሁም በተጨማሪ "ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት" 1ቆሮ. 11÷27። በዚህ መሠረት ሰው ንስሐ ሳይገባ የቀደመ በደሉን

በንስሐ ውሃ ሳይታጠብ ቢቀርብ ዕዳ ይሆንበታል። ስለዚህ ወደ ቁርባኑ ለመቀረብ የሚያስፈልገው ትልቁ ነገር ንስሐ ነው።

በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በቅዳሴው ሰዓት ካህኑ እጁን ይታጠባል ዝሙት፣ ቂም፣ ልዩ ሃሳብ ያለበት ቢኖር አይቅረብ ይላል። ይህም ንስሐ ሳይገባ ማለት ነው። ዝሙት በሥጋ ላይ የሚሠራ ኃጢአት ነው። "ወደ ሴት ያየ የተመኛትም አመነዘረ" ይላልና ማቴ. 5፥28፣ ቂም ይዞ ጸሎት ሳል ይዞ ስርቆት አይሆንም ጌታም "በቀል የእኔ ነው እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ" ይላል ሮሜ 12፥19። ስለዚህ በሰው ቂም ሳይዙ መገኘት ለዚያም ሰው ኃጢአቱን ይቅር ማለት ይገባል። "ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ የሰማዩ አባታችሁ እናንተንም ይቅር ይላችኋል ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ የሰማዩ አባታችሁ ይቅር አይላችሁም" ይላል። ማቴ. 6፥14-15 ስለዚህ እውነት ከቂም መራቅ ስላለብን ይህን ካህኑ ያውጃል ያ ሰው እግዚአብሔር ይቅር እንዲለው ሲመጣ ያዘነባቸውንና ያሳዘናቸውን ይቅር ብሎ መሆን አለበት። ያለዚያ ግን "የኃጢአት ደሞዙ ሞት ነው።" እንዳለው ያ ሰው በሞት ፍዳ ይያዛል ሮሜ 6፥23።

ልዩ ሃሳብ ማለት በመጠራጠር፣ ግራ በመጋባት፣ በእምነት መጉደል ወይም አማናዊ የሆነውን የክርስቶስን ሥጋ ያድነኝ ይሆን፣ አያድነኝ ይሆን በማለት ከተዋህዶ ሃይማኖት ውጭ የሆነ ንስሐ ሳይገባ፣ እምነቱን ሳያስተካክል በእምነቱ ሕፀፅ ይዞ አይቀበል ለማለት ነው። አንድ ሰው ንስሐ እስኪገባና ለኃጢአቱ ይቅርታ እስከለመነ ድረስ አንዳች እንዳይቆርብ የሚያግደው ነገር የለም። ቁርባን ዕድሜን፣ ጾታን አይወስንም፣ አይለይም። ወንድ ልጅ



ከተጠመቀበት ከ40 ቀን በኋላ ሴት ልጅ ከተጠመቀችበት ከ80 ቀን በኋላ ንስሐ እየገቡ መቁረብ እንዳለባቸው የቤተክርስቲያን ቀኖና ያዛል።

6) ፕሮቴስታንቶች በታቦት፣ በስዕል፣ በመስቀል አያምኑም። እንዲያውም ለታቦት፣ ለስዕል፣ ለመስቀል መስገድ፣ መሳለም ለጣዖት መስገድ፣ መሳለም ነው ብለው ያጣጥላሉ።

✞ በኦ/ተ/ቤ/ክ/ግን ሥዕል፣ መስቀል፣ ታቦት ክብር አላቸው የእነዚህም ሰጪና ባለቤት እግዚአብሔር ነው።

## ታቦት

ታቦት ማለት ቤተ፣ አደረ ከሚለው የግዕዝ ቃል የወጣ ነው። ታቦት ማደሪያነቱ ለጽላተ ኪዳኑ ማደሪያና የእግዚአብሔርም መገለጫ ነው። ስለዚህ ያሉትን መ/ቅዱሳዊ ጥቅሶች እንይ።

- "እግዚአብሔርም ሙሴን ወደ እኔ ወደ ተራራው ውጣ በዚያም ሁን እነርሱን ታስተምር ዘንድ እኔ የጻፍኩትን ሕግና ትዕዛዝ የድንጋይም ጽላት እሰጥሃለሁ አለ" ዘጸ. 24፥12 ይህ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተጻፉትን ሕግና ትዕዛዝ እንዲቀበል ጥሪ ካደረገለት በኋላ ምን መደረግ እንዳለበት ሲገልጽ "በመጀመሪያ በመካከላቸው አድር ዘንድ መቅደስ ይስሩልኝ።" ዘጸ. 25፥8።
- "ከግራር እንጨትም ታቦትን ይሥሩ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል ይሁን" ዘጸ. 25፥10 እነዚህ በሙሉ ከእግዚአብሔር



www.ethiopianorthodox.org

ለሙሴ የተሰጡ መመሪያዎች ናቸው የሰጠሁትንም ጽላት በታቦቱ ውስጥ አኑረው ብሎታል። በመቀጠልም

* "በዚያም ከአንተ ጋር እገናኛለሁ የእስራኤልንም ልጆች ታዝዝ ዘንድ የምሰጥህን ነገር ሁሉ በምስክሩ ታቦት ላይ ባለው በሁለት ኪሩቤል መካከል በስርየት መክደኛው ላይ ሆኜ እነጋገርሃለሁ።" ዘጸ. 25፥22 ከዚህ በላይ ምን ማረጋገጫ ያስፈልጋል። እግዚአብሔር በታቦቱ ላይ ሆኖ ስለሚያናግረው ማደሪያው መሆኑን እግዚአብሔር ራሱ ገለጸ እንጂ ሙሴ ፈጥሮ ያወራው ወይም ቤተ ክርስቲያን ፈጥራ የምትሰራው አይደለም ፍጹም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው።

<u>ከዚህ በመነሳት ሃሳቡን ትንሽ እስኪ እንመልከት</u>

ታቦት በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር በደብረ ሲና ለሊቀ ነቢያት ለሙሴ ተገልጦ የውለታና የመታዘዝ ምልክት እንዲሆን፤ በዚህ አድሬ በዚህ ላይ ሆኜ እገለጥላችኋለሁ ሲል አስር ሕግጋት የተጻፈባቸውን ሁለት ጽላቶችን ሰጠው። ዘጸ. 24፥12፤ ዘጸ. 28፥7። ታቦት እግዚአብሔር 10 ሕግጋት ያስተላለፈበት ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር የክብሩ መገለጫ ዙፋን ነው። እነ ሰሎሞን ሌሎችም እስራኤላውያን ለታቦት የሠገዱት በታቦቱ ላይ ስላለው ሕግ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ለምሕረት በሚመጣበት ጊዜ ዙፋኑ ስለሆነም ነው። ይኸውም እግዚአብሔርን እስራኤል በሚያስቀይምበት ጊዜ እርሱ ደግሞ በረሃብ በቸነፈር በጦርነት በምርኮ ይቀጣቸዋል ኢያ. 7፥6። ንስሐ ገብተው ይቅርታ ሲጠይቁት ደግሞ አባት ልጁን እንደሚምረው ደግሞ እርሱም ይምራቸዋል። እግዚአብሔር



የማራቸው መሆኑን የሚያውቁት በታቦቱ ላይ ብርሀት ደመና መጥታ ስታርፍ ነው። የምስክሩ ታቦት ድንኳን በደመና ይሞላል። በታቦቱ ላይ ሆኖ እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን ያነጋግራል። ይህንንም እስራኤላውያን "ሽሂኑሃ" ይሉታል። ለምህረት መምጣት፣ መገለጥ ማለት ነው።

ቤ/ክ የብሉይ ኪዳንን የእምነት ጥላነት ይዛ እንደመምጣቷ፤ ታቦተ ሕጉ፣ ጽላተ ኪዳኑ አላት። የአዲስ ኪዳኑ ታቦት የክርስቶስ ሥጋና ደም የሚፈትትበት ቅዱስ መሠዊያ ነው። መንፈስ ቅዱስ በታቦቱ ላይ የሚወርድበት የቅዳሴው ሰዓት "ኤጲፋንዮስ" "አስተርዮ" ይባላል ይህም መገለጥ ማለት ነው።

ቤ/ክ ስለ ታቦት ያላት ትምህርታዊ መመሪያ ያልገባቸው አንዳንዶች እንደመሰላቸው ቢተረጉሙትም ቤ/ክርስቲያናችን ግን በሙሴና በክርስቶስ፣ በብሉይና በሐዲስ፣ በጣዖትና በታቦት፣ በምሳሌና በአማናዊ ያለውን ልዩነት ስለምታውቅ ለሚጠይቃት ሁሉ ይህን እምነቷን ታስረዳለች።

በኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት (Oriental Churches) ታቦት የተለመደ ሕግ ነው። ሥጋና ደሙን የሚፈትቱት በታቦቱ ላይ ነው። ክርስቲያኖች አንድ ሊያውቁት የሚገባው ትልቁ ነገር በብሉይ ኪዳን የነበረው የታቦት አገልግሎት የበጎችና የጥጆች ደም በቅድስተ ቅዱሳን ፊት ለፊት የመሠዋት ሥርዐት ነበር። ይህም በእውነተኛው አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደም ተወግዶ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ ይለናል ዕብ. 9፥12። ስለሆነም አሁን በቅድስቱ ውስጥ በታቦቱ ላይ ይገለጽና ይከብር የነበረው

እግዚአብሔር እንደሆነ ሁሉ የልጁ የኢሱስ ክርስቶስ ደም እኛን ከኃጢአት ሁሉ በማጠብ የቀደመውን መሥዋዕት አስወግዶ እርሱ መሥዋዕት በመሆን ከብሯል። በታቦቱም ላይ የማዳኑን ምስጢር በመግለጽ ሰዎች ሁሉ ሥጋውን በልተው፣ ደሙን ጠጥተው፣ እንዲድኑ ይናገራል ዮሐ. 6፥54። ይህን እውነት በመያዝ ታቦት በብሉይ ኪዳን የነበረ አገልግሎትና በአዲስ ኪዳን ያለው አገልግሎት ልዩነቱን በትክክል መረዳት ይገባል። ይህንኑ በመረዳት ነው በብሉይ ኪዳን አሕዛብ የነበሩ አገሮች በአዲስ ኪዳን ታቦትን የያዙ የምናገኘው። ለምሳሌ ግብጻውያን ታቦቱን "ሉሕ" ይሉታል ጽላት ሰሌዳ ማለት ነው ያለሱ ሥጋና ደሙን አይፈትቱም።

የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ተብለው የሚጠሩ የግሪክ፣ የሩሲያ፣ የሮማኒያ ሌሎችም ወደ ክርስትና የተመለሱት ከአረማዊነት ስለሆነ የታቦቱን ምሥጢር አያውቁትም በታቦቱ ፈንታ ከመንበር የማይነሳ እንደ ታቦት የሚከብር የጌታ የስቅለቱ ወይም የግንዘቱ ሥዕል ያለበት የነጭ ሐር መጎናጸፊያ አላቸው። ያለሱ ሥጋና ደሙን አይፈትቱም። ይህንንም በጽርዕ "እንደምኒሲዮን" ይሉታል። "ሕየንተ ታቦት" ማለት ነው። የሮማ ካቶሊኮች "ሜንሳ" Mensa ይሉታለ። ጠረጴዛ ማለት ነው። ከእምስቱ አብያተ ክርስቲያናት በቀር አዲስ ቤ/ክርስቲያን በሚሰራበት ጊዜ የእጽመ ቅዱሳን ሽራፊ እንዲቀመጥ ያዛል።

ቀደም ብለን ከላይ ለተናገርናቸው በሙሉ እነዚህን ጥቅሶች ተመለከት። ዘጸ. 13፥21-22፤ 19፥16-18፤ 24፥16-18፤ 24፥16-17፤ 33፥10-11፤ 25፥22፤ 16፥17፤ ዘዳ. 5፥4፤ ዘኁል. 9፥15-16፤ 7፥8-9፤ ዘሌዋ. 16፥2፤ 9፥6-23፤ 14፥10፤ ነገ. ቀዳ. 8፥10-11፤ ሐጌ 4፥9፤ ዮሐ. 1፥14።



## ጽላት የእግዚአብሔር ነው ታቦት ደግሞ ማደሪያው

ዘጸ. 31፥18 ላይ እንደምንመለከተው እግዚአብሔርም ከሙሴ ጋር በሲና ተራራ የተናገረውን በፈጸመ ጊዜ በእግዚአብሔር ጣት የተፃፈባቸው ከከበረ ድንጋይ የተሰሩ ሁለቱን የምስክር ጽላቶች ሰጠው ይለናል። በሰው ባልሆነ በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈውን ይዞ ሙሴ ከተራራው ላይ ሲወርድ ይዞአቸው የነበሩት ጽላቶች "የእግዚአብሔር ሥራ ነበሩ። ጽሕፈቱም በጽላቶቹ ላይ የተቀረጸባቸው የእግዚአብሔር ጽሕፈት ነበር።" ዘጸ. 32፥15-17 ይነግረናል። ታዲያ የእግዚአብሔር ሥራ ከጣዖት ጋር ምን መስማማት አለው? ምን ግንኙነት አለው? የእግዚአብሔርን ታቦት መቃወም የእግዚአብሔርን ሥራ መቃወም ነውና፤ በእርግጥ እነዚህ ጽላቶችን ሙሴ ከተራራው ይዞ በወረደ ጊዜ ሕዝቡ ለጣዖት ሲሰግዱ ስላየ እጅግ አዝኖ ጽላቱን ወርውሮታል። ጽላቱም ተሰበረ ጣዖቱም ተቀጠቀጠ፣ ደቀቀ። ነገር ግን ጽላቱን ሰብረሃልና አያስፈልግህም አልተባለም። እግዚአብሔር የአምልኮት ዕቃው መገሪያው በፈቃዱ ሊገለጥበት የወደደው ነውና ዳግም በዚያው መልክ እንዲቀርጸው አዘዘው "እግዚአብሔርም ሙሴን አለው ሁለት ጽላቶች እንደፊተኞቹ አድርገህ ጥረብ በሰበርካቸው በፊተኞቹ ጽላቶች የነበሩትን እጽፍባቸዋለሁ።" ዘጸ. 34፥1 እንዳለው ሁሉ በዘዳ. 10፥1-5 እንደምናየው በነዚያ ጽላቶች ላይ እንደ ፊተኞቹ እግዚአብሔር ጽፎባቸዋል።

ታቦት የጽላቱ ማደሪያ ደግሞ የእግዚአብሔር መገለጫ ለመሆኑ መ/ቅዱስ እንዲህ ይለናል። "...ለአንተም የእንጨት ታቦት ሥራ ከግራር እንጨትም ታቦትን ሥራ ጽላቶቹን ከሠራሁት ታቦት ውስጥ አደረግኋቸው እግዚአብሔርም እንዳዘዘ በዚያ ኖሩ።" ዘዳ.

10፥1-5 በተጨማሪም ዘጸ. 25፥22፣ ዘዳ. 37፣ ዘጸ. 26፥31-37 ተገልጾ እናገኘዋለን።

## ለታቦት ሊደረግ የሚገባ ስግደትና ክብር

- ኢያ. 7፥6 ታቦት የእግዚአብሔር ስለሆነ ለእግዚአብሔር አምልኮትን ማቅረቢያ ነው። ሙሴም ታቦቱ በተዘጋ ጊዜ "አቤቱ ተነሳ ጠላቶችንህም ይበተኑ ዘንድ የሚጠሉህም ይሽሹ ዘንድ" እያለ ይጸልይ ነበር። ኢያሱ ቀኑን ሙሉ በታቦቱ ፊት እየሰገደ ዋለ ይላል። እነሆ ባያስፈልግ ኖሮ ኢያሱ ባላደረገው ነበር፤ ባልሰገደም ነበር።
- ዘኁ. 7፥89 "ሙሴም ወደ መገናኛው ድንኳን እርሱን ለማነጋገር በገባ ጊዜ የቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ ካለው ከስርየት መክደኛ ከላይ ከኪሩቤል መካከል ድምጹ ሲናገር ይሰማ ነበር። እርሱም ይናገረው ነበር።"
- ሳይገባው ሥልጣነ ክህነት ሳይኖረው ታቦተ እግዚአብሔርን በመንካቱ ኦዛ ተቀስፏል 1ዜና. 13፥10፣
- ኦሪት ዘጸአት 33፥10 "ሕዝቡም ሁሉ የዳመናው ዓምድ በድንኳኑም ደጃፍ ሲቆም ያየው ነበር። ሕዝቡም ሁሉ ተነስቶ እያንዳንዱ በድንኳኑ ደጃፍ ይሰግድ ነበር በድንኳኑም ውስጥ የእግዚአብሔር ታቦት ነበረች። ይላል ስለዚህም በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ በሚገኘው በታቦት ፊት መስገድ የሚገባ እንጂ እግዚአብሔር ያልፈቀደው አለመሆኑን ያሳየናል።
- ታቦት ስመ እግዚአብሔር የተጻፈበት ስለሆነ ሊሰገድለት ይገባል። ይኸውም ጉልበት ሁሉ ለክርስቶስ ስም ይምበርከክ ይላል። ለስሙ ሊደርግ ስለሚገባው ስግደት በታቦት ፊት



www.ethiopianorthodox.org

እንሰግዳለን ፊል.2፥3 ለታቦት ስለሚደረግ ክብር መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል።

- "የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ወደ ሰፈር በገባ ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ በእልልታ ተቀበሉት" ይላል። 1ሳሙ 4፥5 ዳዊትም እንዲሁ በእግዚአብሔር ፊት በመዘመር የእግዚአብሔርን ታቦት አክብሯል። 2ኛ ሳሙ. 6፥16-23 ሕዝቡም ታቦቱን ባዩ ጊዜ ሁለት ሺህ ጫማ ያህል ርቀው እንዲሄዱ ያዛል። ለሕዝቡም ወደ ታቦቱ እንዳይቀርቡ መታዘዛቸውን ይገልጻል። ኢያ. 3፥3 የእግዚአብሔርን ቤት እንደማንኛውም ቤትና ሥፍራ እንዳናየው የጸሎትና የአምልኮት ቦታና ታቦት መሆኑን በዘሌ. 16፥2 እንዲህ ይላል። "እኔ በስርየት መክደኛው ላይ በደመናው ውስጥ እታያለሁና እንዳይሞት በመጋረጃው ውስጥ በታቦቱ ላይ ወዳለው ወደ ስርየቱ መክደኛው ወደ ተቀደሰው ስፍራ ሁልጊዜ እንዳይገባ ለወንድምህ ንገረው" ብሎታል። ስለዚህም ታቦትን እንደሚገባ ማክበር ለታቦት የሚገባ ስግደትን፣ እልልታና ምስጋና በእግዚአብሔር ፊት ማቅረብ የተገባ ነው።

## በታቦት ላይ የሚነሱ የፕሮቴስታንት ጥያቄዎች

1. ፕሮቴስታንቶች ታቦት ተሽሯል ይላሉ ለዚህም የሚያቀርቡት ጥቅስ 2ቆሮ. 3፥3-18 ያለውን ቃል በመጥቀስ ነው። እንዲሁም ከጣኦት ጋር ያገናኙታል።
2. እግዚአብሔር የሰጠው አንድ ታቦት ነው ይህ ሁሉ ታቦት ከየት መጣ? ይላል
3. ታቦት ብሉይ ኪዳን ነው በአዲስ ኪዳን ታቦታችን ክርስቶስ ነው ሽሮታል ይላሉ።

ለእነዚህ ጥያቄዎች መልሶቹን እንደሚገባ እንሰጣለን።

በመጀመሪያ በ2ኛ ቆሮ. 3፥3-18 ያለው ቃል የሚናገረው ስለ ታቦት መሻር ሳይሆን የብሉይ ኪዳንን አገልግሎትና የአዲስ ኪዳንን አገልግሎት በማነጻጸር የተናገረው ነው። እስኪ ለማንኛውም ቃል በቃል እያየነው እንሂድ።

- "እናንተ በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ እንጂ በቀለም አይደለም።" ይህ ማለት በእግዚአብሔር መንፈስ ካለን ማገልገል እንችላለን በቀለም አይደለም ማለቱ እናንተን የቀረጻችሁ ልጆች ያደረጋችሁ ደሙ ነው እንጂ ቀለም አይደለም፤ ማለት በተጻፈ ነገር (ሕግ) አልዳናችሁም፣ በልጁ ደም እንጂ ብሎ ሊያነጻጽር ፈልጎ እንጂ ታቦት አያስፈልግም አላለም። ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን በቀለም የተጻፈውን በመፈጸም እንደሚድኑ ስለተነገራቸው ነው አሁን ግን የእግዚአብሔር መንፈስ አጽንቶአችኋል፣ ቀድሷችኋል ለማለት ነው።

✞ እኛ ታቦት ከዘለዓለም ሞት አዳኝ ነው አላልንም ታቦት የእግዚአብሔር የአምልኮት መማሪያ ስለሆነ ማክበር አለብን አምልኮታዊ ስግደት መስገድ አለብን አልን እንጂ፤ የክብሩ መገለጫ የአምልኮቱ መፈጸሚያ ነውና።

- "...ሥጋ በሆነ በልብ ጽላት እንጂ በድንጋይ ጽላት ያልተጻፈ በእኛም የተገለገለ የክርስቶስ መልዕክት እንደመሆናችሁ የተገለጠ ነው።"



✞ በብሉይ ኪዳን አገልግሎት ውስጥ ጽላቱ ላይ የተጻፈውን ብቻ ያገለግሉ ነበር። ነገር ግን በልባቸው የተጻፈ ስላልነበረ እንደሚገባ አልኖሩበትም። አሁን ግን በአዲስ ኪዳን በልብ ጽላት ውስጥ መቀረጽ አለበት አለን እንጂ ጽላት አያስፈልግም አላለም። ጽላትማ አያስፈልግም ማለት ሕጉ ትዕዛዛቱ አያስፈልጉም ብሎ የእግዚአብሔርን ሥራ መቃወም ነው።

- "... እርሱም ደግሞ በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃል..." በጣም ግልጽ የሆነ ጽሑፍ ነው። የምናገለግለው በመንፈስ መሆኑን ነገረን በፊደል ለማይሆን ማለቱ ለገደለ መገድል፣ ጥርስ ስለ ጥርስ ነበር አሁን ግን በመፊስ ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች ስላደረገን አዲሱ ቃል ኪዳን ደግሞ ክፉን በክፉ አለመቃወም፣ ጠላት መውደድ፣ ስለሆነ ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንድንሆን የአገልግሎቱን መንፈስ ሰጠን ለማለት ነው ማቴ. 5፥17-44። ከዚህ ጋር አያይዞ "ፊደል ይገድላል መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል" ይላል። እንዲያውም ይህ ቃል ጽላትን ለመቃወም የተነገረ ከሆነ አባትና እናትህን አክብር የሚለው ሕግ ይገድላል ማለት ነው። ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ ያለው አማናዊ የሆነው በጽላቱ ላይ የተጻፈው ፊደል ይገላል ስለዚህ ሌላ አምላክ ልናመልክ ይገባናል ማለት ነዋ! ግን አይደለም ቀደም ብለን እንደገለጽነው ሕጉ መንፈስ ስላልነበረው ሰዎችን ከሞት ሊያድን እንዳልቻለ ገለጸልን እንጂ ለታቦት አለማስፈለግ የተነገረ አይደለም።

“ዳሩ ግን የእስራኤል ልጆች ስለዚያ ስለተሻረው ስለፊቱ ክብር የሙሴን ፊት ትኩር ብለው መመልከት እስኪሳናቸው ድረስ ያ በፊደላት በድንጋዮች ላይ የተቀረጸ የሞት አገልግሎት ክብር ከሆነ የመንፈስ አገልግሎት እንዴት ይልቅ በክብር አይሆንም የኩነኔ አልግሎት ክብር ከሆነ ይልቅ የጽድቅ አገልግሎት በክብር አብዝቶ ይበልጣልና” 1ቆሮ. 3÷9

ስለተሻረው ስለፊቱ ክብር ያለው ታቦትን ሳይሆን በሙሴ ፊት ላይ ታይቶ የነበረው የእግዚአብሔርን የክብር ብርሃን ነው። ይህንንም በዘጸ 33÷22 “እግዚአብሔር ለሙሴ እንደሚገለጽና ጀርባውን እንደሚያሳየው ቃል ገባለት። እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር ተነጋግሮ ከጨረሰ በኋላ ከሲና ተራራ ወረደ። የፊቱም ቁርበት አንጸባረቀ” ይላል። ዘጸ. 34÷29 “ከፊቱ ክብር የተነሳ ሙሴን ማየት የእስራኤል ልጆች አልቻሉም። በዚህም ምክንያት ሙሴ በፊቱ ላይ መሸፈኛ አደረገ።” ዘጸ. 34÷35 ጳውሎስ ስለተሻረው የፊቱ ክብር ያለው ይህን በሙሴ ፊት ላይ ታይቶ ስለነበረው አንጸባራቂ ቁርበቱ (ቆዳው) እንጂ ስለታቦት አይደለም።

በማያያዝም ያ በፊደላት በድንጋዮች ላይ የተቀረጸ የሞት አገልግሎት በክብር ከሆነ የሚለው የታቦት አገልግሎት የሞት አገልግሎት ነው ለማለት ሳይሆን ያ የሙሴ ሕግ (ሕገ ኦሪት) ሲሰጣቸው ክብር የነበረው ሆኖ ሳለ ከዘላለም ሞት ሊያድናቸው እንዳልቻለ ሁሉ በዘመናቸው መከራ ጸንቶባቸው እየተፈተኑ በታቦቱ ኃይል እየተቀጡ ስለተጓዙ አገልግሎቱ እነሱን ያዳነ (ከዘለዓለም ጥፋት) ማለትም ከአዳምና ከሔዋን የውርስ ኃጢአት ነፃ ያወጣቸው አለመሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህማ ባይሆን ሙሴ



ሞትና ኩነኔን አገለገለ እንጂ እግዚአብሔርን አላገለገለም ማለት ነውን? እነ ዳዊት እነ ሰሎሞን ነቢያት ሁሉ ያገለገሉት ሞትን ነበር ማለት ነዋ? እግዚአብሔርም የሰጠው የታቦት አገልግሎት የሞት ነበር ማለት ነዋ? ይህ ከሆነ ደግሞ እግዘአብሔር የሙታን አገልጋዮች አምላክ ሊሆን ነው። ይህ ሁሉ ግን ሐሰት ነው። ከዘለዓ ለም ሞት ሊያድናቸው እንዳልቻለ ለመግለጽ ነበር። በክብር ከሆነ ብሏልና እግዚአብሔር ሞትን አክብሮ ሰጣቸው አንልም እነሱም ሞትን አላከበሩም ምስጢሩ ግን ከዘለዓለም ሞት ከመዳን ምስጢር ጋር የተገናኘ ስለሆነ ጳውሎስ አነፃጽሮ ገፈው እንጂ ክብር የለውም አላለም።

የጽድቅ አገልገሎት አብዝቶ ይበልጣል ብሏልና ጽድቅን የሰጠን ለመንግሥቱ ያበቃን ክርስቶስ ስለሆነ ይህ አገልግሎት ቤ/ክ እንደሚበልጥ አውቃ በታቦቱ ላይ ሥጋና ደሙን ፊትቃ ታቀብላለች እንጂ ፍየልና ጥጃ አታርድም።

እንግዲህ ምዕመናን እስከ መጨረሻ ያለው ንባብ ይህን አብራርቶ ለመግለጽ የተሞከረበት እንጂ ታቦት ተሸሯል አያስፈልግም አላለም። ይህማ ቢሆን ጳውሎስ በግልጽ ቋንቋ ተሸሯል ባለን ነበር። ነገር ግን ጌታ እንዳስተማረው “እኔ ሕግና ነቢያትን ልሽር አልመጣሁም ልፈጽም እንጂ” እንዳለ ፈጽሞታል ማቴ. 5÷17 ተሸሯል ብሎ ማስተር ግን ታናሽ እንደሚያደርግ መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጥልናል ማቴ. 5÷20። ታቦት ደግሞ የጌታ ሕግና ትዕዛዝ ነው ዘጸ. 24÷12 እንዲህ ይላል።

"እግዚአብሔርም ሙሴን ወደ እኔ ወደ ተራራው ውጣ በዚያም ሁን እንርሱን ታስተምር ዘንድ እኔ የጻፍሁትን ሕግና ትዕዛዝ የድንጋይም ጽላት እሰጥሀለሁ አለው" ከዚህ በላይ ምን ማረጋገጫ ያስፈልጋል? ስለዚህ የጳውሎስን አገላለጽ እንደሚገባ ልንረዳው ይገባል። ለገዛ ጥፋታቸው ወንጌሉን ያጣምማሉ እነርሱም የተረገሙ ናቸው እንዳለው ከመረገም እንድን ዘንድ እውነቱን እንወቅ ገላ. 1፥8። ኢየሱስ ክርስቶስ የሕያዋን አምላክ እንጂ የሙታን አይደለምና ማቴ. 22፥32።

በዚህ ቃል ላይ የአዲስ ኪዳን አገልግሎት እንደሚበልጥ ተናገረ እንጂ ያ ክብር ያለው ታቦት ክብሩ ቀረ አላለም። ምክንያቱም በአዲስ ኪዳን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከዘለዓለም ሞት በመዳናችን አገልግለን ወደ ዘለዓለም ፍዳ ሳይሆን የምንሄደው ወደ ሕይወት በመሆኑ ነው። ነገር ግን ሁብሉይ ኪዳን አገልግለው ሞት ይይዛቸው ነበር። በአዲስ ኪዳን ግን ሞትን ድል አድርጎ በተነሳው ጌታ እኛም በሞት ላይ ኃይል አግኝተናልና ነው።

በሁለተኛ ደረጃ የሚያነሱት ጥያቄ ታቦትን ከጣኦት ጋር በማገናኘት ነው ጣኦትና ታቦት ግን በፍጹም አይገናኙም ልዩነታቸውን እስኪ እንመልከት

ታቦት

- በእግዚአብሔር ፈቃድ ተሰጠ ዘጸ. 24፥12፤ ዘጸ. 34፥31
- በእግዚአብሔር እጅ ተጽፎ ተሰጠ የእግዚአብሔር ሥራ ነው ዘጸ. 20፥1-20፤ ዘጸ. 23፥17፤
- በኃይል ይሠራል ዘኁ. 21፥8፤
- እግዚአብሔር በፈቀደላቸው እንደ ሙሴ ባሉ ሰዎች ይዘጋጃል።
- የእግዚአብሔር የስሙ ማደሪያ ነው ስሙን ይዟል።
- ሰማያዊ ነው ራእይ 11፥19
- በታቦቱ ላይ እግዚአብሔር ይከብራል። ኢያ 3፥3-19
- የእግዚአብሔር ሕግ ነው ዘጸ. 24፥12
- አምልኮታዊ ስግደት ይቀርብበታል በታቦቱ ፊት መንበርከክ ይገባል ኢያ. 7፥6

ጣኦት

- በሰይጣን ተሰጠ፤
- ሰይጣን ባደረባቸው ሰዎች ተጠረበ፤
- የሰይጣን ማደሪያ ነው፤
- ኃይሉ እግዚአብሔር የለውም፤
- ሰይጣን በወደዳቸው ሰዎች ይዘጋጃል፤
- የአጋንንትን ስም ይዟል፤
- ምድራዊና እጅግ ጊዜያዊ የሰይጣን መጠቀሚያ ነው።
- እግዚአብሔር አይከብርበትም፤ ሰይጣን ግን ይከብርበታል፤
- የእግዚአብሔር ሕግ አይደለም፤
- የሰይጣን ነው እንዳንገዛለት ታዞናል ዘጸ 20፥4-6
- በጣኦት ፊት መንበርከክ ምዋርት ነው፤ ከእግዚአብሔር ጋር ጥል ነው። አታድርግ ተብሏል ዘሌ. 26፥1

ታቦትን ከጣኦት ጋር ለሚያገናኙ ይህን ልዩነት በደንብ እንዲያጤኑት እንመክራቸዋለን። ክርስቶስ ከቤልሆር ጋር፤ ታቦት ከጣኦት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። 2ቆሮ. 6፥15

ሌላው በታቦት ላይ የሚነሣው ጥያቄ ለሙሴ የሰጠው አንድ ታቦት ነው። ይህ ሁሉ ታቦት ከየት መጣ? ይላሉ። የገብርኤል፣ የማርያም፣ ታቦት ብሏል ወይ ይላሉ።

በመሠረቱ እንዲህ ለሚለው አንድ ጥያቄ ብቻ እናነሳለን።

1ኛ የተፃፈው መጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው ስንት ነው?

2ኛ የተሰራው የመጀመሪያው መቅደስ ስንት ነው? ብለን ብንጠይቅ ለእነዚህ የምናገኘው መልስ አንድ ነው የሚል ነው። ታዲያ ይህ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ ከየት መጣ? ይህ ሁሉ ቤ/ክርስቲያንስ ምን ያደርጋል? ሰው እግዚአብሔርን ለማምለክ ከፈለገ የግድ ኢየሩሳሌም መሄድ አለበት ማለት ነውን? ሰው ሁሉም ያቺኑ አንድ መጽሐፍ መጠቀም አለበት ማለት ነውን? ግን አይደለም። መልሱ ለአገልግሎት የሚል ነው እንዲሁ የታቦቱ አገልግሎት እንደሚገባ ይዳረስ ዘንድ ያው አንዱ ታቦት በብዛት አገኘነው እንጂ የተለያየ ታቦት አይደለም። ለምን ይሰየማል? ለሚለው የመታሰቢያ ስማቸው እንዳይጠፋ ጌታ ቃል ገብቶአልና ነው ኢሳ. 56÷4 ለዚህ ስፈ የሆነ ማብራሪያው ቤ/ክርስቲያን በሚለው ላይ ተመልከት።

ከዚሁ ጋር በማያያዝ ታቦታችን ክርስቶስ ነው ይላሉ ግን ክርስቶስ እኔ ታቦታችሁ ነኝ አላለም አምላካችሁ፣ አባታችሁ ነኝ አለን እንጂ። ሮሜ. 9÷5፣ ኢሳ. 9÷6



## ቤተክርስቲያን

ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል በሶስት ዓይነት ፍቺ አጠቃቀም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እናገኛለን። ቤተክርስቲያን የምንለው የክርስትናን ሃይማኖት ነው። ቤተክርስቲያን ማለት የክርስቲያኖች ቤት መኖሪያ ማለት ነው። ፍቺው እንደሚከተለው ነው።

1ኛ) የመጀመሪያው ፍቺ የተወሰነ ቦታን ያመለክታል ሕንጻ ቤተክርስቲያን እንለዋለን።

2ኛ የክርስቲያኖች ሕብረት ወይም አንድነት ቤተክርስቲያን ይባላል። (Community)

3ኛ እያንዳንዱ ግለሰብ ቤተ ክርስቲያን ይባላል።

### የመጀመሪያውን ፍቺና ትርጉሙን እንመልከት

ሕንጻ ቤተክርስቲያኑ የእግዚአብሔር መመለኪያ ቤት ስለሆነ ክርስቲያኖች ተሰባስበው የሚጸልዩበት፣ የሚባረኩበት፣ ሥርዐተ እግዚአብሔርን የሚፈጽሙበት፣ ሕገ እግዚአብሔርን የሚማሩበት፣ ንስሐ የሚገቡበት ስለሆነ ቤተ ክርስቲያን ብለን እንጠራዋለን።

አምላካችን እግዚአብሔር አስቀድሞ ለሙሴ "በመካከላቸው አድር ዘንድ መቅደስ ሥሩልኝ" ብሏል ዘጸ. 25÷8። ይህም የሚያመለክተው መቅደሱን መሥራት ከፈቃደ እግዚአብሔር የተገኘ እንጂ ፈጠራ እንዳልሆነ ግልጽ ያደርግልናል።



www.ethiopianorthodox.org

የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ የእውነት ቤት ነው። ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ይገልጻዋል "በዘገይ በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንዲገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ ቤቱም የእውነት አምድና መሠረት የሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ነው።" 1ጢሞ. 3፥15። ይህ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር የራሱ ማደሪያ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ይህ ቤት የሰማይ ደጅ ነው እንጂ ሌላ አይደለም ዘፍ. 28፥16 (Gate of Heaven)

እኛ እግዚአብሔር በሕንጻው ብቻ ይወሰናል አላልንም። ነገር ግን የአምልኮቱ ቤት ነው አልን እንጂ። ለዚህም እንዲሰራ ከእግዚአብሔር ትዕዛዝ ተሰጠ እንጂ አንዳችም በራሱ ፈቃድ የሠራ የለም።

ሕንጻ ቤ/ክርስቲያኑ ድንጋይ ነው፣ ጭቃ ነው አይባልም እቃው የተሰራበት ድንጋይ ሆነ፣ ጭቃ ሆነ፣ ሣር ሆነ የሚከብርበት የሚመለክበት ጌታ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በማቴ. 21፥7-13 እንደምናነበው ጌታ ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ ሕጻናት ያመሰግኑት ይዘምሩ ነበር። በዚህን ጊዜ ሕጻናቱን ዝም እንዲሉ ሲከለክሏቸው ድንጋዮችም እንደሚያመሰግኑት ተናግሯል። ይህም ብቻ አይደለም፤ ወደ መቅደሱ በገባ ጊዜ ሻጮችንና ለዋጮችን አግኝቶ በጅራፍ እየገረፈ እንዳስወጣቸውና "ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል የአባቴን ቤት የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት" ዮሐ- 2፥13 በማለት ገርፎ ሲያስወጣቸው እናያለን። ታዲያ ቤቱ የማይከብርበት ቢሆንሕንጻው የማያስፈልግ ቢሆን ጌታ አምላካችን በጅራፍ ገርፎ ባላስወጣቸው ነበር፤ ቤቱ ግን የእውነት አምድና መሠረት ስለሆነ



በጅራፍ ገርፎ አስወጥቶአቸዋል። ሁሌም እኛ ጌታን በምናከብርበት የክብር ቤቱ በመገኘት እናመልከዋለን። እንገዛለታለን ሥጋና ደሙን በመቀበል ከእርሱ ጋር ያለንን አንድነት እንገልጻለን።

በእግዚአብሔር ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ላይ ማንም ሊናገር አይችልም። ቤቱም የሚቃወም የእግዚአብሔርን ማደሪያ ቤት እየተቃወመ መሆኑን እንዲያውቅ እንወዳለን።

በእግዚአብሔር ፈቃድ እንዴት የእግዚአብሔር መቅደስ እንደተሰራ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እንመልከት።

- ሰሎሞንም በእስራኤል ላይ በነገሠ በአራተኛው አመት ዚፍ በሚባለው በሁለተኛው ወር የእግዚአብሔርን ቤት መሥራት ጀመረ 1ነገ. 6፥1። ለዘለዓለም የሚኖርበት ማደሪያ ቤት መሠራቱን ተናገረ 1ነገ. 8፥1-66።

## <u>ለምን እንሳለማለን (እንሰግዳለን)?</u>

በሕንጻው ቤተ እግዚአብሔር ተገኝተን እንሳለማለን፣ እንሰግዳለን ይኸውም ለባለቤቱ ያለንን ፍቅርና አክብሮት ለመግለጽ እንጂ የምናመልከው ማን እንደሆነ እናውቀዋለን። የመሳለማችን ወይም የመስገዳችን ምስጢር በቤተ እግዚአብሔር ፊት ስለሆነ የምንሰግደው ለእግዚአብሔር እንጂ ለሕንጻው አይደለም ወይም ለድንጋዩ አይደለም። ስለዚህ እስኪ መረጃ የሚሰጡንን ጥቅሶች እንመልከት።

- ኦሪት ዘጸአት 33፥10 ሕዝቡም ሁሉ የዳመናው ዓምድ በድንኳን ደጃፍ ሲቆም ያዩ ነበር፤ ሕዝቡም ሁሉ ተነስቶ እያንዳንዱ በድንኳኑ ደጃፍ ይሰግድ ነበርና መቅደስ ስለ ሆነ ድንኳን ነው እንሰግድም አላሉም በዛ ቤት በዛ ድንኳን ለከበረው ለእግዚአብሔር ሰገዱ እንጂ።
- ቤቱ እውነተኛ የእግዚአብሔር የክብሩ መገለጫ ቤት ስለሆነ እንሰግዳለን። ክብሩ በቤተ ክርስቲያን ላይ የተገለጠ ስለሆነ ለቤ/ክርስቲያን የጸጋ ስግደት እንሰግዳለን።
- 2ዜና መዋዕል 7፥1-3 "ሰሎሞንም ጸሎቱን በፈጸመ ጊዜ እሳት ከሰማይ ወረደ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና ሌላ መሥዋዕቱን በላ የእግዚአብሔርም ክብር ቤቱን ሞላ የእግዚአብሔርም ክብር የእግዚአብሔርን ቤት ሞልቶት ነበርና ካህናቱ ወደ እግዚአብሔር ቤት መግባት አልቻሉም። የእስራኤልም ልጆች ሁሉ እሳቱ ሲወርድ የእግዚአብሔርም ክብር በቤቱ ላይ ሲሆን ያዩ ነበር በወለሉም ላይ በግምባራቸው ወደ ምድር ተደፍተው ሰገዱ እርሱ መልካም ነውና ምህረቱም ለዘለዓለም ነውና ብለው እግዚአብሔርን አመሰገኑ" በማለት በግልጽ መጽሐፍ ቅዱስ የክብሩ መገለጫ የሰማይ ደጅ እንደሆነች በተለያዩ ቦታዎች እንደሚያስረዳን ልናስተውል ይገባናል። ክብሩ ከተገለጠበት በክብሩ ሥፍራ በማደሪያው ድንኳን የማንገኝበት የማንሰግድበት ምክንያት ምን ይሆን? እግዚአብሔር በማደሪያው ውሰጥ ነው፤ እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ በክብር ታቦቱ ላይ በቃል ኪዳኑ ላይ ነው። ይህን ደግሞ የምናገኘው በቅድስት ቤተ/ክርስቲያን ውስጥ ነው። ስለዚህ ለቤ/ክርስቲያን የጸጋ ስግደት እንሰግዳለን ለአምላካችን የአምልኮት ስግደትን በመገዛትና በፍርሃት እናቀርባለን። ለዘለዓለም ቅ/ቤ/ክርስቲያን የእግዚአብሔር የክብር ቤቱ ነች ለምን ቢባል ተሰባስበን የምናስቀድሰው፣ ቅዱስ ወንጌልን የምንማረው፣ የኃጢአት ሥርየት የምናገኘው፣ የምንጠመቀው በዚሁ ቤት ነውና።
- መጽሐፍ ሳሙኤል ካልዕ. 12፥20 "ዳዊትም ከምድር ተነስቶ ታጠበ ተቀባም ልብሱንም ለወጠ ወደ እግዚአብሔርም ቤት ገብቶ ሰገደ" ይላል። ይህ ደግሞ ከሀዘናችን በተጽናናን ጊዜ እግዚአብሔር ያደረገውን ሁሉ እንደፈቃዱ ሆነ ብለን በተቀበልን ጊዜ ሁሉ ከመኝታችን ተነስተን ጠዋት ልብሳችንን ቀይረን ለቤ/ክርስቲያን የሚገባ ልብስ ለብሰን ወደ ቤ/ክርስቲያን ሄደን መሳለም እንዳለብን ጭምር ያስተምረናል።
- መዝ. 5፥7 "እኔ ግን በምሕረትህ ብዛት ወደ ቤትህ እገባለሁ አንተንም በመፍራት ወደ ቅድስናህ መቅደስ እሰግዳለሁ።"
- መዝ. 28(29)፥2 "የስሙን ክብር ለእግዚአብሔር አምጡ በቅድስናው ስፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ" ይላል። ታዲያ ይህ የቅድስና ሥፍራ ቅ/ቤ/ክርስቲያን አይደለምን? የእያንዳንዳችን መኖሪያ የእኛ መከበሪያ እንደሆነ ሁሉ የእግዚአብሔር የቅድስናና የክብር ቦታው ቤ/ክ ስለሆነ መስገድ እንዳለብን ያስተምረናል።
- እኛ ቤት እያለን እግዚአብሔርን ቤት አይኑርህ አትክበር በምድር ላይ ሥፍራ አያስፈልግህም ብሎ እንደመቃወም ያህል ይሆናል። የቤ/ክርስቲያንን ማንነት መቃወም። ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር ቤት መጥቶ መስገድ የሚገባ ነው።
- መዝ. 95(96)፥9 "በቅድስናው ሥፍራ ለእግዚአብሔር ሰገዱ" ይላል ታዲያ ይህ የቅድስና ሥፍራ ቅ/ቤ/ክርስቲያን መሆኗ ለምን ይዘነጋል?

- መዝ. 131(132)፥7 "ወደ ማደሪያዎቹ እንገባለን እግሮቹ በሚቆሙበት ሥፍራ እንሰግዳለን።" ማደሪያው ቤቱ ታቦቱ እንደሆነ በዛ ሆኖ ሙሴን እንደሚያናግረው በዘጸ. 25፥22 ላይ ገልጾት የለምን?
- መዝ. 137(138)፥2 "በመላዕክት ፊት እዘምርልሃለሁ ወደ ቅዱስ መቅደስህ እሰግዳለሁ" በማለት በግልጽ የተናገረው ቅዱስ መቅደሱ (ቤ/ክርስቲያን) መሆኗን በመገንዘብ ልንሰግድ እንዲገባን መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል።
- ሕዝ. 46፥1-2 "አለቃውም በስተውጭ ባለው በር በደጅ ሰላሙ መንገድ ገብቶ በበሩ መቃን አጠገብ ይቁም ካህናቱም የእርሱን የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የደህንነቱን መስዋዕት ያቅርቡ እርሱም በበሩ መድረክ ይስገድ" ከደጅ መባችንን ስናቀርብ በበሩ ላይ ተደፍተን የምንሰግደው ይህን መመሪያ አድርገን ነው። ለቤ/ክርስቲያንም መስገዳችን በውስጡ ላደረ ለእግዚአብሔር መንፈስ መስገዳችን ነው።
- 1ኛ. ነገ. 9፥3 "... በፊቴ የጸለይከውን ጸሎትህንና ልመናህን ሰምቻለሁ፥ ለዘላለምም ስሜ በዚያ ያደርግ ዘንድ ይህን የሰራኸውን ቤት ቀድሻለሁ ዓይኖቼና ልቤ በዘመኑ ሁሉ በዚያ ይሆናሉ።" ለሕንጻው ቤተመቅደስ እግዚአብሔር የሰጠውን ይህን ታላቅ ክብር ማስተዋል ይገባል።
- ሐዋ. 18፥22 "ወደ ቂሣርያም በደረሰ ጊዜ ወጥቶ ለቤ/ክርስቲያን ሰላምታ ከሰጠ በኋላ ወደ አንጾኪያ ወረደ።" ይህ በርግጥም በአዲስ ኪዳን ለቤ/ክርስቲያን መስገድ ወይም ሰላም ለኪ ቅ/ቤተክርስቲያን፣ ቅ/ቤ/ክርስቲያን ሆይ ሰላምታ ይገባሻል ብሎ መስገድ የተገባ መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ አስተምሮናል።



ለዚህም ነው ቤቱ የእውነት አምድና መሠረት ነው ያለው 1ጢሞ. 3፥16።

## <u>በመሳለም ላይ የሚነሱ የመናፍቃን ጥያቄዎች</u>

1ኛ እኛ ነን እንጂ የሱ መቅደሶች ሕንጻው አይደለም።

2ኛ ለቤ/ክርስቲያን መስገድ ለድንጋይ መስገድ ነው። ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ ይላልና

ለአንደኛው ጥያቄያቸው መልስ 3ኛውን የቤተክርስቲያን ፍቺ ስንመለከት በደንብ ግልጽ ይሆናል። ነገር ግን በትክክል የቤ/ክርስቲያንን መንፈስ የለዩት አይመስለንም። እኛ የእግዚአብሔር መቅደስ ነን ማለት የአምልኮቱ ቤት አያስፈልግም ማለት አይደለም። ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ እንደሚባለው ሀሳቡ ፊጽሞ አልተረዱትም ለምሳሌ ለአንድ ተማሪ መጽሐፍ አለልህ እሱን አንብብ ት/ቤት መሄድ ምንም አይጠቅምህም እንደ ማለት ነው። ያም ሰው በክርስቶስ ክርስቲያን እንደመሆኑ የክርስቶስ አገልጋይ ነው ከተባለ በቃህ አትሂድ አታገልግል ብሎ እንደማገድ ነው። ወይም ወታደርን ያለ መሣሪያ ጦር ሜዳ እንደመላክ ነው። ወታደሩን ብቃቱ አለህ መሣሪያ አያስፈልግህም እንደማለት ነው። ግን እንዲህ አይደለም እኛ የእግዚአብሔር ቤ/መቅደስ መሆናችን እርግጥ ነው ሕንጻ ቤተመቅደሱ ግን የአምልኮ ሥፍራ ነው። የአምልኮት ቤት ነው። "በመካከላችሁ አድር ዘንድ መቅደስ ሥሩልኝ" እንዳለው። ዘጸ. 25፥8

ለሁለተኛው ጥያቄያቸው መልስ የሚሆነው ከኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ ያለው የእርሱ ያልሆኑትን ከእርሱ ጋር ተቃዋሚ የሆነውን ነው እኛ ቤ/ክ አምላክ ናት አላልንም። ቤ/ክርስቲያን የእግዚአብሔር የክብር ማደሪያ ናት አልን እንጂ። ስለዚህ የሚቃወሙበት ጥቅስ አግባብ ያለው ቢሆን ጥሩ ነው እኛ አምላክ ናት ብለን ቤ/ክርስቲያንን ስለማናመልክ ጥያቄው ወይም ወቀሳው ሕጋዊ አይደለም። ለድንጋይ አንሰግድም ለእግዚአብሔር እንጂ። ይኸውም በ1ኛ ነገ. 9፥3 ላይ እንደተገለጸው የእግዚአብሔር አይኑም ልቡም በቤተክርስቲያን ላይ ነውና እንሰግዳለን፤ እንሳለማለን።

## ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ ቅባት የከበረች ነች

- ዘፍ. 28፥18 "ያዕቆብም ማልዶ ተነሣ ተንተርሶት የነበረውንም ድንጋይ ወስዶ ሐውልት አድርጎ በላዩም ዘይትን አፈሰሰበት ያዕቆብም ቤቴል አለው የእግዚአብሔር ቤት ማለት ነው።"

## 2ኛ የክርስቲያኖች አንድነት ቤተ ክርስቲያን ይባላል።

ይህ የክርስቲያኖች አንድነት በጥንት ጊዜ ጽርዓውያን "ካሌዎ ካሎ" ከሚለው ግሳቸው አውጥተው አክሊሲያ ይሉታል። ፍቺው ጽውዕት ኅሪት ማለተ ነው። ይህን አገላለጽ በብዙ፥ ቤተ ክርስቲያን ዘግብጽ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ማህበር የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ማህበር በማለት ብዙ ጊዜ ይገለጻል። 1ኛ. ጴጥ. 5፥13።



ለምሳሌ ይህን አንድነት የሚገለጹትን ጥቅሶች እንመልከት።

- ሰው ቢበድል መጀመሪያ ለብቻው እንዲመከር በኋላም ሁለት ሦስት ሆነው እንዲመክሩት እነሱን ግን ባይሰማ ለቤተክርስቲያን ንገራት ይላል ማቴ. 18፥17 ይህ አንድነቱን (ጉባኤውን) ይገልጻል።
- በዓላተ እግዚአብሔርን ለማክበር የተሰበሰቡ እስራኤላውያን አክሊሲያ የሚለውን ስያሜ አግኝተዋል። ዘዳ. 9፥10
- ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል በቃል 114 (መቶ አስራ አራት) ጊዜ በአዲስ ኪዳን ተገልጾአል። ከእነዚህም የተወሰኑት የክርስቲያኖች አንድነት (Community) የሚያሳዩ ናቸው።

## 3ኛ) እያንዳንዱ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን ይባላል።

ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንዲህ በማለት ይገልጻዋል። "ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ቅዱስ ነውና፥ ያውም እናንተ ናችሁ።" 1ቆሮ. 3፥17 ይህ ቃል የእግዚአብሔር ቤተመቅደሶች መሆናችንን ያመለክተናል። ይህ ማለት ግን ሕንጻ ቤተክርስቲያን የአምልኮ ስፍራ አያስፈልግም ማለት አይደለም። ስለዚህ ስለ ቤተክርስቲያን ያለው ትምህርት ከብዙ በጥቂቱ ይህን ይመስላል።

በተቃዋሚዎች በኩል የክርስቲያኖች አንድነት በሚለውና እያንዳንዱ ሰው ቤተ ክርስቲያን ይባላል በሚለው ላይ የሚያነሱት ጥያቄ ስለሌለ በዚሁ ይበቃናል።

www.ethiopianorthodox.org

# ስዕል

ሥዕል እንደ ታቦት በኦርየንታል ኦ/ተ/ቤተክርስቲያናት ያለና የሚሰራበት ነው። ስዕል እግዚአብሔር ጋር የተያያዘና በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን የሚሰራበት ነው ስዕል በእግዚአብሔር ፊት የተሰጠ ሕግ ነው። ይኸውም ለሙሴ በታቦተ ሕጉ በጽላት ኪዳኑ ላይ ስዕለ ኪሩብን እንዲስል ታዞ ነበር ዘጸ. 25፥18፤ ዘጸ. 37፥7፤ ነገ. ቀዳ. 6፥33። እግዚአብሔር እንዲሁ ለነቢዩ ሕዝቅኤል የኢየሩሳሌምን ከተማ ስዕል ሳልባት ብሎታል። ሕዝ. 4፥1-3።

በብሉይ ኪዳን የመጀመሪያ ሰዓሊ ሙሴ ነው። ሰሎሞንም የመጀመሪያው ቤተ መቅደስ በሠራ ጊዜ ስዕለ ኪሩብን ስሏል። ስዕል በቤተክርስቲያን አጀማመሩ ከዚህ ለየት ይላል። ስዕል ነገሥታት ክርስቲያኖችን በሚያሳድዱበትና በሚገሉበት ወቅትና ዘመን በዋሻ በካታኮምብ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ ለአዲስ አማኒያን ማስተማሪያ የሚሆኑ በቂ መጻሕፍት ባለመኖራቸው ከቅዱሳት መጻሕፍት ታሪኮች በስዕል እየሳሉ ያስተምሩ ነበር። እንዲሁም የሃይማኖት ወንድሞቻቸው ሰማዕታት ለክርስቶስ በመመስከራቸው ስለ ተገደሉ አገዳደላቸውን በስዕል ሥለው ያስቀምጡት ነበር እነዚህ ሥዕሎች ድሮ ክርስቲያኖች በተሰደዱባቸው ዋሻዎች በአመድና በከሰል ተስለው ይገኛሉ።

በስዕል ምክንያት በ8ኛው መቶ ክ/ዘመን ክርስቲያኖች በሦስት ተከፍለው ነበር።



ሀ) አንዳንድ ክርስቲያኖች ስዕልን በጣም ከመውደዳቸው የተነሣ ስዕሎች አማልክት ናቸው እስከ ማለት ደርሰዋል። እነዚህም ኢኮኖሣትሪያ ይባላሉ።

ለ) አንዳንዶች ደግሞ ስዕሎች ፈጽመው አያስፈልጉም ሥዕሎች ማጥፋት አለብን የሚሉ ፀረ-ስዕሎች ናቸው። እነዚህም ኢኮኖማኺያ ይባላሉ።

ሐ) ሌሎች ክርስቲያኖች ግን ሥዕሎች አማልክት ናቸው ሣይሉ፤ ማጥፋት አለብንም ሳይሉ ትክክለኛውን ትምህርት ይዘው ሥዕሎችን የሚወዱ የሚያከብሩ ናቸው። ሆኖም የቤዛንታይን መንግሥት ኢኮኖማኺያን ስለደገፈ ቤ/ክርስቲያን ለብዙ ዘመናት ስትጠብቃቸው የነበሩ ሥዕሎች በሙሉ ተቃጠሉ። ሆኖም ሥዕሎቻችን መጥፋት የለባቸውም የሚሉ ክርስቲያኖች ጩኸታቸው ስለ በረከተ የሮማና የቤዛንታይንን መንግሥት ሊያናጋው ሆነ በዚህ ግዜ በ787 ዓ.ም. በኒቂያ ጉባኤ ተደርጎ ስለ ስዕሎች አስፈላጊው ትክክለኛው ቀኖና ተደነገገ።

በምስራቅ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ሥዕሎች የሚሣሉት በቀለም ነው። ላቲኖች (ካቶሊኮች) ግን በቅርጽ ነው። ይህን ያህል ስለ ስዕል አመጣጥና ታሪክ ከገለጽን ስዕል በቤተክርስቲያናችን ያለውን አስተዋጽኦ እንመልከት።

1ኛ) ወንጌላዊ መልዕክት አለው። ይኸውም የጌታን የስቅለት ሥዕል ስናይ እንዴት ስለእኛ እንደተሰቀለ ስለሚያሳየን ወንጌሉ ላይ የተጻፈውን መልዕክት በሥዕል ገልጦ ያሳየናል።

2ኛ) በሥዕሉ አማካይነት ለሥዕሉ ባለቤት ያለንን ክብርና ፍቅር እንገልጽበታለን።

3ኛ) ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ ለማይችሉና ቅዱሳት መጻሕፍት እጥረት በነበረበት በካታኮምብ (ግበበ ምድር) ውስጥ በማስተማሪያነት አገልግሏል። አሁንም እንዲሁ ማንበብ የማይችሉ ሁሉ ሥዕሉን በማየት መልዕክቱን በልባቸው ያኖሩበታል።

4ኛ) ትምህርታዊ ሥራ

5ኛ) የቤተክርስቲያን የማስተማር ሥርዐትን ያሳየናል

6ኛ) በቀለማቸው ውስጥ የሚታየው የወንጌል መንፈሳዊ ምስጢር

ይኸውም በስዕሉ ውስጥ የሚታዩ የተለያዩ ቀለማት የራሳቸው ምሥጢር መልዕክት አላቸው። ለምሳሌ በአረንጓዴ በቀይ በቢጫ ቢጫል

- አረንጓዴው ለአዳም አምላክ የሰጠውን ተስፋ ያሳያል
- ቀዩ የመንፈስ ቅዳስ በእሳት አምሳል መውረድ ያሳያል
- ቢጫ አምላክ ሰው ሆነ ሰው አምላክ ሆነ የሚለውን ሥግው (ሥጋ የለበሰው) ክርስቶስን ያሳየናል።

ወይ በጥቁር፣ በቀይ፣ በነጭ፣ ቀለም ተስሉ ብናየው የራሱ ትርጉም አለው።

- ጥቁሩ አብ አስቀድሞ በሰው ልጆች ኃጢአት አዝኖ እንደነበር ያሳያል፣
- ቀይ ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ እንዳዳነን ያሳየናል።
- ነጭ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን በርግብ አምሳል መውረዱን ያሳየናል።



7ኛ ምዕመናን (አማኞች) የሚጠባበቁትን አዲስ ተስፋ ማሳያ ነው።

ብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን የቅዱሳት ሥዕላት መሠረት የእግዚአብሔር ቃል ነው። እስኪ በሁለቱ ኪዳናት ያለውን የስዕል እውነታ እንመልከት።

## ስዕል በብሉይ ኪዳን

በዘመነ ብሉይ በመጀመሪያ ጊዜ ሥዕለ ኪሩቤልን እንዲያዘጋጅ የታዘዘው ነቢየ እግዚአብሔር መራሔ እስራኤል የነበረው ሙሴ ነበር። የነገረውም ከነ አሠራሩ ጭምር ነው። ካዘጋጀውም በኋላ ስዕሉን በክብር በታቦቱ አጠገብ እንዲያስቀምጥ ነግሮታል። በመጨረሻም በዚያም ከአንተ ጋር እገናኛለሁ የእስራኤልንም ልጆች ታዝዝ ዘንድ የምሰጥህን ነገር ሁሉ በምስክሩ ታቦት ላይ ባለው በሁለት ኪሩቤል መካከል በሥርየት መክደኛውም ላይ ሆኜ እነጋግርሃለሁ ብሎታል። ዘጸ. 25፥21-22

- ዘኁ. 7፥89 "ሙሴም ወደ መገናኛው ድንኳን እርሱን ለመነጋገር በገባ ጊዜ በምሥክሩ ታቦት ላይ ካለው ከሥርየት መክደኛ በላይ ከኪሩቤልም መካከል ድምጽ ሲናገረው ይሰማ ነበር።" እርሱም ይናገረው ነበር ይላል ይህም የሥዕልን ታላቅ ክብር ያሳየናል። እግዚአብሔርም እንደተናገረው ማድረጉን ይገልጽልናል።
- ዘኁ. 23፥19 "እግዚአብሔር ይዋሽ ዘንድ ሰው አይደለም" ይለናል።



www.ethiopianorthodox.org

- ዘጸ. 21፥1 ላይ በአሥሩም የቤተመቅደሱ መጋረጃዎች ላይ ምስለ ኪሩቤን እንዲሥል የሰጠው ትዕዛዝ ሥዕል በእግዚአብሔር ዘንድ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ የሚያሳየን ነው።
- 1ኛ ነገ. 6፥21-29 "... በቤቱም ግንብ ዙሪያ በውስጥና በውጭ የኪሩቤልና የዘንባባ ዛፍ የፈነዳም አበባ ምስል (ሥዕል) ቀረጸ" ይላል። ይህም ንጉሡ ሰሎሞን ያደረገው እግዚአብሔር ለሙሴ እንደነገረው ሥዕለ መሳል ሃይማኖታዊ ግዴታው በመሆኑ ነው።
- 2ኛ ዜና. 7፥11-12 "ሰሎሞንም የእግዚአብሔርን ቤትና የንጉሡን ቤት ጨረሰ በእግዚአብሔር ቤትና በራሱ ቤት ይሠራው ዘንድ በልቡ ያሰበውን ሁሉ አከናወነ። እግዚአብሔርም ለሰሎሞን በሌሊት ተገልጦ እንዲህ አለው ጸሎትህን ሰምቻለሁ ይህም ስፍራ ለራሴ ለመሥዋዕት ቤት መርጫለሁ።" ብሎታል። ይህ የሚያሳየን እግዚአብሔር ሁሉንም ወዶ ሲቀበልልት ሥዕሉን አያስፈልግም ወይም ምን ያደርጋል አላለውም። ትዕዛዙ ከእግዚአብሔር የመጣ ስለሆነ እግዚአብሔር ተቀበለው እንጂ እንደውም ለራሴ የመሥዋዕት ቤት መርጫለሁ ነው ያለው ስለዚህ ሥዕል በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ታላቅ ክብርና መልዕክት አለው። በእግዚአብሔርም የተፈቀደ ነው።
- ዘኁ. 27፥8-9 "እባብን ሥርተህ (የእባብን ሥዕል ቀርጸህ) በዓላማ ላይ ስቀል የተነደፈውም ሁሉ ሲያዩተ፥ በሕይወት ይኖራል።" ወዲያው የእባቡን ሥዕል በነሐስ ሠርቶ ዓላማ ላይ ሰቀለ በማየት እንዴት መዳን ይቻላል? ብለው ስላልተጠራጠሩ የተሰቀለው እባብ አይተው ድነዋል። ዛሬም ባለመጠራጠር የሚቀበለው ቢኖር ይድንበታል።
- ሕዝ. 4፥1-3 "አንተም የሰው ልጅ ሆይ ጡብን ወስደህ በፊትህ አኑራት የኢየሩሳሌምንም ከተማ ስዕለ ሳልባት ከበባት ምሽግም



ሥራባት ይህም ለእስራኤል ቤት ምልክት ይሆናል።" ይህ ሥዕል በእስራኤል ቤት ምልክት ሆኖ መጨው የእስራኤል ልጆች ሁሉ እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ያላትን ግንኙነትና እምነት ኢየሩሳሌምም እንዴት ሆና ትኖር እንደነበር የተማሩበት እንደነበር ታሪክ ያስረዳል። ሥዕል ታላቅ የሆነ የመልዕክት ማስተላለፊያ ነው። በተጨማሪም እንዲሁ በሕዝ. 9፥3 እና ሕዝ. 10፥1 ላይ ገልጦልናል።

## ስዕል በአዲስ ኪዳን

ለአዲስ ኪዳን ሥዕል መሠረቱ፥ የብሉይ ኪዳን ሥዕል ነው። ምክንያቱም ለአዲስ ኪዳን መሠረቱ፥ ብሉይ ኪዳን ነውና። ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ሠላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር በዚህች ምድር ላይ በተመላለሰ ጊዜ ሥዕለ ኪሩብ ካለበት ቤተመቅደስ የተለየበት ጊዜ አልነበረም። ለምሳሌ፡-

- ጌታ በተወለደ በአርባ ቀኑ እናቱ፥ ድንግል ማርያም ወደ ቤተመቅደስ ወስዳዋለች። ሉቃ. 2፥22-24
- የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ በሆነው ጊዜም ከእናቱ፥ ከድንግል ማርያምና ከጠባቂዋ ከዮሴፍ ጋር የፋሲካን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ ሄዷል። ሉቃ. 2፥41-50
- ዕለት ዕለትም ስዕለ ኪሩብ ባለበት ቤተመቅደስ ተገኝቶ አስተምሯል። ቤተመቅደሱንም የአባቴ ቤት ብሎታል። ማቴ. 26፥55፤ ዮሐ. 18፥20፤ ዮሐ. 2፥13
- በሽተኞችን በመቅደስ ውስጥ ተገኝቶ ፈውሶአቸዋል። ማቴ. 21፥12 ይህ ሁሉ የተደረገው ስዕለ ኪሩቤል ያለበት መቅደስ

ውስጥ ነው። ባያስፈልግ ኖሮ ስዕሎች አግባብ እንዳልሆኑ ባመለከታቸው ነበር።

- በመቅደስም የሚሸጡትንና የሚገዙትን ሁሉ አወጣ የገንዘብ ለዋጮችንም ገበታዎች፣ የርግብ ሻጮችንም ወንበሮች ገለበጠና "ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፎአል (ኢሳ. 56÷7) እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችኋት" (ኤር. 7÷11) አላቸው። ማቴ. 21÷13።
- ሐዋ. 3÷1 ላይ እንደምናነበው ጴጥሮስና ዮሐንስ ለጸሎት ዕለት ዕለት በመቅደስ እየተገኙ በስዕል ፊት ተደፍተው ይጸልዩ ነበር። በመጨረሻው በገላትያ መልዕክት ምዕ. 3÷1 ጀምሮ እንደምናነበው በፊታቸው ተሰቅሎ የሚታየውን ኢየሱስ ክርስቶስን ባለማስተዋላቸው ወቅሶአቸዋል። የስዕል አጠቃላይ መልዕክት ወንጌልን ሰማዕታትን የጌታን ክብር እንዴት እንደነበር የሚያሳይ መሆኑ ሊታወስ ይገባዋል። ይህም በግበበ ምድር (ካታኮምና) የተጀመረው የሥዕል ሥራ ዛሬ ለምናየው በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለተሳሉ የቤ/ክርስቲያን ስዕላት መሠረት የጣለ ነው።

## <u>በስዕል ፊት ቆሞ መጸለይ</u>

በስዕል ፊት ቆሞ መጸለይ ሥዕሉን አምላክ ነው ብሎ ማምለክ አይደለም። ለሥዕሉ ባለቤት ያለንን ፍቅርና አክብሮት ለመግለጽ ነው እንጂ። ከሥዕሉም ባለቤት በረከት ለማግኘት እንጂ፤ እንዲሁም በመንፈስም ድልድይ ሆኖ ከሥዕሉ ፊት ቆመን በምንጸልይበት ጊዜ ይኸንን በረከት እናገኛለን።



ይህም በእምነት የሚገኝ በረከት ነውና ማጤን ወሳኙ ጉዳይ ነው። "የለመነውን ሁሉ እንደተቀበልን ብናውቅ ብናምን ይሆንልናል" ይላል። ማር. 11÷24 እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ በ1ኛ ዮሐ. 5÷14 "በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው እንደ ፈቃዱ እንዳች ብንለምን ይሰማናል።" ይላል ይህ እውነት በልባችን ካለ በሥዕል ፊት ቆመን መጸለይ ከአምላክ ጋር የመገናኛው የመሰብሰቢያ አንዱ መንገድ እንጂ ከጣኦት አምልኮ ጋር ፍጹም አይገናኝም።

እግዚአብሔር በወደደው ሁሉን ሊያደርግ የሚችል አምላክ ነው። የልብ መደንደን ካልሆነ በስተቀር በሚያስደንቅ ጥበቡ በረከትንና ተአምራትን ያደረገባቸውን የቤተክርስቲያንን ሀብታት ማስተዋል ይገባል።

- ዘጸ. 4÷17 ይህችንም ተአምራት የምታደርግባትን በትር በእጅ ይዘሀት ሂድ የሙሴ በትር እንጨት ብትሆንም ድንቅ ድንቅ ተአምራትን አድርጋለች። እንጨት ናትና እንዴት ተአምራት ይሠራል እንጨት ነው ተብሎ ሊናቅ እንደማይችል ሁሉ በስዕላትም ዘንድ ታላላቅ ተአምራት ያደርጋል።
- 2ኛ ነገ. 2÷8 ኤልያስም መጎናጸፊያውን ወስዶ ጠቀለለው ውኃውንም መታ ወዲህና ወዲያም ተከፈለ ሁለቱም በደረቅ ተሻገሩ የኤልያስ መጎናጸፊያ ጨርቅ ብትሆንም የዮርዳኖስን ወንዝ ለሁለት ከፍላለች። ይህን ድንቅ እንዴት ጨርቋ አደረገው ብለን አንቃወምም ነገር ግን እግዚአብሔር በጨርቋ ላይ ድንቁን አደረገ። ይህም እውነት እንዲሁ በሥዕል ላይ ይፈፀማል።

- 2ነገ. 6፥1-7 "... የእግዚአብሔርም ሰው የወደቀው ወዴት ነው? አለ ሥፍራውን አሳየው እንጨትም ቆርጦ በዚያ ጣለው ብረቱም ተንሳፈፈ።" እንግዲህ ምን እንላለን መስመጥ የነበረበትን ብረት ያንሳፈፈው ቅርፊት እግዚአብሔር ድንቅ ካደረገበት። የከበደውን የሚያቀል አምላክ በስዕሉ ፊት ቆሞ መጸለይማ እንዴት እጅግ አብልጦ በረከትና ድንቅ አያስፈጽምም?
- ሐዋ. 5፥15-16 "ስለዚህ ጴጥሮስ ሲያልፍ፡ ጥላውም ቢሆን ከእነርሱ አንዱን ይጋርድ ዘንድ ድውያንን ወደ አደባባይ አውጥተው በአልጋና በወስካ ያኖሯቸው ነበር። ... ሁሉም ይፈውሱ ነበር።" እንዲሁ በእምነት ሥዕሉን የዳሰሱ ሁሉ ይፈወሳሉ። በሥዕሉም ፊት ቆመው በመጸለያቸው ይባረካሉ።
- ሐዋ. 19፥12 "እግዚአብሔርም በጳውሎስ እጅ የሚያስገርም ተአምራት ያደርግ ነበር። ስለዚህም ከአካሉ ጨርቅ ወይም ልብስ ወደ ድውዮች ይወስዱ ነበር ደዌያቸውም ይለቃቸው ነበር።"

ከዚህ በላይ በአጭሩ ለመግለጽ እንደሞከርነው ቅዱሳን የነፍሳቸው ቅድስና ለሥጋቸው የሥጋቸው ቅድስና ደግሞ ለምርኩዛቸው፣ ለጥምጥማቸው፣ ለቀሚሳቸውና ለጥላቸው ተርፎ ድንቅ ድንቅ ተአምራትን አድርገዋል። በዚሁ መሠረት ቅድስናቸው ለሥዕሎቻቸውም ጭምር የተረፈ በመሆኑ በሥዕሎቻቸው ተአምራትን ያደርጋሉ። ለምሳሌ ነቢዩ ኤልያስ በእሳት ሰረገላ ካረገ በኋላ ደቀመዝሙሩ ኤልሳዕ በመምህሩ በኤልያስ መጎናፀፊያ ተአምራት ተደርጎለታል። 2ኛ ነገ. 2፥14 ከኤልያስ ተርፎ ለኤልሳዕ ያደረገው እግዚአብሔር የእሱ ድንቅ ሥራ ነው። ዛሬም በስዕሎች



በረከት ቢተላለፍ ቢደርሰን ተመስገን ልንል እንጂ ፈጽሞ የሚቃወሙት ባልሆነ ነበር። ከዚህም የምንረዳው ቅዱሳን በአጸደ ሥጋ ባይኖሩም የእነርሱ በሆነ ነገር ሁሉ ማለትም በሥዕሎቻቸው አማካይነት ለእኛ ተአምራት እንደሚደረግልን ነው። ሥዕሎቹ ከዚህ አልፈው ቃል አውጥተው የሚናገሩበት ጊዜ አለ። ምክንያቱም እግዚአብሔር የበለዓለምን አህያ እንኳ እንደ ሰው አናግሯል። ዘኍ. 22፥28፣ የቢታኒያን ድንጋዮች አዘምሯቸዋል ሉቃ. 19፥40።

## ለስዕል የሚገባ የጸጋ ስግደት

የቅዱሳን ሥዕሎች ከዓለማውያን ሥዕሎችና ከጣዖታት ምስሎች ተለይተው የተቀደሱ በመሆናቸው ይሰገድላቸዋል። ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ፍጹም ቃል ኪዳን የጻድቁ በረከት እና አማላጅነት የሚገለጥበት እንዲሁም ጻድቁን አቅርቦ የሚያሳየን ያ ሥዕል ቅዱስ ስለሆነ ስግደት ይገባዋል። ለምሳሌ አንድ ልጅ የሞተበትን አባቱን በትልቁ ፎቶውን አሳድጎ ይሰቅለዋል። ይኸውም ፍቅሩን ለመግለጥ ነው። እኛም የምንሰግደው ለሥዕሉ ባለቤት ያለንን ፍቅር ለመግለጽ መሆኑ ሊታወቅ ይገባዋል።

ሙሴና አሮን ወደ መገናኛው ድንኳን መጥተው በታቦቱና በሥዕለ ኪሩብ ፊት እየሰገዱ ከእግዚአብሔር ትዕዛዝ ይቀበሉ ነበር። የእግዚአብሔርም ክብር የሚገለጥላቸው በዚህ ጊዜ ነው። ዘኁ. 16፥45፣ 26፥6

እግዚአብሔር በኦሪቱ አትስገድላቸው ያለው ለአሕዛብ ጣዖታት ምስሎች እንጂ ለቅዱሳት ሥዕላት አይደለም። ይህን ለማስረዳት እስራኤላውያን ሙሴ ሕግ ሊቀበል በወጣ ጊዜ ጣኦት ሲያመልኩ ቀስፏቸዋል። ብዙ ጊዜም እንደ አሕዛብ ጣኦት ሠርተው ሲያመልኩ ይቆጣቸውም ነበር። መሳ. 2፥11-14፣ 2ነገ. 17፥7-18፣ 21፥11-12። ስጢም በተባለ ቦታ ሃያ አራት ሺህ እስራኤላውያን በመቅሰፍት የረገፉት ብዔል በተባለ ጣኦት ፊት በመስገዳቸው ነው። ዘኁ. 24፥1 በሥዕለ ኪሩቤል ፊት በሰገዱበት ጊዜ ግን አንድም ቀን አልገሰጻቸውም፣ አልተቆጣቸውም። ይህም በሥዕል ፊት ቆሞ መጸለይ መስገድ የሚገባ መሆኑን ያሳየናል።

## መስቀል

መስቀል በኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ እንደ ታቦትና ስዕል ከፍተኛ ክብርና ቦታ ያለው ነው።

## የመስቀል ታሪካዊ አመጣጥ
## (The Historical background of Cross)

ሰውን በመስቀል ላይ መስቀል የተጀመረው በፋርስ አገር ነው፤ ይኸውም በፋርስ አገር አምልኮት የመሬት አምላክ (ኦርሙዝድ) ስለሆነ ፋርሶች አንድ ወንጀለኛ በሀገራቸው ሲገኝ ቅጣቱን በመሬት ላይ የተቀበለ እንደሆነ ኦርሙዝድ ጣኦታቸው የሚረክስባቸው ስለሚመስላቸው ቅጣቱን በስቅላት ይፈጽሙት ነበር። ይህ የፋርሶች ሕግ እንደ ሕግ ሆኖ ወደ ሮም ሄደ። ሆኖም



www.ethiopianorthodox.org

በብሉይም በመስቀል የሚቀጡ ብዙ ውንዛን ነበሩ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በምን ዓይነት ሞት እንዲሞት ሲያስረዳ፡-

- ዮሐ. 3፥14 "ሙሴ እባብን በበረሃ (በምድረ በዳ) እንደሰቀለ የሰው ልጅ እንዲሁ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል።"
- ዮሐ. 12፥32 "እኔ ከምድር ከፍ ከፍ ያልኩ እንደሆነ ሁሉን ወደእኔ እስበዋለሁ።" ይላል ከፍ ብሎ እንደሚሰቀል ሲያመለክተን ርግማንንም እንደተሸከመ ሲገልጥ እንዲህ ይላል።
- ገላ. 3፥13 በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ እርግማን ሆኖ ከእርግማን ዋጀን ይላል። ርጉም በተባለው ተሰቅሎ በመስቀሉ ሞት እኛን ከርግማን ዋጀን ከሞትም አዳነን። መስቀል ከክርስቶስ በፊት የመቅጫና የእርግማን ምልክት ሲሆን በክርስቶስ ግን የደህንነታችን አዋጅ የታወጀበት ሰላማዊ ዙፋን ነው። ሞትና ዲያብሎስ ድል የተደረገበት የድል ምልክት ነው። ሥጋውና ደሙ የተፈተተበት ቅዱስ መስዋዕት ነው። ቄሱ የሚባርክበት የምናማትበበት አጋንንትን የምናሳድድበት ቅዱስ መስቀል ነው። መዝ. 59፥3 "ለሚፈሩህ ምልክት ሰጠሃቸው" ይላልና ለእኛ የተሰጠን ምልክት ቅዱስ መስቀሉ ነው። ይህም ለሚፈሩት ነው።

## መስቀል የብሉይ ኪዳን ምሳሌዎች አሉት

1. ሙሴ የፈርኦንን መስግላን ድል ያደረገበት በትር፣
2. የኖህ መርከብ የተሠራችበት እንጨት፤ ይህ የኖህ መርከብ የተሠራበት እንጨት መርከብ ሆኖ ነፍሳትን እንዳተረፈ

በእንጨት መስቀል ላይ የተሰቀለው የዓለሙ ገዥ ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን በመስቀል መሰቀሉን ያመለክታል። እኛንም አዳነን መርከቧ ነፍሳትን እንዳዳነች ማለት ነው።

3. በትረ አሮን
4. የሙሴ አርዌ በትር

መስቀል ለእኛ ለክርስቲያኖች ኃይላችን፣ ጽንዐችን፣ ቤዛችን፣ መድኃኒታችን ነው። "የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለኛ ለምንድን የእግዚአብሔር ኃይል ነው።" 1ቆሮ. 1፥18። ለቅዱስ መስቀል ክብርና ስግደት ይገባል። "እግሮቹ በሚቆሙበት ሥፍራ እንሰግዳለን" መዝ. 131፥7።

## በመስቀል ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች

1. ኢየሱስ የተሰቀለው ቀጥ ባለ እንጨት ላይ እንጂ በተመሳቀለ እንጨት ላይ አይደለም (ጆሆቫ ዊትነስ)።
2. ኢየሱስ የገደለውን መስቀል አናከብርም። እርሱን ማክበር ጠላትን መውደድ ነው፣ ጣኦት ማምለክ ነው (ፕሮቴስታንት)።

## ለመጀመሪያው ጥያቄ መልስ የሚከተለው ነው።

ኢየሱስ የተሰቀለው በተመሳቀ እንጨት ላይ ነው። መስቀል ማለት በአማርኛው ትርጉም ከአንድ ቦታ መስመር ወደ ሌላ መስመር የሚሄድ የተመሳቀለ ማለት ነው። በእንግሊዝኛው እንዲሁ Cross /Kruds us/ mark made by drawing one line across another ይላል። በጣም ግልጽ የሆነ ነው። አንድ እንጨትና መስቀል ማለት ልዩነት አለው። አሁን እያወራን ያለነው ስለተመሳቀለው መስቀል



www.ethiopianorthodox.org

እንጂ አንድ ግንድ ላይ ስለተፈጸመ ድርጊት አይደለም። እስኪ መረጃ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንመልከት።

- ማቴ. 27፥32 "ስምዖንም መስቀሉን ይሸከም ዘንድ አስገደዱት" አንድ ግንድ እንዲሸከም አላስገደዱትም። መስቀል አለን እንጂ፥ መስቀያ ቢለን ኖሮ አንድ እንጨት ይሆን ነበር ቅርጹን ለይቶ ሲናገር መስቀል አለ።
- ማር. 15፥29-30 "ከመስቀል ወርደህ ራስህን አድን" አሉ ከግንዱ ላይ ወይም ከእንጨት ወርደህ አላሉም። የተሰቀለው በተመሳቀለ እንጨት ላይ ስለሆነ ከመስቀል ውረድ አሉት።
- ዮሐ. 19፥17-19 "መስቀሉን ተሸክሞ" የሚለው አገላለጹም ይህንኑ ያመለክታል።
- ቆላ. 1፥20 "በመስቀል ባፈሰሰው ደሙም" በመስቀል ላይ ተሰቅሎ የተሰቀለው ቀጥ ባለ እንጨት ላይ ሳይሆን በመስቀል ላይ ነው። ዕብ. 12፥1-2 ተመልከት።
- ገላ 6፥14 "እኔ ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም ከተሰቀልኩበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ የምመካበት ነገር የለኝም።" ይላል መስቀል ኃይላችን፣ ጽንዐችን የምንለውም ለዚህ ነው። እንግዲህ በዚህ መሠረት ክርስቶስ የተሰቀለው በተመሳቀለ እንጨት እንጂ በግንድ ወይ ቀጥ ባለ እንጨት አለመሆኑን ያስረዳናል።

የይሆዋ ምስክሮች እንደ መረጃ የሚያቀርቧቸውን ጥቅሶች እስኪ እንመልከት።

- 1ጴጥ. 2፥24 "ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ" ስለሚል እንጨት ማለት ግንድ ነው በማለት ይተረጉሙታል።

ነገር ግን እውነቱ ይሄ ነው እንጨት የሚለው ቃል ማቴሪያሉን ዕቃውን ለይቶ ነገረን እንጂ ግንድ አላለንም። ብረት አይደለም ወርቅ አይደለም ወይም ሌላ አይነት ዕቃ አይደለም። የተሰቀለው በእንጨት ነው። በብረት ላይ ወይም በወርቅ ላይ አልተሰቀለም ለማለት ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ገላ. 3፥13 የሚገልጸው በምን እንደተሰቀለ ዕቃውን ይገልጻል እንጂ ግንድ አላለንም።

ለምሳሌ በመጽሐፈ አስቴር ላይ የምናገኘው ሃማ የተሰቀለው በግንድ ላይ ነው። እስኪ ጥቅሱን እንመልከት። ሐማንም ለመርዶክዮስ ባዘጋጀው ግንድ ላይ ሰቀሉት በዚያም ጊዜ የንጉሡ ቁጣ በረደ አስቴር 7፥10 በመስቀል ላይ ሰቀሉት አላለም በተመሳቀለ እንጨት ላይ ስላልተሰቀለ በአንድ ወጥ ግንድ ላይ ስለተሰቀለ በግንድ ላይ ሰቀሉት አለ እንጂ። ስለዚህ በማስተዋል ሁሉንም ማየት ይኖርብናል። ግንድ አንድ ወጥ እንጨትና መስቀል የተለያየ ነውና።

ለሁለተኛው የፕሮቴስታንቶች አባባል። ደግሞ ቀደም ብለን የገለጽናቸውን ጥቅሶች በቂ መልስ የሚሰጡ ስለሆኑ በጥንቃቄ ይመልከቷቸው።



## ከተለያዩ ማዕድናት የሚሰራው መስቀል ትርጉም

መስቀል ከተለያዩ ማዕድናት ሊሰራ ይችላል፤ መስቀሉ የሚሰራባቸው ማዕድናት የራሳቸውን ባህርያት እንዳላቸው ሁሉ ምሳሌውን ለመግለጽ ብቁ ናቸው ብለው አባቶች ያስቀመጡትን ማየት ይገባል።

- ከብረት ቢሰራ የተቸነከረበትን ችንካር ለማመልከት ነው።
- ከወርቅ ቢሰራ ወርቅ ንጹህ እንደሆነ ንጹሀ ባህርይ እድፈት የሌለብህ ጽኑ አንተ ነህ ብሎ ለመመስከር ነው።
- ከእንጨት ቢሰራ የተሰቀለው በዕጽ በእንጨት ላይ መሆኑን ለማመልከት ነው።
- ከብር ቢሰራ ተስፋን፣ ዕድልን ያመለክታል። ይኸውም እርሱ ለሰው ልጆች ሁሉ የሆነ ቤዛን በደሙ ከፍሏልና በእርሱ ተስፋ እንድናደርግ ያመለክተናል።

## መስቀል በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ ሃገራችን የክርስቲያን ደሴት ከመባሏም በላይ የእግዚአብሔር ቸርነት ያላት የበረከት የረድኤት አገር ናት። ይኸም የጌታ ግማደ ሰመስቀል በ14ኛው ክ/ዘመን በአጼ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል። አመጣጡም የኢትዮጵያ ነገሥታት የግብጽ ካሊፋዎች ሀገረ ገዥዎች በኃይል ይጋፏቸው ስለነበር የግብጽ ሀገር ገዥዎች ደግሞ የግብጽን ክርስቲያኖች (ኮፕታውያን) ያሰቃዩአቸው ነበር። ስለዚህም ይህ አለመግባባት እንዲወገድና የግብጽ ክርስቲያኖች ዕረፍት እንዲያገኙ በማሠብ

የኢየሩሳሌሙ ፓትርያርክ አቡነ ዮሐንስ ከግብጽ የአህናስ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስንና አባ ማዕምር የሚባሉ ሉዑካን ወደ ኢትዮጵያ መጡ። በዚያን ጊዜ አፄ ሠይፈ አርዕድ አርፈው የልጃቸውን ልጅ አፄ ዳዊት ነግሠው ነበር። እነዚህ ልዑካን በኢትዮጵያውያንና በግብጻውያን ነገስታት መካከል ያለውን ቅራኔ አስወግደው ሲመለሱ አፄ ዳዊት በነበራቸው ቀና መንፈስ አቡነ ዮሐንስ የኢየሩሳሌሙ ፓትርያርክ እሌኒ ንግሥት አስቆፍራ ከአስወጣችው ከጌታ ግማደ መስቀል ክፋይ ለበረከት እንዲልኩላቸው ወርቅ፣ አልማዝ፣ ገጸ በረከት አስጭነው ወደ ኢየሩሳሌም መልዕክተኞችን ላኩ። መልዕክተኞቹ ኢየሩሳሌም ደርሰው ገጸ በረከቱን ለፓትርያርኩ ከሰጡ በኋላ ፓትርያርኩ፣

1. የጌታን ግማደ መስቀል፣ የቀኝ በኩሉን ክፋይ፣
2. ጌታ ላይ አይሁድ የሚኙበትን (ያረጉለት) አክሊለ ሶኩን
3. ሉቃስ የሳላት ምስለ ፍቁር ወልዳ የእመቤታችን ስዕል ላኩላቸው።

መልዕክተኞቹም ተቀብለው ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ አፄ ዳዊት መልዕክተኞቹን ለመቀበል ሲሄዱ የተቀመጡባት ባገራ ፈረስ ጥላቸው መሞታቸውን ታሪካቸው ይናገራል። መስቀሉ ወደ ሀገራችን የገባው መስከረም አስር ቀን ነው። መስቀሉ የተቀመጠው መስከረም 21 ቀን በወሎ ክ/ሃገር በግሸን ማርያም ነው።

በዚህ ሁኔታ የገባው የጌታ ግማደ መስቀል ዛሬም ድረስ ተአምራዊ ነው። ይህም ሀገራችን ኢትዮጵያን ለመስቀል ያላትን ታላቅ አክብሮትና ፍቅር የገለጸችበት አብይ ምስክር ነው። ሕዝቡም ለመስቀል ያለውን ፍቅርና አክብሮት ለመግለጽ ይነቀሰዋል፣



በልብሱ ላይ ይጠልፈዋል። ይህ ደግሞ የሚያሳየው መስቀል በኢትዮጵያውን ዘንድ ምን ያህል ክብር እንዳለው ነው።

## ጾም

ጾም ማለት መዋል፣ መከልከል፣ መቆየት ማለት ነው። ለተወሰነ ጊዜ ከጥሉላት ምግብ ወይም ከእንስሳት ከሚገኝ ምግብ መከልከል፣ ለተወሰነ ሰዓት ደግሞ ምንም ሳይበሉ በመቆየት እግዚአብሔርን በማሰብ የምንፈጽመው ትሩፋት ነው። ከዚህም ሌላ ጾም በዚህ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን አይን ከሚያየው መጥሮ ነገር፣ ጆሮም ከሚሰማው፣ አፍ ከሚናገረው፣ እጅ ከሚሰራው፣ ከሰውነት ሕዋሳቶቻችን ሁሉ የኃጢአት ሥራ መቆጠብ መከልከል ማለት ነው።

## ጾም ምን ይጠቅመናል?

1. ፈቃደ ሥጋን ለፈቃደ ነፍስ ማስገዛት እንድንችል ያደርገናል፤ ይኸውም ሥጋ የሚወዳቸውን ነገር በጾም ጊዜ ከልክለነው ተቆጥበን ስለምንቆይ የነፍስ ኃይል ይበረታል። ካለን እናካፍላለን እንሰጣለን። ክርስትና ማለት እንደ ሥጋ ፈቃድ መኖር አይደለም። ሥጋ ደካማ ስለሆነ ወደ ኃጢአት ይመራናል ለዚህም ጌታ በጌቴ ሴማኒ ለደቀመዛሙርቱ “ከእኔ ጋር አንዲት ሰዓት እንኳ ልትተጉ አልቻላችሁምን? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ መንፈስም ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው” ማቴ. 26÷41። ያለው ለዚህ ነው። እዚህ ላይ መንፈስ የተባለችው ነፍስ ናት መንፈስ የተባለችበት ምክንያት



www.ethiopianorthodox.org

ረቂቅ ስለሆነች ነው። "እግዚአብሔርም የሕይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ።" ዘፍ. 2÷7 ረቂቅ ስለሆነች መንፈስነቷን ይህ ጥቅስ ያረጋግጣል። አንድ ሰዓት እንኳ ልትተጉ አልቻላችሁም ያለው ለፈቃደ ሥጋቸው አድልተው ስለተኙ ነው። ከዚህ የምንማረው በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት እና በምጽዋት ፈቃደ ሥጋውን ለፈቃደ ነፍስ ማስገዛት ያልቻለ እንኳን እስከ ሞት ድረስ ሊታመን፤ ለአንድ ሰዓት እንኳ መጽናት አይችልም። ጌታ ግን "እስከ ሞት ድረስ የታመንክ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ።" ይላል ራእይ 2÷10።

ፈቃደ ሥጋቸውን ለፈቃደ ነፍሳቸው ማስገዛት የማይችሉ ሰዎች ሆዳቸው አምላካቸው ነው፤ ክብራቸው በነውራቸው ነው። ይላል ፊል. 3÷19 "ምን ጊዜም ለሆዳቸው ይገዛሉ እንጂ ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙም" ሮሜ. 16÷17 እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ደግሞ ክደው ከሃይማኖት ለመውጣት ፈጣኖች ናቸው። ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ጽፎልናል።

"እንግዲህ ወንድሞች ሆይ ዕዳ አለብን እንደ ሥጋ ፈቃድ ግን እንኖር ዘንድ ለሥጋ አይደለም፤ እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ፡ ዘንድ አላችሁና በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ። በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና።" ሮሜ. 8÷12-14። ሲል እንዲሁ ለሮሜ ሰዎች በላከው መልዕክቱ፡ "ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነው መንፈስ ግን የዘለዓለም ሕይወት ነው" በማለት ገልጾታል። በመንፈስ የሰውነትን ሥጋ መግደል የተባለው ፈቃድ ሥጋን



ለፈቃደ ነፍስ ማስገዛትን ለመግለጽ ነው። የክርስትና ትርጉሙም ይኸው ነው ሮሜ 8÷6። "ሆድ ለመብል ነው መብልም ለሆድ ነው ያንንም ይሄንንም እግዚአብሔር ያጠፋቸዋል።" 1ቆሮ. 6÷12።

የሥጋ ፈቃድና የነፍስ ፈቃድ እርስ በእርሳቸው ይጣላሉ። "ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፤ እነዚህ እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ" ገላ. 5÷17 ታዲያ ፈቃደ ነፍስ እንዲያሸንፍ መጾም፣ መጸለይ፣ መስገድ ይገባል። ለፈቃደ ሥጋ መገዛት ግን መጨረሻው ሞት ነው። ሮሜ. 6÷22 ራስንም ለኃጢአት መሸጥ ነው ሮሜ 7÷14።

እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ ሰዎች ሁሌ የሚያስቡት ስለ ሥጋ ነው፤ ነፍስ ግን የምታስበው የእግዚአብሔርን ሕግና ትዕዛዝ መጠበቅ ነው። የነፍስ ፈቃድ ይኸው ነውና የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይለናል "አትሳቱ፡ እግዚአብሔር አይዘበትበትም ሰው የሚዘራውን ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና በገዛ ሥጋው የሚዘራ (ለፈቃደ ሥጋው የተገዛ) መበስበስን ያጭዳል በመንፈስ የሚዘራ (ለፈቃደ ነፍሱ የተገዛ) የዘለዓለም ሕይወት ያጭዳል" ገላ. 6÷7 ጳውሎስ ይህን ሲናገር ራሱንም ኃጢአት የሥጋ ፈቃድ ሊያሸንፈው ይታገለው ነበርና እንዲህ አለን "ስለዚህ እኔ ያለ አሳብ እንደሚሮጥ ሁሉ እንዲሁ አልሮጥም ነፋስ እንደሚጎስም ሁሉ እንዲሁ አልጋደልም ነገር ግን ለሌሎች ከሰበኩ በኋላ ራሴ የተጣልኩ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ።" 1ቆሮ. 9÷27። እያንዳንዱ ክርስቲያን ራሱን እየቀጣ እየቆጠበ ሊኖር እንዲችል የራሱን ሕይወት ጳውሎስ በመግለጽ አስረድቶናል። ይህን ከምናደርግበት መሣሪያ አንዱና ዋነኛው ጾም ነው። ጸሎትና

ስግደት፣ ምጽዋትንም በዚሁ ረድፍ የምንፈጽማቸው ሲሆን ሥጋን ለፈቃደ ነፍስ ማስገዛት ይቻለናል።

## 2. መልካም የሆነውን ነገር ከእግዚአብሔር መቀበልን እንድንሻ ያደርገናል።

ለጌታ ደቀመዝሙር ፍቁረ እግዚእ ዮሐንስ በመልዕክቱ እንደጻፈው "በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው። እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምነው ይሰማናል።" 1ዮሐ. 5÷14 የተናገረው ቃል በወንጌል እንዲሁ ተገልጾአል "ለምኑ ይሰጣችኋል ፈልጉ ታገኙማላችሁ..." ማቴ. 7÷7-8 ሲል አስተምሮናል። በዚህ መሠረት የእግዚአብሔር ሰዎች በጾም በጸሎት ሆነው የለመኑትን ሁሉ አግኝተዋል። ሲለምኑም እንደ ፈቃዱ ለምነውታልና። እንደ ሥጋ መሻት ሳይሆን እንደ ነፍስ መሻትና ፍላጎት ለምነውታል የጠየቁትንም ተቀብለዋል።

- የነቢያት አለቃ ሙሴ አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት ጾመ አርባው ቀን እስኪፈጸም እንጀራ አልበላም ውሃም አልጠጣም ይለናል። ዘጸ. 34÷28 ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር በጽላቶቹ ላይ ቃሉን እንዲቀርጽበት ለሙሴ ፈቅዶለታል። ይህ ልመና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በመሆኑ ተቀብሎታል። የእግዚአብሔር ፈቃድ ሕዝቡ በሕጉ እንዲሄዱ ነበርና።
- 1ኛ. ነገ. 19÷8 ኤልያስ ተነሥቶም በላ ጠጣም በዚያም ምግብ ኃይል እስከ እግዚአብሔር ተራራ እስከ ኮሬብ ድረስ አርባ



ቀንና አርባ ሌሊት ሄደ በአንድ ቀን ምግብ አርባ ቀን ያለ ምግብና ውሃ በጾም እንደሄደ ይነግረናል።

- ዳን. 1÷8-15 ዳንኤልና ሶስቱ ብላቴኖች የባቢሎን ቤተመንግሥት ጮማ ሳያገኙቸው ጾሙ እግዚአብሔርም ጥበብን፣ እውቀትንና ማስተዋልን ሰጣቸው። እነዚህ ሰዎች እንደ ፈቃዱ ተመላልሰዋልና የጥበብና የእውቀት ፍሬ አሳደረባቸው።
- ሐዋ. 13÷1-3 "... ከጾሙ ከጸለዩም እጃቸውን ከጫኑባቸው በኋላ አሰናበቱአቸው።" የመንፈስ ቅዱስን ኃይል የተቀበሉትና ለጌታ ሥራ የተለዩት በጾምና በጸሎት መልካም ፍሬ ነው።
- ዕለት ዕለት ቅ/ጳውሎስም በጾም ያሳልፍ ነበር ይህም መልካም የሆነውን ከእግዚአብሔር ለመቀበል ነው። አብያተ ክርስቲያናትን ያስብ ነበርና የነሱም ነገር ይጨንቀው ነበር። 2ቆሮ. 11÷27-28።
- ከላይ ያየናቸውና ሌሎችም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለምነው የተቀበሉ ናቸው ይህም መልካም የሆነውንና የበለጠውን እንዲያገኙ ወደ እግዚአብሔር በጾምና በጸሎት ዘወትር ይለምኑት ነበር።

## 3. ስለ ራስና ስለ ወገን ኃጢአት እንድናዝን ያደርገናል።

"ኃጢአት የለብንም ብንል እንዋሻለን። ነገር ግን በኃጢአታችን ብንናዘዝ ከኃጢአት ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።" 1ዮሐ. 1÷8-10 ኃጢአት ደግሞ እንዲወገድና የመጣ ጥፋት በሕዝብ ላይ እንዳይደርስ በጾም ምህረትን አግኝተዋል። ወደ እግዚአብሔር በመመለሳቸው ክፉት ድነዋል። ለዚህም ነው በኢዩ. 2÷15-17

“በጽዮን መለከትን ንፉ ጾምንም ቀድሱ ጉባኤውንም አውጁ” እያለ የተናገረን። ይህ ጾም በሕብረት በአገር ላይ በወገን ላይ በኃጢአት ምክንያት ከሚመጣ ቁጣ እንድንድን ነው። ያዕቆብ እናንተ ኃጢአተኞች እጆቻችሁን አንጹ ሁለት ሃሳብም ያላችሁ እናንተ ልባችሁን አጥሩ። ተጨነቁና እዘኑ ሳቃችሁ ወደ ሃዘን ደስታችሁም ወደ ትካዜ ይለወጥ። ከጥንት ጀምሮ መናንያን አባቶች ከዓመት ዓመት እየጾሙ፣ እያዘኑ ስለራሳቸው፣ ስለሀገራቸው ሁሉ የሚጸልዩት ለዚህ ነው። ስለ ራስና ስለ ወገን ጾመው ከኃጢአት ጥፋት ድነዋል፤ ስለ ኃጢአታቸው አዝነዋል።

- ዳን. 10፥2 “በዚያን ጊዜ እኔ ዳንኤል ሦስት ሳምንት ሙሉ ሳዝን ነበር...” ጾም ስለ ኃጢአት ማዘን ነው ያልነው ስለ ሕዝቡ ይጸልይ ስለ ነበር ነው “አሁንም አምላካችን ሆይ የባሪያህን ጸሎትና ልመና ስማ ጌታ ሆይ በፈረሰው በመቅደስህ ላይ ስለ አንተ ስትል ፊትህን አብራ። አምላኬ ሆይ በፊትህ የምንለምንህ ስለ ብዙ ምህረትህ ነው እንጂ ስለ ጽድቃችን አይደለምና። ጆሮህንም አዘንብለህ ስማ አይንህንም ገልጠህ ጥፋታችንንና ስምህ የተጠራባትን ከተማ ተመልከት። አቤቱ ስማ አቤቱ ይቅር በል አቤቱ አድምጥና አድርግ ስምህ በከተማህና በሕዝብህ ላይ ተጠርቷልና ስለ ራስህ አትዘግይ።” ዳን. 9፥17-19። ልመናውን ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት በጾም እያዘነ ያቀርብ ነበር። የእስራኤልን ሰዎችና ቅድስቲቱን ከተማ እግዚአብሔር ያስብ ዘንድ ይማፀን ነበር።



- ነህምያ በምርኮ ላይ ያሉትን የእስራኤል ሰዎች ሥቃይና መከራ በሰማና የኢየሩሳሌምም ቅጥር መፍረሱን በነገሩት ጊዜ እያዘነ ወደ እግዚአብሔር ይጾምና ይጸልይ ነበር። “ይህን ቃል በሰማሁ ጊዜ ተቀምጬ አለቀስሁ አያሌ ቀናትም አዝን ነበር በሰማይም አምላክ ፊት እጾምና እጸልይ ነበር” ነህ.1፥1-4

- ዕዝራ በምርኮ ያሉት ወገኖቹ የበደሉት በደል አሳዝኖት ሀዘኑን ይገልጽ የነበረው በጾም ነበር። “ዕዝራም ከእግዚአብሔር ቤት ፊት ተነስቶ ወደ ኤልያሴብ ልጅ ወደ ዮሐናን ጓዳ ገባ ስለ ምርኮኞቹም ኃጢአት ያለቅስ ነበርና ገብቶ እንጀራ አልበላም ውኃም አልጠጣም” ዕዝ. 10፥6

- በንጉሥ አርጤክስስ ዘመን ሃማ የሚባል የንጉሡ ሰው እስራኤልን ለማጥፋት ባቀደና መርዶኪዮስ የሚባለውን ሰው ለመግደል በቆረጠ ጊዜ ንግሥቲቱ አስቴር በሃማ ኃጢአት አዝና ሃዘኗን በጾም ነበር የገለጸችው “... ሄደህ በሱሳ ያሉትን ሁሉ አይሁድ ሰብስበህ ለእኔም ጹሙ ሶስት ቀን ሌሊቱንና ቀኑን አትብሉ አትጠጡም እኔና ደንገጡሮቼም እንዲሁ እንጾማለን” አስቴ. 4፥6 ይህም ሀዘናቸውን በጾም ሲገልጡ እግዚአብሔር ሁሉን ያያልና ወዲያው መልስ መጣላቸው። ሞቱ ለእስራኤላውያን መሆኑ ቀርቶ ለራሱ ለሃማ ሆነ። ይህም ስለ ኃጢአት አዝኖ በመጾም የተገኘ ፍሬ ነው። ማንም የገዛ ፍሬውን ይበላልና ክፉ ዛፍም መልካም ማፍራት አይቻለውም ማቴ. 12፥33

- ሃና ልጅ ስላልነበራት ታዝን ነበር። ሃዘኗንም በጾም ገለጸች እግዚአብሔርም ተመለከታት እግዚአብሔርም ማህፀኗን ዘግቶት ነበርና ጣውንቷ ታስቆጣት ታበሳጫትም ነበር። እርሷም ወደ እግዚአብሔር በምትወጣበት ጊዜ ታበሳጫት ነበር። እንዳትም አትቀምስም ነበር 1ኛ. ሳሙ. 1፥6-7።

- ዳዊት ኃጢአቱን ሰውሮ በእግዚአብሔር ነቢይ በናታን ከተገለጠበት በኋላ በዝሙት የተፀነሰው ልጅ እንደሚሞት ባየና በሕመም በተሰቃየ ጊዜ ሃዘኑን በጾም ነበር የገለጠው ስለ ሠራው ኃጢአት ሁሉ ያዝን ነበር። "ዳዊትም ስለ ሕጻኑ እግዚአብሔርን ለመነ ዳዊትም ጾመ ገብቶም መሬት ላይ ተኛ።" 2ኛ ሳሙ. 12፥16

## 4. <u>ሰውነትን በእግዚአብሔር ፊት እንድናዋርድ ያደርጋል</u>

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በመልዕክቱ "በጌታ ፊት ራሳችሁን አዋርዱ ከፍ ከፍም ያደርጋችኋል" ያዕ. 4፥10 ራስን በማዋረድ በረከት አለ ከፍ ከፍ ማለት አለ። ቅዱስ ጴጥሮስ በመልዕክቱ "ከሃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ" 1ጴጥ. 5፥6 በማለት ተናግሮአል። ራሳችንን ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ብናዋርድ ከፍ እንላለንና። እግዚአብሔርም ራስን ዝቅ በማድረግ የምንለምነውን ልመና ሁሉ ይሰማናል ይለመነናል። ይህም በጾም የሚገኝ ፍሬ ነው።

- ዕዝራ 8፥21-23 "በአምላካችን ፊት ራሳችንን እናዋርድ ዘንድ ከእርሱም የቀናውን መንገድ ለእኛና ለልጆቻችን ለንብረታችንም ሁሉ እንለምን ዘንድ በዚያ በአኅዋ ወንዝ



www.ethiopianorthodox.org

አጠገብ ጾም አወጅሁ። ንጉሡንም የአምላካችን እጅ በሚሹት ሁሉ ላይ ነው ብለን ተናግረን ነበርና በመንገድ ካለው ጠላት ያድነን ዘንድ አፍሬ ነበርና ስለዚህም ነገር ጾምን ወደ እግዚአብሔርም ለመንን እርሱም ተለመነን።" በማለት ይገልጽልናል። ጌታ ስለ ሁሉ ይለመናል። እኛም ልመናችንን ሁሉ በጾም ብናደርገው እንደሚለመነን የሚያስረዳን ነው። "የጠየቃችሁትን (የለመናችሁትን) ሁሉ ወዲያው እንደተቀበላችሁ እመኑ ይሆንላችኋልም።" ማር. 11፥24 ራስን በማዋረድ በእግዚአብሔር ፊት መቅረብ ከፍ ያደርጋል።

- እግዚአብሔር ዳንኤል ራሱን በማዋረድ ያቀረበውን ልመናና ጾም ሁሉ ሰምቶለታል ተመልክቶታል። "እርሱም እንዲህ አለኝ አትፍራ ልብህ ያስተውል ዘንድ ሰውነትህም በአምላክህ ፊት ይዋረድ ዘንድ ካደረግህበት ከመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ቃልህ ተሰምቶአል።" ዳን. 10፥12 እግዚአብሔር በፊቱ ራሱን አዋርዶ በጾም የቀረበውን ዳንኤልን መስማቱን እንዲህ ያረጋግጥልናል። እንዲሁ እኛም ራሳችንን ዝቅ አድርገን የምንጾመው ጾም ውጤት አለው። በመጨረሻም ስለ ቃልህ መጥቻለሁ ብሎታል ይህ አንድ ታላቅ የእግዚአብሔር ኃይል ራስን በማዋረድ ውስጥ እንዳለ ያሳየናል። ያለ ትዕቢትና ኩራት ሆነን የምናደርገው ራስን ማዋረድ በጌታ ዘንድ ታላቅ ያደርገናል።

## 5. <u>ወደ እግዚአብሔር እንድንመለስ ያደርገናል።</u>

ንጉሡ አክዓብ በእግዚአብሔር ፊት ራሱን ከፍ በማድረግ የሸጠ ሰው ነበር። 1ነገ. 20፥20። የሚስቱን የኤልዛቤል ቃል ሰምቶ ሚስቱ በፈጠረችው የተንኮል መረብ ንጹሁ ናቡቴ አክዓብ የናቡቴን እርሻ ስለፈለገ ብቻ በግፍ በድንጋይ ተቀጥቅጦ ተገደለ።

እግዚአብሔርም ኤልያስን ወደ አክዓብ በመላክ ራስህን ሸጠህ ስለ ሠራኸው ኃጢአት እግዚአብሔር ይበቀልሃል። የአንተንም ሰውነት ውሻ ይበላዋል ብሎ የወቀሳ ቃሉን ኤልያስ በተናገረው ጊዜ አክዓብ በሠራው ኃጢአት ተጸጽቶ በመመለስ ራሱን በጾም አዋርዷል። እግዚአብሔርም በመመለሱ በእርሱ ዘመን ሊያመጣ የነበረውን ጥፋት መልሶለታል። "አክዓብም ይህን ቃል በሰማ ጊዜ ልብሱን ቀዶ ገላውን ማቅ አልብሶ ጾመም በማቅ ላይ ተኛ ቅስስ ብሎም ሄደ። ደግሞም አክዓብ በፊቴ እንደተዋረደ አየህን? በፊቴ የተዋረደ ስለሆነ በልጁ ዘመን በቤቱ ላይ ክፉ ነገር አመጣለሁ እንጂ በእርሱ ዘመን ክፉ ነገር አላመጣም የሚል የእግዚአብሔር ቃል ወደ ቴስብያዊው ወደ ኤልያስ መጣ።" 1ኛ ነገ. 20፥27-29።

- የነነዌ ሰዎች በመመለሳቸው በጾምና በጸሎት በመማፀናቸው ከመጣው እሳት ድነዋል። ይህም ጾም ወደ እግዚአብሔር የመመለስ ውጤት መሆኑን ያሳየናል። ወደ እግዚአብሔር መመለስ ከሚገለጽበት አንዱ ይህ ጾም ነው። የነነዌ ሰዎችም ዮናስ የተናገራቸውን ሰምተው በፈሪሃ እግዚአብሔር በመቅረባቸው ምህረትን አውርዶላቸዋል። ዮና. 3፥5-10።
- በዘፍ. 7፥13-24 ያሉትን የሰብአ ትካት (የኖህ ዘመን) ሰዎች ስንመለከት ፈጽሞ ለመመለስና ወደ እግዚአብሔር ለመምጣት ፈቃደኞች ስላልነበሩ በንፍር ውሃ ሊጠፉ ችለዋል። እንዲሁም በዘፍ. 19፥23-28 ያለውንም የሰዶምና የገሞራ ጥፋት ስንመለከት እግዚአብሔርን አንሰማም ብለው እርስ በርሳቸው ስለረከሱ በእሳት ዲን ሊቃጠሉ በቅተዋል። ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ እንዳገኘው እንደ ሎጥ ቢሆኑና ቢጾሙ ቢጸልዩ ኖሮ በዳኑ ነበር።



- ማቴ. 11፥20-24 ወዮልሽ ኮራዚ ወዮልሽ ቤተሳይዳ በእናንተ የተደረገው ተአምራት በጢሮስና በሲዶና ተደርጎ ቢሆን ማቅ ለብሰው አመድም ነስንሰው ከብዙ ጊዜ በፊት ንስሐ በገቡ ነበር። በማለት ጌታ የተናገረውና ኮራዚ ቤተ ሳይዳ የተወቀሱት ባለመመለሳቸው ነው። ስለዚህ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ለጾም ሁል ጊዜ ራሱን ያዘጋጀ መሆን አለበት። ወደ እግዚአብሔር መመለሱ በመጾሙ ያረጋግጣልና።

## 6. <u>አጋንንትን ድል ማድረጊያ መሣሪያ ነው።</u>

- ዘፍ. 3፥1-21 ስንመለከት አዳምና ሔዋን በአምሮትና በመጎምጀት ተይዘው ያን ፍሬ ለመብላት የበቁት ባለመጾማቸው ነው። እንደውም እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጠው የመጀመሪያው ሕግ መጾም መከልከል ነው። ዘፍ. 2፥17 አትብላ በማለት አዋጅ ነግሯል ታዲያ አጋንንት አፍሮ ይሄድ ነበር። ግን ባለመጾማቸው ለሰው ሁሉ ፍዳ መጥቶበት ነበር። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ተወገደልን እንጂ። ለዚህም ነው ቅ/ጳውሎስ በመብል ምክንያት የእግዚአብሔርን ሥራ አታፍርስ የሚለው ሮሜ. 14፥20።
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጾም አጋንንትን ድል ለማድረግ እንደምንችል ጾሞ አሳይቶናል። በመብል ምክንያት የመጣውን ፈተና ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም በእግዚአብሔር ቃል እንጂ በማለት ዲያብሎስን አሳፍሮታል ማቴ. 4፥11። ይህ ደግሞ የጾም ውጤት ነው። አሁንም ቅዱስ ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ሲናገር እንዲህ ብሎአል። "የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስ የሆነ ደስታ ናት

እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችም።" ሮሜ. 14÷17። ይህም ታላቅ የሆነ በረከት ደስታ ያለው በመብል ላይ ሳይሆን በመንፈስ ባለ ደስታ መሆኑን ያረጋግጣል። የዚህ ደስታ ዋናው መንገድ ደግሞ በጾም የምናገኘው ድል ነው። ሙሉ በሙሉ ጌታን ሲፈትነው አጋንንት አፍሮ የተመለሰው በዚህ ታላቅ መንፈሳዊ ተግባር ነው።

- ማቴ. 17÷21 "... ይህ አይነት ግን ከጾምና ከጸሎት በቀር አይወጣም አላቸው።" ሐዋርያት አጋንንቱን ማውጣት አቅቷቸው ተጨንቀው በጠየቁት ጊዜ እናንተ እምነት የጎደላችሁ እስከ መቼ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ በማለት ከመለሰላቸው በኋላ ይህ የሚወገደው በጾምና በጸሎት ነው ሲል ጌታ ራሱ አጋንንትን ማባረሪያው መንገድ ይኸው መሆኑን ገልጾአል። አለመጾም የእምነት ጎዶሎነትና ሆድን የማምለክ ውጤት ነው። በመጾም ግን አጋንንት ያፍራል ክፉ ነገር ይሸሻል ፈተናን ማሸነፍ ይቻላል ያለው የእግዚአብሔር እውነት ይኸው ነው። ስለዚህ በጾም አጋንንትን ድል ማድረግ እንደሚቻል ጌታ አስተምሮናል እያንዳንዳችን በመጾማችን እንባረክበታለን ድል እናደርግበታለን እንጂ አናፍርበትም።

## የጾም አይነቶች

ጾም በሁለት ዓይነት መንገዶች ይከናወናል። ይኸውም

1. በግል
2. በአዋጅ



## የግል ጾም

በግል ስንል አንድ ሰው ስለ ደረሰበትና በእርሱ ላይ ስለ ሆነበት ነገር ሁሉና ስለሚፈልገው ጉዳይ እግዚአብሔር ተገቢውን መልስ እንዲሰጠው የሚጾመው ጾም ነው። ለምሳሌ ዳዊት የልጁን መሞት በሰማ ጊዜ ጾሞአል 2ኛ ሳሙ. 12÷16። እንዲሁም ሰዎች በግላቸው ስለደረሰባቸው ችግርና ስለሚፈልጉት ነገር ሁሉ የሚጾሙት ጾም ነው።

ሌላው በግል ጾም ጊዜ የሚኖረን አመጋገብና ከጥሉላት (ከዓሣ ከሥጋ ከቅቤ) ከመሳሰሉት በሚገባ መጠበቅ ይገባል። ነገር ግን በግል ጾም ጊዜ ጾሙ ይፋ ስላልሆነ ራሱን እንዲሰውር የእግዚአብሔር ቃል ያዛል "በስውር የሚያይህ አባትህ በግልጥ ይከፍልሃል" ማቴ. 6÷18። በዚህ መሠረት ከእርሱና ከእግዚአብሔር ውጭ ጾሙን የሚያውቅበት መኖር የለበትም። ነገር ግን በምግብ አዘገጃጀት በኩል የሚረዳው ሌላ ሰው ካለ ምስጢሩን ሳያሳውቅ የጾም ምግብ እንዲዘጋጅለት መግለጽ ቢኖርበት ያን ያህል ስውርነቱን ይገልጠዋል አያሰኝም። ነገር ግን በግል ጾማችን ጊዜ እኛ እየጾምን ባለንበት ወቅት አንድ ወዳጃችን ቢመጣ ከእርሱ ጋር ማንኛውንም ነገር ደስ ብሎን እንድንመገብ ያዛል። ሃይማኖተ አበው ሠልስቱ፥ ምዕት።

## የአዋጅ ጾም

ይህ ጾም በስውር ሳይሆን ሁሉ አውቆት ክርስቲያን የሆነ ሁሉ የሚጾመው ጾም ነው። መጽሐፍ ቅዱስም በአዋጅ የታወቀ ጾም እንድንጾም ሲያስተምረን እንዲህ ይላል። "በጽዮን መለከትን



www.ethiopianorthodox.org

ንፉ ጾምንም ቀድሱ ጉባኤውንም አውጁ” ኢዮ. 2፥15 በዚህ መሠረት ሰው በአዋጅ ለሁሉ ተነግሮ ሊጾም ይገባዋል። ይህም ከአሕዛብና ክርስቶስን ከካዱ ተለይተን የምንታይበትና የእግዚአብሔር መሆናችን ተለይቶ የሚታወቅበት ነው። “የአህዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበት በመዳራትና በሥጋ ምኞትም በስካርም በዘፈንም ያለ ልክም በመጠጣት ነውርም ባለበት በጣኦት ማምለክ የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃልና” 1ጴጥ. 4፥3። የሥጋ ምኞት አንዱ መብላት መጠጣት ነው። ከዚህ ደግሞ እንድንጾም ይበቃችኋል በማለት ያስረዳናል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደምናነበው ብዙዎች አዋጅ አውጀው ሁሉም በመጾማቸው ከሚመጣ ቁጣ እንደተረፉ እናያለን። ዮና. 3፥5፣ ዕዝ. 10፥6፣ ነህ. 1፥1-4 ይህ የሚያመለክተን በሕብረት በአዋጅ አብሮ መጾም በረከት እንዳለው ግልጽ የሚያደርግ ነው። እንዲሁም በአዋጅ አንድ ሆነው በሕብረት ሐዋርያት በመጾማቸው መንፈስ ቅዱስ ለይቶአቸዋል። ሐዋ. 13፥1-3

ቤተ ክርስቲያናችንም ይህንኑ መሠረት አድርጋ በአዋጅ ጾም ደንግጋ ምዕመናኖቿን የምታጾመውና ሥርዐቱን ሁሉ የምትፈጽመው ይህን አብነት አድርጋ ነው። በዚሁም መሠረት ሰባት የአዋጅ አጽዋማት ቀኖና አላት። ሁሉንም ከነምስጢራቸውና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሳቸው እንመልከት።

**1ኛ) <u>አቢይ (ሁዳዴ) ጾም፡-</u>** ይህ ጾም ሀምሳ አምስት (55) ቀን የምንጾመው ጾም ሲሆን፣ ካሉት አጽዋማት ውስጥ በቁጥሩ ብዛት አንደኛ ነው። አቢይ ማለት ዋና ማለት ሲሆን የአጽዋማቱ ሁሉ



የበላይ በመሆኑ ነው። ይህም ማለት በምስጢሩም በቀናት ብዛቱም። ይህ ጾም የምንጾምበት ምክንያት ጌታ የጾመው ጾም በመሆኑ ነው። ማቴ. 4፥1 ጾሙም ሦስት ክፍሎችና ስምንት ሳምንት አሉት። ሦስቱ ክፍሎች እንደሚከተለው እንገልጻቸዋለን።

55 ቀናት

| ዘወረደ | የጌታ ጾም | ሕማማት |
|---|---|---|
| (ጾመ ሕርቃል) | አርባ ቀን | ስምንት ቀን |
| አንድ ሳምንት | ከቅድስት - ሆሳዕና | የጌታ መከራን |
| የመጀመሪያው ሳምንት | ያለው | የምናስብበትና የምንሰግድበት |

ሳምንታቱ ያላቸውን ምስጢር ከማየታችን በፊት ሳምንታቱን በዝርዝር እንያቸው።

<u>የ55ቱ ቀናት ሳምንት ስያሜ</u>

| 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ | 5ኛ | 6ኛ | 7ኛ | 8ኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ዘወረደ | ቅድስት | ምኩራብ | መጻጉዕ | ደብረዘይት | ገብርሔር | ኒቆዲሞስ | ሆሳዕና |

ዘወረደ (1ኛ) → ጾመ ሕርቃል ይባላል

ከ2ኛ እስከ 8ኛ → የጌታ ጾም ይባላል

- **<u>ዘወረደ /ጾመ ሕርቃል/</u>** ይህ ጾም የጾሙ መግቢያ የመጀመሪያ ሳምንት የምንጾመው ነው። ዘወረደ ያሰኘው አምላክ ሰው ሆኖ መውረዱን መወለዱንና መሰቀሉን

ለማስታወስ ነው። ጾመ ሕርቃል ያሰኘው ግን ታሪኩ ባጭሩ እንደዚህ ነው። በ614 ዓ.ም. ኪርዮስ የሚባል የፋርስ ንጉሥ ኢየሩሳሌምን በመውረር ጥቃት ያደርሳል። በዚህ ወቅት በኢየሩሳሌም ቤተ መዘክር ውስጥ ንግሥት እሌኒ አስቀምጣው በክብር የነበረውን የጌታ ኢየሱስን መስቀል ከሙዚየሙ ይወስዳል። ካህናቱን ይገድላል፣ ከተማይቱንም ያቃጥላል፣ በዚህ ወቅት ስልሳ ሺህ የሚደርሱትን አቁስሎና ገድሎ ሶስት ሺህ የሚሆኑትን ማርኮ ወደ ፋርስ ባቢሎን ይመለሳል። በዚህን ጊዜ ከጦርነቱና ከጥፋቱ ሰለባ ያመለጡት በየዋሻውና ጉራን ጉሩ ገብተው የተሸሸጉት ተሰባስበው ከአስራ አራት (14) አመት በኋላ በ628 ዓ.ም. ጩኸታቸውን የደረሰባቸውን በደል ለፈጣሪያቸውና ለክርስቲያኑ የሮም ንጉሥ ሕርቃል ይነግሩታል። እርሱም ነገሩን አስቦበት ሁሉም የአንድ ሳምንት ጾም እንዲይዙለት ይጠይቃል። ሁሉም ጾሙን በሚገባ ይጾሙታል አንድ ሳመንቷ እንዳበቃች በምርኮ የሄደውን የኢየሱስን መስቀልና የተማረኩትን ክርስቲያኖች ለመመለስ ህርቃል ጦር መዝዞ በኪርዮስ ላይ ተነሣበት ድል ለህርቃል ሆነና መስቀሉን ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። የተማረኩትም በሙሉ ነጻ ወጡ። በዚህ መሠረት ከጌታ ጾም ጋር አያይዘን እንጾመዋለን። ይህም ብዙ ምክንያቶች አሉት። ከእነዚህም ጾሙ የጌታን ጾም በሚጾሙበት ወቅት ላይ ስለተጾመ ቤ/ክርስቲያን አብራ ደንግጋዋለች። ምክንያቱም ለጾም ማድላት ይገባልና።

ሌላው ዝግጅት ማድረግን ያመለክታል። እኛም ስንጾመው እንዲህ ብለን እንጾማለን። ጌታ ሆይ እኔ በኃጢአት የተማረኩ ሰው ነኝ ብዙ ኃጢአቶች ማርከው ይዘውኛል። አንተ ግን ሁሉን



ይቅር ባይ ነህና ህርቃል በዚህ ወቅት የአንተን ክቡር መስቀል ከምርኮ እንዲመለስ ኃይል ሰጥተህ እንዲያሸንፍ ያደረከው አንተ ነህና እኔንም በኃጢአት ላይ ድል እንዳገኝ መንፈሳዊ ጦር በውስጤ እንዲበዛልኝ አድርግ ቅዱስ መስቀልህ ከምርኮ እንደተመለሰ እኔንም በኃጢአት ከመማረክ መልሰኝ በማለት ራሳችንን ለጌታ ጾም የምናዘጋጅበት ነው። ኤፌ. 6፥14-18

ሁለተኛው የጾሙ ክፍል የጌታ ጾም የምንለው ነው። ይህ ጌታ ስለጾመ የምንጾመው ነው። "በጎቹም ድምጹን ያውቃሉና ይከተሉታል ከሌላው ግን ይሸሻሉ እንጂ አይከተሉትም" ዮሐ. 10፥4 ክርስቲያኖች የክርስቶስ በጎች ምዕመናን ናቸውና ጌታን ይከተሉታል። ያደረገውን ያደርጋሉና በዚህ መሠረት እኛም ይህንኑ አውቀን የጌታ በጎች ነንና እንጾማለን ድምጹን ሰምተናልና እንከተለዋለን። ሌላውን ግን አትጹሙ የሚለንን አንከተልም።

ሦስተኛው የጾሙ ክፍል ሕማማት ነው በዚህ ወቅት ቅዳሴ አይኖርም ከምሴተ ሐሙስ በስተቀር ይኸውም የሐሙስ ማታ ራት ማለት ነው። ሰው ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን ገብቶ የጌታን መከራና ሥቃይ እያሰበ በእግዚአብሔር ፊት የሚሰግድበት፣ የሚጸልይበት፣ በእንባ መከራውን እያሰበ የሚያለቅስበት ነው። ሐሙስ ግን ቅዳሴ ይኖራል እግዚአብሔር ይፍታህ ተብሎ ግን አይሸኝም። ቅዳሜ ስዑር ወይም የተሻረ ቅዳሜ ማለት ነው በዚህ ወቅት ስዑር ያሰኘው ቅዳሴ ስለሌለና በጾም ስለሚዋል ነው። በእሁድ ፋሲካ ይሆናል፤ ይህም መሸጋገር ደስታ ማለት ነው። ከኃጢአት ወደ ጽድቅ፣ ከሞት ወደ ሕይወት መጥተናልና ነው።

ሁለተኛው እሁድ ቅድስት በመባል ሲታወቅ ይኸም ጌታ ስለ ዕለተ ሰንበት ቅድስና በምኩራብ ያስተምራቸው ነበርና ይህን ግልጽ አድርጎ የሚያስረዳ ነው። ምክንያቱም አይሁድ በሰንበት ያደርጉት የነበረው ሥርዐት ለሰንበት ያላቸው አክብሮት ፈሩን የለቀቀ ስለነበር የሰንበትን ምስጢር በግልጽ ያስቀመጠበት ነው። ለሰንበት ጌታዋ የሰው ልጅ መሆኑንም አስረድቶበታል። ማቴ. 12÷8

ሦስተኛው እሁድ ምኩራብ በመባል ሲታወቅ በየምኩራቦቻቸው ጌታ እየዞረ ማስተማሩንና ድውዮችንም መፈወሱን የሚያመለክት ንባብና የጌታን መዋዕለ ስብከት በአይሁድ ምኩራብ ውስጥ እንዴት እንደነበረ ያሳየናል። "ኢየሱስ በምኩራቦቻቸው እያስተማረ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዞር ነበር" ማቴ-9÷35።

አራተኛው እሁድ መፃጉዕ በመባል ሲታወቅ ሰላሳ ስምንት አመት ዘመድ ወገን አጥቶ መዳን ያልቻለውን አንድ ሰው ቤቱ ድረስ በመሄድ ጌታ እንደፈወሰው የሚናገር ነው። ይህም በደዌያትና በችግሮቻችን ሁሉ የበላይ የሆነው ጌታ እንደሚያድነን ያመለክተናል። "ተነሣና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ" ዮሐ. 5÷8

አምስተኛ እሁድ ደብረ ዘይት በመባል ይታወቃል። ይህም ማዕከለ ጾም በመሆኑ ብዙ ጊዜ ተለይቶ በሰንበት ስም ወደ ተሰየመው ብቸኛ ወደ ሆነው ሳማ ሰንበት በመሄድ ሰው በአሉን ያከብራል የዚህ እሁድ ትርጉም ጌታ ስለ ዳግም ምጽአቱ



ያስተማረበትን የሚዘክር በመሆኑ ነው። "እርሱም በደብረ ዘይት ተዘምጦ ሳለ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው ንገረን ይህ መቼ ይሆናል የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድን ነው? አሉት" ማቴ. 24÷3 በዚህ መሠረት ደብረ ዘይት ያሰኘው ጌታ ስለመምጣቱና ስለ መጨረሻው የተናገረበት ቦታ መሆኑን ለማስታወስ ነው።

ስድስተኛው እሁድ ገብርሔር በመባል ሲታወቅ ይህም ጌታ መልካም ሠርተው ለታመኑ የሚያደርገው በረከት የሚገለጥበት ሳምንት ነው። ገብርሔር ማለት ቸር ባሪያ የሚል ትርጉም ያለው ነው። "መልካም አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃልና በብዙ እሾምሃለሁ" ማቴ. 25÷21፤ መዝ. 117÷25።

ሰባተኛው እሁድ ኒቆዲሞስ በመባል ይታወቃል። ጌታ ለኒቆዲሞስ ስለ ዳግም መወለድ ያስተማረበትና የገለጸበትን የምናስብበት ነው። "እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም።" ዮሐ. 3÷3።

ስምንተኛ እሁድ ሆሳዕና በመባል ሲታወቅ ትርጉሙም መድኀኒት አሁን አድን አሁን አቅና ማለት ነው። ይህም ጌታ በኢየሩሳሌም መቅደስ ገብቶ ያስተካከለባት ቤቱን ያከበረበት ቀን ነው። "ኢየሱስም ወደ መቅደስ ገባና በመቅደስ የሚገዙትንና የሚለውጡትን አወጣ" ማቴ. 21÷12 ይህ እሁድ የመጨረሻው ሳምንት ነው። መታሰቢያነቱም ጌታ መቅደሱን ያከበረበት በመሆኑ ነው።

## 2ኛ) <u>ጾመ ስብከት (የነቢያት ጾም)</u>

ይህ ጾም ነቢያት የጾሙት ጾም በመሆኑ እንጾመዋለን። ከጌታ ልደት በፊት ስለ መሲሁ ኢየሱስ መምጣትና መገለጥ የጾሙት ጾም ነው። ይህንንም በሱባኤ እንዴት ፈጽመውት እንደነበር መልዐኩ ቅ/ገብርኤል በራእይ ተገልጦ ለነቢዩ ዳንኤል አስረድቶታል። "ዓመፃን ይጨርስ ኃጢአትንም ይፈጽም በደልንም ያስተሰርይ የዘለዓለምን ጽድቅ ያገባ ራእይንና ትንቢትን ያትም ቅዱሰ ቅዱሳኑንም ይቀባ ዘንድ በሕዝብህና በቅድስት ከተማ ላይ ሰባ ሱባኤ ተቆጥሮአል። ስለዚህ እወቅ አስተውልም ኢየሩሳሌምን መጠገንና መሥራት ትዕዛዙን ከሚወጣበት ጀምሮ እስከ አለቃው እስከ መሲህ ድረስ ሰባ ሱባኤና ስድሳ ሁለት ሱባኤ ይሆናል። እርሷም በጭንቀት ዘመን ከጎዳናና ከቅጥር ጋር ትሠራለች" በማለት በትንቢተ ዳንኤል 9፥24-25 በተናገረው መሠረት አባቶች አውጥተውና አውርደው ከኅዳር ወር አጋማሽ ጀምሮ ማለት ከህዳር 15 እስከ ልደት ታህሣሥ 29 እንድንጾመው ደንግገዋል።

መጽሐፍ ቅዱስም "በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ታንጻችኋል" ኤፌ. 2፥20 በማለት እንደተናገረው እኛም ከልደቱና ከነቢያቱ በረከትና ረድኤት ለመካፈል እንጾመዋለን። እኛም ዘወትር በአዲስ ልጅነት እንዲጠብቀን እንለምነዋለን። ነቢያት ሊያዩት ወደው ያላዩትን እኛ እንድናየው ስላደረገን በማመስገንና በልደቱ የሰጠንን እርቅና ሰላም እንዳናጣ እንዲጠብቀን በመማፀን እንጾመዋለን።



## <u>3ኛ) የሐዋርያት ጾም (የሰኔ ጾም)</u>

ይህ ፆም ሐዋርያት ለማገልገል ከመሰማራታቸው በፊት አገልግሎታቸው የቀና እንዲሆን ለመንፈስ ቅዱስ ስራ መለየትን እግዚአብሔርን እንዲሰጣቸው በመለመን የፆሙት ፆም ነው ሐዋ13፥1-3

መሰረታችን ሐዋርያት ናቸውና፤ የዋኖቻችንን ሥራ እኛም መፈጸም ስላለብን እንጾመዋለን። ሐዋርያትን እንዳፀናቸው ፤በአገልግሎቱም እንዳበረታቸውና እንደለያቸው ሁሉ እኛም እንዲያፀናን፣ እንዲያበረታን በመማፀን ለመልካሙ ሥራ እንተጋ ዘንድ በመለመን እንፆመዋለን። ከጰራቅሊጦስ ማግስት ጀምሮ ሐምሌ 5 ድረስ በመፆም ይፈፀማል።

## 4ኛ <u>የፍስለታ ጾም ጾመ ማርያም</u>

ከነሐሴ አንድ እስከ አስራ ስድስት የምናጾመው ሲሆን ይህም እመቤታች በ54 ዓ.ም. ገደማ በጥር 21 ቀን ታርፋለች። ሐዋርያት ሊቀብሯት ሲሄዱ አይሁድ ይበትኖቸዋል። ከስምንት ወር በኋላ በነሐሴ ሐዋርያት አስክሬኗን አግኝተው ቀብረዋታል። እርሷም እንደ ልጇ ትነሳለች በዚህ ጊዜ ቶማስ ስታርግ አግኝቷት ሰበኗን እንደሰጠችው ውዳሴ ማርያም ትርጉም ይናገራል። እርሱም ሐዋርያት ጋር ደርሶ የሆነውን ሁሉ ጠይቆ እሱም ያየውን የእመቤታችንን ትንሣኤ ከገለጸላቸው በኋላ ይህ በረከት ለኛም ይድረሰን በማለት ከነሐሴ 1 እስከ ነሐሴ 14 ከጾሙ በኋላ በ14ኛው

ቀን ጌታ ትኩስ በድን አድርጎ በእመቤታችን መንበርነት ሥጋ ወደሙን ፈትቶ አቁርቦአቸዋል። እነሱም ከቀበሯት በኋላ በ3ኛው ቀን በክብር አርጋለች።

## ለእመቤታችን ትንሣኤ ማረጋገጫ

ይህ የእመቤታችን ማርያም ከሞት የመነሣት ምስጢር ለብዙዎች አልዋጥላቸሁ ብሏቸዋል። እንደውም ይህን ስንናገር አንዳንዶች እመቤታችንን አምላክ ያደረግናት ይመስላቸዋል። ሌሎች ደግሞ እሷን ከጌታችን ጋር እኩል ለማድረግ እየጣርን ያለንና የፈጠራ ወሬ እያወራን ለማሳመን የምንሞክር ይመስላቸዋል። ይህ ሁሉ ግን በርግጥ ትክክለኛ አስተሳሰብ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሞትን እንኳ ያልቀመሱ እስከአሁን እንዳሉ ይነግረናል። ለምሳሌ ያህል ሄኖክ አልሞተም። "ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም እግዚአብሔር ወስዶታልና" ዘፍ. 5፥27። ከእግዚአብሔር ጋር አካሄዱን በማድረጉ ከተወሰደ ይልቅ አምላክን የወለደች እመቤታችን ያቀፈችው፣ በመልዐኩ የተበሰረች፣ በእግዚአብሔር ልዩ ጸጋ የተሰጣት፣ መንፈስ ቅዱስ የጸለለባት በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ያላት እናት ስለሆነች አርጋለች፣ ተነስታለች ቢባል ምን ይደንቃል። አይሆንምስ እንዴት ይባላል "ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና" ሉቃ. 1፥37፣ ዘፍ. 18፥14።

ያለውን የምናየውን እውነት በዘለዓለማዊ እውነት ሊሻርና ሊቀየር እንደሚችል ማስተዋል ይኖርብናል። ኢያሱ ከአሞራውያን ጋር በተዋጋ ጊዜ ፀሀይ እንዳትጠልቅ በማድረግ አቆሟታል ኢያ



10፥12-13። መጨለም ነበረበት ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ብለን መከራከር አንችልም። እንዴት እርሷ ትነሳለች ብለን ልንቃወምም አንችልም። ለዚህም እኮ ነው ጌታ በወንጌል ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ብሎ የተናገራቸው። "እውነት እላችኋለሁ የሰው ልጅ በመንግሥቱ ሲመጣ እስኪያዩ ድረስ እዚህ ከሚቆሙት ሞትን የማይቀምሱ አንዳንድ አሉ።" ማቴ. 16፥28። ታዲያ ጌታ የዋሸ ይመስለናል። የእመቤታችንን መነሣት (ትንሣኤ) መናገር ምኑ ላይ ነው አዲስ የፈጠራ ወጌ የሚያደርገው እነ ኤልያስ በእግዚአብሔር ኃይል ተነጥቀው በደመና እንደሄዱ እንደ ዐረጉ ይናገራል 2ኛ. 2፥11። ይልቅ የአምላክ እናቱ ከሁሉ የተመረጠሽ የተባለች ወደ ሰማይ መውጣቷ ቢነገር ምን ሐሰት ያደርገዋል። "ኢየሱስም በእኔ የሚያምንብኝ ቢኖር እኔ የማደርገውን ብቻ ሳይሆን ከእኔም የበለጠ ያደርጋል።" ዮሐ. 14፥12 ያለው ቃል ሊስተዋል ይገባዋል። እኛም አምላክን በማመኗ የርሱ ባለሟል በመሆኗ ጌታ አስነሣት አልን እንጂ በራሷ ሥልጣን ከሞት ተነሣች አላልንም። እሱ ግን በርሱ በማመኗ ከሰው የተለየ ትንሣኤ እንደልጇ በማግኘቷ ፍጹም ትንሣኤ መነሳቷ በርሱ ፈቃድና ቸርነት እንጂ በማንም እንዳልሆነ ግልጽ ሊሆን ይገባል። እኛም ይህንኑ ትንሣኤ እንነሳለንና። ከሰው ልጆች ቀድማ መነሳቷ ለጌታ ያላት ፍጹም እምነቷንና የማይለወጠው እናትነቷ የፈጸመው ድንቅ እንደሆነ እናምናለን። ማንም ቢከራከር በሁሉ ነገር እመቤታችን እንደምትበልጥ ፈጽሞ ሊያምን ይገባዋል። እኛ ልጅ ነን እርሷ ግን እናት ነችና። እርሷ በጌታ ዘንድ እንደ ልጅ ሳይሆን እናት መሆኗ ሊታወስ ይገባዋል። በጣም ከእኛ ማንነት ጋር ትልቅ ልዩነት መኖሩን አምነን በጸጋ እንደምትበልጣቸው አውቀው ቢያስተውሉት ይበጃል። "ራሱን ዝቅ ያረገ ከፍ ይላልና" ያዕ. 4፥10።

በጣም የሚያስደንቁ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ እውነቶች እንመለከታለን። እኛ መሆን አለበት ብለን ያመንበት በርግጥ በእግዚአብሔር ዘንድ አይሆንምና። እርሱ ግን እንደወደደ ያደርገዋል። ኤልሳዕ ባንድ ወቅት የነቢያት ልጆች ሥፍራ ጠቦአቸው እንጨት ለመቁረጥ ወደ ሜካ በሄዱ ጊዜ የአንዱ ምሳር ብረት በጥልቅ ውሃ ውስጥ ይወድቅበታል። በዚህን ጊዜ ኤልሳዕ እንጨት ቆርጦ ወደ ጥልቁ ውሃ ሲጥለው ብረቱ ተንሳፈፈ እንጨቱ ሰመጠ። 2ኛ. ነገ. 6፥1-7 ብረት በተአምር በውሃ ላይ ሊንሳፈፍ አይችልም ግን ዘላለማዊ እውነት አሸንፎ ይህ ሆነ። እንዲሁ ሁሉ እንደርሱ የጠነከረ እምነትና ጸጋ በረከት የሞላባት እናት ከፍ ከፍ ብላ አርጋለች እንጂ ከውሃው ሥር እንደሰመጠው እንጨት ከመሬት በታች አልቀረችም። አማላጅነቷ ከሁላችን አይለየን።

## 5ኛ) <u>የነነዌ ጾም (ነይ ነይ)</u>

ይህ ጾም የነነዌ ሠዎች የዮናስ ትምህርት ሰምተው የጾሙት ጾም ነው እነርሱም ጾሙን በመጾማቸው ከእሳት እንደ ዳኑ ሁሉ እኛም ጌታ ሆይ እንደ እሳት ከሚፋጅ ኃጢአት ነፃ አድርገን ነነዌን በምሕረትህ አይን እንዳየሁት እኛ እያንዳንዳችንን፣ ሀገራችንንና ሕዝባችንን በምሕረትህ አይተን ተመልከተን በማለት እየተማጸን የምንጾመው ጾም ነው። ዮሐ. 3፥3።

## 6ኛ) <u>ጾመ ድኅነት (አረብ ረቡዕ)</u>

ይህ ጾም የዘለዓለም ጾም ነው ይሉታል። ጾሙ የማይጾመው ከዕለተ ፋሲካ አንስቶ እስከ ጰራቅሊጦስ ባሉት ሀምሳ ቀናት ብቻ ነው። በዚህ ጾም የመዳናችን ምሥጢር የተፈጸመባቸው ቀናት ስለሆኑ ጾሙ ጾመ ድኅነት ተብሏል።



<u>ረቡዕ፡-</u> የምንጾመው ጌታ ላይ ሴራ የጠነሰሱበት ዕለት ስለሆነ የአይሁድን ተንኮል መጥፎነት በማሰብ እንጾማለን። እኛም ጌታ ሆይ ልቤን ከተንኮልና ምቀኝነት ጠብቅልኝ የኃጢአት ሴራ እንዳላደርግ እባክህን ጠብቀኝ ስንል እንጾማለን ለኃጢአት ቀጠሮ በመያዝ ብዙዎች ይኖራሉና። ነገ ዝሙት ለማድረግ ለመስረቅ ለመዋሸትና ለማግኘት በምኞቱ ይጸንሳልና ይህን ሴራ ከልብ እንዲያጠፋልን ከአይሁድ ሃሳብ ጋር በዚህ እንዳንተባበር እንጾማለን። ይህን ሸንጎ ያደረጉበት ጌታ እንዲሞት የወሰኑበት ሸንጎ "ሲንሃሪየም" በመባል ይታወቃል።

<u>አርብ፡-</u> ጌታ የሞተበት፣ የተሰቀለበት ቀን በመሆኑ በጾም እናስበዋለን። ይህም ጌታ ሆይ አንተ ስለኃጢአታችን ስትል ተሰቅለህ አድነኸናልና። አሁን እኛን ያዳንከን ልጆችህን ጠብቀን አጽናን ስንል እንጾማለን።

7ኛ) <u>የገሀድ ጾም</u>፡- ለውጥ፣ ልዋጭ ማለት ነው ፍቺው ከዘይቤው አይገናኝም። ወይም እንደ ዘይቤው ግልጥ ማለት ነው ይፋ ማለት ነው። ገሃድ የጥምቀት ብቻ ነው ጥምቀት ረቡዕና አርብ ሲውል ተለውጦ ማክሰኞና ሐሙስ ይጾማሉ። በነሱ ለውጥ ጥምቀት የሚውልባቸው ረቡዕና አርብ ፍስክ ቀን ሆነው ይውላሉ።

በሌላው ቀን ቢውል የጥምቀት ዋዜማ አይበላም። ሰኞ ጥምቀት ቢውል እሁድ ጥሉላት ማለት ሥጋ ቅቤ ወዘተ አይበላም። ነገር ግን ከውሃ ከምግብ ግን አይጾምም። ከአርብና ረቡዕ ውጭ

ሲውል በዚህ መልኩ ይከናወናል። ገሀድ ለጥምቀት ብቻ ነው። አንዳንዶች ግን ለልደትም ገሃድ ብለው ይጾማሉ ይህ አጉል ልማድ ነው። ምክንያቱም ከልደት በፊት ያሉት ቀናት በሙሉ ከጾመ ነቢያት ጋር ይጾማሉ። ስለዚህ ገሃድ የለውም የማይጾሙ ግን ገሃድ ብለው ይጾሙታል።

## በጾም ወቅት የማይበሉ ምግቦች

መጽሐፍ ቅዱስና ፍትሐ ነገሥት እንደሚያስረዳን በጾም የማንመገባቸው ምግቦች የእንስሳት ውጤት የሆኑትን በሙሉ ነው። ቅቤ እደማይበላ በመዝ. 108፥24 ተጽፎአል። ሥጋና የመሳሰሉት እንደማይበሉ ዳን. 10፥3 ላይ ተጽፎአል። ሌላው አጨቃጫቂ ጉዳይ ዓሣ ነው። ዓሣ በመሠረቱ አትክልት ወይ ድንች ወይ ካሮት አይደለም። እንስሳ ነው፤ ጾም አለው ስለዚህ አይበላም። ብዙ ሊቃውንት የተከራከሩበት ቢሆንም ተከራካሪዎቹን የሚያስታርቅ ቃል ሠለስቱ ምዕት በዚሁ አንቀጸ ጾም ላይ አስቀምጠዋል። ይኸውም ለእመ ተገዓገዝክሙ በጾም አድልው ለጾም በጾም ምክንያት ብትከራከሩ ለጾም አድሉ ብለዋል። ይህን መሠረት አድርገው በሦስተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ፓትርያርክ በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ጊዜ ዓሣ መጾም አለበት ተብሎ በሲኖዶስ ስለተወሰነ ጭቅጭቁ መፍትሔ አግኝቷል።

የሚከተሉትን ጥቅሶች ቤትህ አንብባቸው 1ኛ ቆሮ. 8፥8፣ 1ቆሮ. 6፥12፣ ሮሜ 14፥17፣ ዕብ. 13፥9 ረጋ ብለህም አጢናቸው።



## በፕሮቴስታንት የሚነሱ የጾም ጥያቄዎች

1. ጾም መጾም ቢገባም ደስ ባለን ጊዜ እንጂ ታውጆ መጾም የለብንም።
2. ስንጾም ሥጋ እንዳንበላ እንከለከልም ወደ አፍ የሚገባ አያረክስምና ይላሉ።

ጾም በሕብረት በአዋጅ ስለመሆኑ ቀደም ብለን ስለጾም በገለጽንበት በስፋት የተገለጠ ስለሆነ አሁን አናነሳውም።

ሁለተኛው አባባል ፈጽሞ ከጾም ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የለውም። እነሱ ለጾም የሚጠቅሱት ጥቅስ እንዲህ ይነበባል "ከሰው የሚወጡት ሰውን የሚያረክሱ ናቸው እንጂ ከሰው ውጭ የሚገባውስ ሊያረክሰው የሚችል ምንም የለም" ማር. 7፥15 ይህን ጌታ የተናገረው ለጾም ሳይሆን እጅ ሳይታጠቡ መብላትን እንደመርከስ ለቆጠሩት አይሁድ ፈሪሳውያን ነው። ማር. 7፥2 ምክንያቱም ሐዋርያት እጅ ሳይታጠቡ መብላታቸውን አይተው ወግ ተላለፉ በማለት ላቀረቡት ጥያቄ ባልታጠበ እጅ መብላት እንደማያረክስ ገለጸ እንጂ ከጾም ጋር የሚያገናኘው አንዳችም ቃል የለውም። ሲጠቅሱ አስተውለው እንዲጠቅሱ እንመክራቸዋለን።

ይቆየን!

ወስብሐት ለእግዚአብሔር